# ቅድስት ድንግል ማርያም

(ሕይወቷ ❖ ተአምራቷ ❖ መገለጧ)

የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ
ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ እና ሌሎች ጳጳሳት እንደጻፉት

አያሌው ዘኢየሱስ እንደተረጎመው

ኅዳር ፳፻፩ ዓ.ም.
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

## ምስጋና

- የትርጉሙን ረቂቅ ውድ ጊዜውን መሥዋዕት በማድረግ አንብቦ ገንቢ አስተያየቱን ለሰጠኝ ለወንድሜ ለዲያቆን ሲራክ ዘኢየሱስ፤
- በመጻሕፍቱ ውስጥ ያሉትን ፎቶግራፎች በሙሉ «ስካን» ላደረገልኝ ወንድሜ ዘውዱ ተካ፤
- እተረጉማቸው ዘንድ የእንግሊዘኛ መጻሕፍቱን ለሰጡኝ ለወንድሜ ዲያቆን ተሾመ ግርማ፣ ለወንድሜ ሀብታሙ ተገኝ እና ለእኅቴ አዜብ በርሔ፤
- የመጽሐፉን 30% ዋጋ ለሸፈነችልኝ ለእህቴ ወለተ ብርሃን፤
- መጻሕፍቱ ተተርጉመው እንዲወጡ በተለያየ መንገድ ለረዱኝ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ በሙሉ መንፈሳዊ ምስጋናዬን በእግዚአብሔር ስም አቀርብላቸዋለሁ።

**የመጻሕፍቱ የእንግሊዘኛ እርእስት፡-**
"The Holy Virgin St. Mary"
"St. Mary's Modern Miracles"
"The apparition of St Virgin Mary at Zeitoun Church"

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን ደንብና ሥርዓት ጠብቆ የተዘጋጀ መጽሐፍ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

አድራሻ፡- ደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን
ወይም
በስልክ ቁጥሮች 0911 15 75 96፤0911 61 59 15
አዲስ አበባ



# እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም

www.ethiopianorthodox.org

በስመ አብ፣ ወወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስ፣ አሐዱ አምላክ፤አሜን።

## ከተርጓሚው

ውድ አንባብያን ወገኖቼ በሙሉ! ከዚህ መጽሐፍ ቀደም ሲል ከብፁዕ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ መንፈሳዊ መጻሕፍት መካከል «የተራራው ስብከት»፣ «የዲያብሎስ ውጊያዎች»፣ «የነፍስ አርነት»፣ «የተስፋ ሕይወት»፣ «መንፈሳዊው ሰው»፣ «መንፈሳዊ ውጊያዎች»፣ «መንፈሳዊው መንገድ»፣ «የባሕታውያን አባቶች ሕይወትና የመዝሙራት ተመስጦ»፣ «መንፈሳዊ ጾም»፣ «እግዚአብሔርና ሰው»፣ «መንፈሳዊ ቃላትና ጥቅማቸው» እና «ሲና 1ኛ መጽሐፍ» የተባሉትን አሥራ ሁለት መንፈሳዊ መጻሕፍት እግዚአብሔር ፈቅዶልኝ በተከታታይ ተርጉሜ ማቅረቤ በእናንተ ዘንድ ይታወቃል። ከዚህ በተጨማሪ ከቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ መንፈሳዊ መጻሕፍት መካከል አንዱን «ሀብታምና ድሀ» በሚል ርዕስ ተርጉሜ ማውጣቴ አይዘነጋም።

አሁንም ቸር፣ መሐሪ፣ ይቅር ባይና ርኅሩኅ የሆነው ልዑል እግዚአብሔር ዕድሜና ጤና፣ ብርታትና እውቀት ሆኖኝ "The Holy Virgin St. Mary"፣ "St. Mary's Modern Miracles" እና "The appariation of St Virgin Mary at Zeytoun Church" ተብለው የተዘጋጁትን ሦስት አጫጭር የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ፣ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ 4ኛ መንፈሳዊ ልጆችና የአለቃ ቡትሮስ ጋይድ መጻሕፍትን አንድ ጥራዝ አድርጌ በሚቀራረብ ርዕስ «ቅድስት ድንግል ማርያም፤ሕይወቷ፣ ተአምራቷና መገለጧ» ብዬ በመተርጎም እንዳቀርብ የማያልቅ ቸርነቱን ስላበዛልኝ ክብርና ምስጋና ለእርሱ ይድረሰው!

የመጀመሪያውና ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የሕይወት ታሪክ የሚናገረውን መጽሐፍ የጻፉት የግብጽ 117ኛ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሲሆኑ መጽሐፉ ሙሉ ለሙሉ የሚያወራው ስለ ድንግል ማርያም አጭር የሕይወት ታሪክ ነው። ሁለተኛውንና በዘመናችን ስለታዩት የቅድስት ድንግል ማርያም ተአምራት የሚያስረዳውን መጽሐፍ ያዘጋጁት ደግሞ የግብጽ 116ኛ ፓትርያርክ የሆኑት የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ መንፈሳዊ ልጆች ናቸው። ሦስተኛውንና የመጨረሻውን መጽሐፍ ያዘጋጁት ዜይቶን/ግብጽ ውስጥ በስሟ በተሰየመው የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስተዳዳሪ የሆኑት አለቃ ቡትሮስ ጋይድ ሲሆኑ መጽሐፉ የሚናገረውም ድንግሊቱ በዜይቶን ተገልጣ ለብዙ ሰዎች ስለ መታየቷ ነው። ምንም እንኳ ሁለተኛውንና ሦስተኛውን መጻሕፍት ያዘጋጁት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ባይሆኑም በሁለቱም መጻሕፍት ላይ የራሳቸውን በቂ አስተያየት ሰጥተዋል።

መጽሐፍ ቅዱስና ሌሎች አዕዋልድ መጻሕፍት ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሲጻፍላት የሚገባትን ያህል የጻፉላት አይመስለኝም። በዚህ ዓለም ጥበብ ታዋቂ የሆኑ ምድራውያን ሰዎችን ለወለዱ እናቶች ብዙ ይጻፍላቸዋል። እናታችንና እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የወለደችው አማናዊውንና ሰማያዊውን አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን ስለሆነ ስለ እርሷ ብዙ ሊጻፍላት ይገባል ብዬ አምናለሁ። ሊጻፍላት የሚገባው እስከ ምን ድረስ ነው? ብዬ ራሴን ስጠይቅ ደግሞ የሚጻፍላት ጽሑፍ ወሰን የማይኖረው ይሆንብኛል። ልጆች ከእናቶቻቸው - እናቶችም ከልጆቻቸው ጋር ያላቸው የፍቅር ቁርኝት ጥብቅ ነው፤ይህን በእርሷና በልጇ ሕይወት ውስጥ ስመለከተው እጅግ ጽኑ ይሆንብኛል። ጸነሰችው፣ ወለደችው፣ ታቀፈችው፣ ጡቶቿን አጠባችው፣ አባበለችው፣ አስተኛችው፣ አዘለችው፣ ስደት ይዛው ሄደች፣ ከስደት ይዛው ተመለሰች፣ መከራውን ሲቀበል አብራው ተቀበለች . . . የሚሉት ቃላት ከመጻፍ በላይ እጅግ ጥልቅ ናቸው። ለሁላችንም የቃላቱ ጥልቀት ከመጻፍ በላይ ስለሚሆኑብን ስለ እርሷ ከመጻፍ የተቆጠብን ይመስለኛል።

የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነልኝ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባቶች የተጻፉ ሌሎች የእናታችን የቅድስት ድንግል ማርያም መጻሕፍትን ተርጉሜ ለማውጣት እሞክራሁ። የእግዚአብሔር ቸርነትና የድንግል ማርያም አማላጅነት ዘወትር አይለየን።

**አያሌው ዘኢየሱስ**
**መስከረም 8 ቀን 2000 ዓ.ም.**

**መጽሐፍ አንድ**
**ቅድስት ድንግል ማርያም (ሕይወቷ)**
**አዘጋጅ:- ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሣልሳዊ 3ኛ**

## ማውጫ


ገጽ

ምዕራፍ አንድ
- ❖ እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ........ 8

ምዕራፍ ሁለት
- ❖ በስሟ የተመሠረተው ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን ........ 10

ምዕራፍ ሦስት
- ❖ የድንግሊቱ ታላቅነት ........ 10

ምዕራፍ አራት
- ❖ በተአምራት የተከበበ ሕይወት........ 13

ምዕራፍ አምስት
- ❖ የድንግሊቱ ጾም ........ 14

ምዕራፍ ስድስት
- ❖ በዓላቶቿ ........ 16

ምዕራፍ ሰባት
- ❖ ድንግል ማርያም በቤተ ክርስቲያን እምነት ውስጥ ........ 18

ምዕራፍ ስምንት
- ❖ የቅድስት ድንግል ማርያም ቅጽል ስሞችና ምሳሌዎች ........ 19

ምዕራፍ ዘጠኝ
- ❖ የቅድስት ድንግል ማርያም ጠባያት ........ 25

ምዕራፍ አሥር
- ❖ እርስዋንም ሆነ ሥዕላቶቿን ቀድሱ ........ 31

**መጽሐፍ ሁለት**
**በዘመናችን የተገለጡ የድንግል ማርያም ተአምራት።**
**አዘጋጆች:- የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ 6ኛ ልጆች**

- ❖ ለሴቶች የሆኑ ምሕረትና ተአምራት። ........ 33
- ❖ የሴቶች የክብር ታሪኮች። ........ 33
- ❖ ቅዱሳት ሴቶች። ........ 34
- ❖ ታላቋ እመቤት። ........ 35
  - ሀ. ድንግሊቱ በክሊቭላንድ (Cleveland)። ........ 36
  - ለ. ድንግሊቱና መነኩሴው። ........ 37
  - ሐ. ድንግሊቱና አካል ጉዳተኛዋ ብላቴና። ........ 38
  - መ. ከድንግል ማርያም የቀረበ ስጦታ። ........ 39
  - ሠ. ራእይና ቃል ኪዳን። ........ 40
  - ረ. ሲፈጠር ጀምሮ ዓይነ ሥውር ለነበረው ሰው የሆነ የድንግሊቱ አማላጅነት። ........ 42
  - ሰ. መለኮታዊው መልእክት። ........ 44
  - ሸ. ድንግል ማርያም አባ ገብርኤልን እንደረዳችው።........ 47
  - ቀ. ድንግል ማርያም፤ትቀበያታለሽ? ........ 50
  - በ. የገዳሙ እድገት። ........ 54
  - ተ. ድንግል ማርያም በስጦታ ከተማ። ........ 55
  - ቸ. ድንግል ማርያምና አባ ስምዖን። ........ 56


www.ethiopianorthodox.org

ኀ. የጠፋችውን ልጃገረድ ድንግል እንደመለሰቻት:: ............ 59
ነ. የአባ ሚካኤል ሕይወት:: ............ 60
ኘ. ድንግል ማርያም በአቡ ዛቢ (Abou Zaby):: ............ 62
አ. የድንግል ማርያም ሥዕል:: ............ 63
ከ. ታማኙ ተጠርጣሪ:: ............ 64
ኸ. ድንግል ሆይ ይቅር በዪኝ:: ............ 65
ወ. ውቢቷ ርግብ ድንግል ማርያም:: ............ 66
ዐ. ድንግል ማርያም በአሱዩት (Assuit):: ............ 67
ዘ. ቅድስት ማርያምና አባ አባኑብ (St. Abanoub):: ............ 67
ዠ. ከድንግል ማርያም የተላከ መልዕክት:: ............ 68
❖ ይህ ሁሉ ምን ማለት ነው? ............ 68

**መጽሐፍ ሦስት**
**ድንግል ማርያም በዜይቱን ቤተ ክርስቲያን እንደ ተገለጠች::**
አዘጋጅ:- የዜይቱን ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ አባ ቡትሮስ ጋይድ::

መግቢያ:: ............ 79
❖ በፓትርያርኩ የተመራ የልዑካን ቡድን:: ............ 80
❖ በዜይቱን የተገለጡ ተአምራታዊ ድኅነቶች:: ............ 82
❖ በዜይቱን የምትገኘው የድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን:: ............ 82
የድንግል ማርያም መገለጥ::
❖ በተለይ በዜይቱን ልትገለጥ የቻለችው ለምንድር ነው? ............ 83
❖ ድንግሊቱ መገለጧን የገለጠችው ለምንድር ነው? ............ 84
❖ ቤተ ክርስቲያንና ድንግል ማርያምን ቅድስት የምንልበት ግንዛቤ:: ............ 86
❖ ሙስሊሞችና ቅድስት ድንግል ማርያም:: ............ 87
❖ የድንግሊቱ ሥዕል:: ............ 87
❖ ድንግል ማርያም በዜይቱን ላይ የተገለጠቸው እንዴት ነው? ............ 88
❖ ድንግሊቱ በተገለጠች ጊዜ የታዩ ያልተለመዱ ሁኔታዎች:: ............ 89

በድንግል ማርያም የተፈጸሙ ተአምራት::
❖ ድንግል ማርያም ብረት እንዳሟሟች:: ............ 91
❖ ኢጥሪብ (Itreeb) ውስጥ የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ተአምራት:: ............ 92
❖ ሦስተኛው ተአምር:: ............ 93

ድንግል ማርያም ስትገለጥ የተፈጸሙ ተአምራት:: ............ 95
❖ ድንግል ማርያምና የቤተ ክርስቲያኗ ካህን:: ............ 95
❖ ሙሽራሽ ይህ ነው:: ............ 96
❖ ድንግል ማርያምና የዘይቱ ብልቃጥ:: ............ 97
❖ ድንግል ማርያምና በካንሰር በሽታ የተጠቃችው ሴት:: ............ 97
❖ ሰባቱ መስቀሎችና በቅብጥ ቋንቋ «አቭኖቲ» (Avnoti) ወይም ደብዳቤዎች የሚለው ቃል:: ............ 98
❖ ድንግል ማርያም የዐይኗን ብርሃን እንደመለሰችላት:: ............ 99
❖ ድንግል ማርያምና የድሆች ፍቅር:: ............ 99
❖ ብርቱ የጆሮ ውስጥ ህመም:: ............ 100
❖ ከችግሮቼ እንድወጣ እርዳኝ::............ 100

- - - - - - - - - - - - - - - - - - - -

❖ «የድንግል መገለጥ እስከ ዛሬ ድረስ እየታየ ነው» ............ 104
❖ «ካይሮ ውስጥ የድንግል መገለጦች ይፋ ሆኑ::» ............ 105



## መጽሐፍ አንድ

# ቅድስት ድንግል ማርያም

(ሕይወቷ)

አዘጋጅ:- ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለሚከተሉት ርዕስ ጉዳዮች ታነባላችሁ:-

ምዕራፍ አንድ
❖ ቅድስት ድንግል ማርያም::

ምዕራፍ ሁለት
❖ በስሟ የተመሠረተው ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን::

ምዕራፍ ሦስት
❖ የድንግሊቱ ታላቅነት::

ምዕራፍ አራት
❖ በተአምራት የተከበበ ሕይወት::

ምዕራፍ አምስት
❖ የድንግሊቱ ጾም::

ምዕራፍ ስድስት
❖ በዓላቶቿ::

ምዕራፍ ሰባት
❖ ድንግል ማርያም በቤተ ክርስቲያን እምነት ውስጥ::

ምዕራፍ ስምንት
❖ የቅድስት ድንግል ማርያም ቅጽል ስሞችና ምሳሌዎች::

ምዕራፍ ዘጠኝ
❖ የቅድስት ድንግል ማርያም ጠባያት::

ምዕራፍ አሥር
❖ እርስዋንም ሆነ ሥዕላቶቿን ቀድሱ::



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ አንድ
## ቅድስት ድንግል ማርያም

ለእናታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም የተተነበየውን ትንቢት የሚያህል ትንቢት የተተነበየላትና የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የተጻፈላት ሴት የለችም። ስለ እርስዋ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ብዙ ምሳሌዎች ተጠቅሰዋል። እንዲሁ በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስለ ሕይወት ታሪኳ፣ ስለ ውዳሴዋና ስለ ተአምራቷ የተጻፉ ቃላት አሉ።

በቀደሙ ቅዱሳን አባቶቻችን መጻሕፍት ውስጥ ክብሯን የሚያጎሉ አገላለጾችና ተመስጦዎች እንደ ምን የበዙ ናቸው! ቤተ ክርስቲያን እርስዋን ለመጥራት የምትጠቀምባቸው ቅጽል ስሞችዋና ውዳሴዎቿ ምንኛ ምሉዕ ናቸው! ከመጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ የተወሰዱ ምስጋናዎቿስ እንደምን ድንቅ ናቸው!

እርሷ የሁላችንም እናት ናት፤እርሷ የሁላችንም እመቤት ናት፤ እርሷ የእኛነታችን መመኪያ ናት፤እርስዋ ከንጉሡ በስተቀኝ የቆመችው ንግሥት ናት፤እርሷ ዘላለማዊ ድንግል ናት፤እርሷ የእግዚአብሔር ጸጋ የሞላባት ንጽሕት ቅድስት ድንግል ናት፤እርሷ ተራዳኢ፣ ረዳትና ርኅሩህ እናት ናት፤እርሷ የብርሃን፣ የምሕረት፣ የድኅነትና የአማናዊው ወይን እናት ናት።

ቤተ ክርስቲያን ክብሯን ከሊቃነ መላእክት በማበለጥ በውዳሴዎቿና በዝማሬዎቿ ውስጥ «ድንግል ሆይ፤አንቺ ከሱራፌልና ከኪሩቤል የሚበልጥ የመወደድ ግርማ አለሽ. . .» በማለት የምታመሰግነው ይህችን ቅድስትና ድንግል እናት ነው።

ቅድስት ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ ውስጥ ስላደገች የጸሎትና የተመስጦ ሕይወትን ከልጅነቷ አንስቶ ኖራለች። እርሷ እግዚአብሔር ያድርባት ዘንድ የመረጣት ቅድስት እናት ናት።

የዚህች ድንግል መወለድ ትውልድ ለረዥም ዘመናት በተስፋ ጠብቋል። የዘመኑ ፍጻሜ መድረሱ የታወቀውም በእርሷ በኩል ነው። ገላ 4:4።

እርሷ የሔዋንን እፍረት በማጥፋት ከኃጢአት በኋላ የነበረውን የሴቶችን ዝና አድሳለች።

እርሷ በድንግልና ያለች የእግዚአብሔር እናት ናት።





መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስደት ወደ ግብጽ በመጣና በምድራችን ላይ ለዓመታት በተቀመጠ ጊዜ ሀገራችንን ባርኮልናል ቀድሶልናልም።

እርሷ ከ32 ዓመታት በፊት ግብጽ ውስጥ በሚገኝ ዜይቶን (Zeitoun) በተባለ ሥፍራ ስትገለጥ በብርሃኗ፣ በገጽታዋና በጉብኝቷ የብዙዎቻችንን መንፈሳዊ ኅሊና ማርካ ነበር።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ብዛት ባላቸው ቦታዎች ላይ የተለያዩ ተአምራት ስለምትሠራ በዓላቶቿን ከዚህ ጋር በማያያዝ እናከብራለን፤ የተአምራቷ ታሪክ ተነግሮ አያልቅምና።

በቅብጣውያን (Copts) ዘንድ ያለው መንፈሳዊ የእምነት ስሜት በልዩ ልምድና መነሣሣት ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር በጥልቀት የተዋሀደ ስለሆነ እርሷ ለእኛ እንግዳ አይደለችም። ባለፉት ዘመናት በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም መጎብኘታችን ለእኛና ለቤተ ክርስቲያናችን እንደ ምን ያለ ታላቅ ክብር ነው! ከብዙ ዓመታት አስቀድሞ ድንግል ማርያም በቤተ ክርስቲያናችን ጉልላቶች ላይ መገለጧ ታላቅ ክብራችን ነው!

ክርስቲያኖች ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የበለጠ የሚወዱት ምንም ዓይነት ሰው የላቸውም።

በግብጽ ውስጥ የሚገኙ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በዓላቶቿን ያከብራሉ። በተለይም **Kiahk** (ታኅሣሥ) በተባለው ወር ውስጥ ለእርስዋ በሚቀርበው ቅዳሴ ውስጥ ያሉ ውዳሴዎች ምንኛ የበዙ ናቸው! የሚዘመሩላት የቤተ ክርስቲያን መዝሙራት፣ የሚነበቡላት የዳዊት መዝሙራትና የሚዜሙላት የክብሯ መገለጫ ዜማዎች በሙሉ ለእርሷ የተሰጡ ናቸው።

ካቶሊካውያኑ እንዲሁ «የድንግል ማርያም ወር» ብለው የሰየሙት አንድ ወር አላቸው።

ግብጽ ውስጥ ከሚገኙ የመነኮሳት ገዳማት መካከል ኤል ባራሙስ (El Baramous) ገዳም፤ኤል ሶሪያን (El Sourian) ገዳም፤ኤል ሞሃራክ (El Moharrak) ገዳም የተባሉት ገዳማት ሁሉ በእርስዋ ስም የሚጠሩ ናቸው። እነዚህ ገዳማት በአሁኑ ሰዓት ግብጽ ውስጥ የሚገኘውን የገዳማት አጠቃላይ ቁጥር ሲሶ (አንድ አራተኛ) የሚይዙ ናቸው።



www.ethiopianorthodox.org

ሃሬት ዙዋላህ (Haret Zuwalah) ተብሎ የሚጠራና ካይሮ ውስጥ የሚገኝ አንድ የመነኮሳይያት ገዳም በእርሷ ስም የሚጠራ ነው:: በምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት በስሟ የሚጠሩ ገዳማትና ትምህርት ቤቶች ምንኛ የበዙ ናቸው!

**ምዕራፍ ሁለት**
**በስሟ የተመሠረተው ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን**

በሐዋርያት ዘመን በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ስም የታነጸውና የተጠራው የመጀመሪያው ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን የሚገኘው ፊልጵስዩስ ውስጥ ነው:: ግብጽ ውስጥ በስሟ የተጠራው ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን የታነጸው ደግሞ በ16ኛው ፓትርያርክ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጤዎናስ (Theonas) ክፍለ ዘመን ሲሆን ጊዜውም 274 ዓ.ም. ነው::

ታዋቂ ከሆኑት የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንዱ በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ በ23ኛው የግብጽ ፓትርያርክ በአቡነ ቴዎፍሎስ የፓትርክና ዘመን Hator 5 (ኅዳር 5) ቀን ነው:: ይህ ቤተ ክርስቲያን የሚገኘው ኤል ሞሃራክ (El Moharrak) ገዳም ውስጥ ነው::

እርሷ ግብጽ ውስጥ በስደት ሳለች በጎበኘቻቸው ሥፍራዎች ላይ እንዲሁ በስሟ የተጠሩ አብያተ ክርስቲያናት ታንጸው ይገኛሉ::

በዚህ አጋጣሚ አውሮጳ ውስጥ «የዜይቱኗ ድንግል» በሚል ስም የሚጠሩ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ፈረንሳይና ቪዬና ውስጥ እንዳሉን ለመግለጽ እወዳለሁ::

**ምዕራፍ ሦስት**
**የድንግሊቱ ታላቅነት**

የድንግሊቱ ታላቅነት በቀኖና የተገለጠው በ431 ዓ.ም. ኤፌሶን ውስጥ በተካሄደው የኤፌሶን ቅዱስ ጉባኤ ላይ ነው:: በዚህ ጉባኤ ላይ 200 ጳጳሳት ተገኝተው ነበር:: እነዚህ ቅዱሳን አባቶች በዚህ ጉባኤ ላይ ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ባጸኑት የቀኖና መቅድም ውስጥ ለክርስቲያኖች እምነት የሚሆነውን ቃል እንዲህ በማለት አስፍረውታል:- «የእውነተኛው ብርሃን እናት የሆንሽ ሆይ፤እናከብርሻለን ከፍ ከፍም እናደርግሻለን፤ የእግዚአብሔር እናት የሆንሽው ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ፤የዓለም ሁሉ መድኃኒት የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ስለ ወለድሽልን እርሱ ወደ እኛ መጥቶ ነፍሶቻችንን ከሞት ባርነት ነጻ አውጥቶልናል::»





በዚህ የክርስቲያኖች ጉባኤ ላይ ይህን መቅድም ለማዘጋጀት መሠረቶቹ ምንድር ነበሩ? የዚህን መልስ ከዚህ በመቀጠል እንሰጣለን:-

ድንግሊቱ የተባረከች ቅድስት ስለ ሆነች በረከቷ በትውልድ ሁሉ ውስጥ የማይቋረጥ በረከት ነው:: ይህ ደግሞ በጸሎቷ ውስጥ እንዲህ ተብሎ ተረጋግጧል:- «እነሆም ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ሁሉ ይሉኛል፤. . .» ሉቃ 1:48::

ቤተ ክርስቲያን ድንግሊቱን በክብር ስሟ ወይም በምሳሌ «ንግሥት» ብላ ትጠራታለች:: የዚህ የክብር ስሟ መገኛ በመዝሙረ ዳዊት ላይ የተጻፈው ቃል ነው:- «በወርቅ ልብስ ተጎናጽፋና ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች::» መዝ 44:9::

ይህ ስለሆነ ነው ብዙ ሠዓሊያን የእመቤታችንን ሥዕል ሲስሉ በራሷ ላይ የክብር አክሊል ደፍተውና ከኢየሱስ ክርስቶስ በስተ ቀኝ አድርገው የሚስሉት::

የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ክብር ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል ለእርሷ ባቀረበው ሰላምታ ውስጥ ተገልጦአል:-

«መልአኩም ወደ እርስዋ ገብቶ:- ደስ ይበልሽ፤ጸጋ የሞላብሽ ሆይ፤ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት::» ሉቃ 1:28:: ይህ ልዩ የምስጋና ምስክርነት ስለሆነ ቅድስት ኤልሳቤጥም ይህንኑ ቃል በድጋሚ ተናግራዋለች:- «. . . በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት፤በታላቅ ድበፅም ጮኸ እንዲህ አለች:- አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፤የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው::» ሉቃ 1:42::

ቅድስት ኤልሳቤጥ በድንግል ማርያም ክብር ፊት ራሷን ስትመለከት ታናሽ መሆኗን ስለ ተገነዘበች ነው ይህ ለእርሷ የማይገባ መሆኑን በመግለጽ በትሕትና የተናገረችው:: ምንም እንኳ ኤልሳቤጥ «በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና. . .» እና «. . . በኤልያስ መንፈስና ኃይል በፊቱ ይሄዳል. . .» (ሉቃ 1:15እና17) የሚሉት ቃላት የተነገሩት ለድንግሊቱ ልጅ ለኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ብታውቅም የእናቱንም ክብር እንዲህ በማለት ገልጣለች:- «የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል?» ሉቃ 1:43::

የድንግል ማርያም ታላቅ ክብርና በእግዚአብሔር ፊት ያላት ሞገስ በጣም ግልጽ በሆነ ማስረጃ የተረጋገጠው እርሷ ለኤልሳቤጥ ሰላምታ ባቀረበች ጊዜ ነበር:: ምክንያቱም ኤልሳቤጥ የእመቤታችንን ሰላምታ



www.ethiopianorthodox.org

በሰማች ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ስለሞላባት የስድስት ወር ፅንስ የሆነው መጥምቁ ዮሐንስ በማኅፀኗ ውስጥ በደስታ ስለ ዘለለ ነው።

ወንጌል ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፦

«ኤልሳቤጥም የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ፅንሱ በማኅፀንዋ ውስጥ ዘለለ፤በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት፤. . .» ሉቃ 1:41።

በእርግጥም እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ያቀረበችላት ሰላምታ ኤልሳቤጥን በመንፈስ ቅዱስ እንድትሞላ ማድረጉ ድንቅ ክብሯን ያረጋግጣል። ከቅዱሳን መካከል ሰላምታው ሰዎችን በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ ያደረገው የትኛው ነው? ኤልሳቤጥ ግን ይህን ምስክርነት እንዲህ በማለት ገልጣለች፦ «እነሆ የሰላምታሽ ድምፅ በጆሮዬ በመጣ ጊዜ ፅንሱ በማኅጸኔ በደስታ ዘሎአልና።» ሉቃ 1:44።

ኤልሳቤጥ የድንግል ማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ብቻ ሳይሆን ትንቢት የመናገርና ራእይ የመመልከት ስጦታን ተቀብላለች።

ይህ በመሆኑም ድንግል ማርያም የእግዚአብሔር እናት መሆኗን አውቃለች፤ከጌታ የተነገረላት ቃል ፍጻሜ ማግኘቱንም አምናለች። ከዚህ በተጨማሪ ፅንሱ በማኅጸኗ ውስጥ የዘለለው በደስታ መሆኑንም አረጋግጣለች። ይህን ደስታ ያመጣውም «. . . የማጸንሽም ፍሬ የተባረከ ነው።» (ሉቃ 1:41-45) ተብሎ የተነገረለት የድንግሊቱ የማኅጸን ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

እርሷ በዓለም ውስጥ ከሚገኙት ሴቶች ሁሉ መካከል በእግዚአብሔር ስለ ተመረጠች ክብሯ እጅግ ታላቅና ብሩኅ ነው።

በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ በሺዎች ለሚቆጠሩ ዘመናት የተጠበቀች ብቸኛ የሰው ዘር እርሷ ብቻ ናት። ከተመረጠች በኋላም እጅግ ታላቅ ክብር ይገባት ስለ ነበር መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እንዲህ በማለት አወድሷታል፦ «. . . መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤የልዑል ኃይልም ይጸልልሻል፤ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል።» ሉቃ 1:35።

ድንግል ማርያም በታላቅ ክብሯ ሴቶችን ሁሉ ትበልጣለች።

ይህ በመሆኑም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ እርሷ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፦ «መልካም ያደረጉ ብዙ ሴቶች አሉ፤አንቺ ግን ከሁሉ





ትበልጫለሽ።» ምሳ 31:29። በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ «ብዙ ሴቶች ክብር አግኝተዋል፤ሁሉም ያገኙት ክብር ግን ከአንቺ ክብር አይበልጥም።» ተብሎ የሚዘመረው መዝሙር የተወሰደው ከዚህ ጥቅስ ይመስላል።

ቅድስት ድንግል ከመጀመሪያው አንስቶ በእግዚአብሔር ኀሊና እና ፈቃድ ስትታሰብ የኖረች እናት ናት።

አምላካችን እግዚአብሔር ለቀደሙ ወላጆቻችን በገባላቸው የድኅነት ቃል ኪዳን ውስጥ የሴቲቱ ዘር የእባቡን ራስ እንደሚቀጠቅጥ ገልጦአል። ዘፍ 3:15።

የሴቲቱ የተባለው ለድንግል ማርያም ሲሆን ዘሯ የተባለው ደግሞ በመስቀል ላይ ሆኖ የእባቡን ራስ ለቀጠቀጠው ለአምላካችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

**ምዕራፍ አራት**
**በተአምራት የተከበበ ሕይወት**

በድንግሊቱ ሕይወት ውስጥ ተአምራት መፈጸም የጀመረው ገና ከመወለዷ አስቀድሞ ሲሆን እነዚህ ተአምራት እስከ ዕለተ ዕረፍቷና ከዚያም በኋላ ባሉት ጊዜያት ውስጥ ሳይቋረጡ ቀጥለዋል። ከእነዚህ መካከል፦

1/ እርሷ በተአምር የተወለደችው መካን ከነበሩ ወላጆቿ ሲሆን ይህም በጌታ መልአክ ብሥራት የተከናወነ ነው።

2/ ለእጮኛ የተሰጠችበት መንገድ ተአምራዊ ነው። ምክንያቱም እንዲወስዳትና እንዲጠብቃት የተመረጠው ሰው ምርጫ የተከናወነው በእግዚአብሔር በመሆኑ ነው።

3/ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በድንግልና በጸነሰችው ጊዜና ከወለደችው በኋላም በድንግልና የመቆየቷ ነገር የተከናወነው ድንቅ በሆነ ተአምር ነው።

4/ ዘመዷ ኤልሳቤጥን በጎበኘችት ጊዜ የተፈጸመው ነገር እንዲሁ ተአምራዊ ነው። ኤልሳቤጥ የድንግል ማርያምን የሰላምታ ድምፅ በሰማች ጊዜ በማኅጸኗ ውስጥ ያለው ፅንስ በደስታ ዘሏል፤መንፈስ ቅዱስም በእርሷ ላይ አድሯል።



www.ethiopianorthodox.org

5/ እርሷ ግብጽ ውስጥ በስደት ሳለች ብዛት ያላቸው ተአምራት ተፈጽመዋል:: ከእነዚህም መንከል አንዱ የጣዖታት መፈራረስ ነበር::

6/ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ገሊላ አውራጃ ውስጥ በምትገኘው የቃና መንደር ውስጥ የፈጸመው የመጀመሪያው ተአምር የተከናወነው በድንግል ማርያም አማላጅነት ነው::

7/ የብረቱ መቅለጥ ተአምርና የሐዋርያው የቅዱስ ማትያስ ነጻ መውጣት የተከናወነው በድንግሊቱ አማላጅነት ነው::

8/ በዕረፍቷ ጊዜ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ ነፍሷን መቀበሉ ሌላው ተአምር ነው::

9/ ከዕረፍቷ በኋላ አይሁድ ሥጋዋ ላይ አደጋ ሊያደርሱ በሞከሩ ጊዜ መድኃኔዓለም ክርስቶስ በእነርሱ ላይ ያደረሰው ቅጣት ተአምራዊ ነበር::

10/ የሥጋዋ ወደ ገነት የማረግ ጉዳይም ተአምር ነው::

11/ በመጻሕፍት የተጻፉና በእርሷ እጆች በየቦታው የተፈጸሙ ሌሎች ብዙ ተአምራት አሉ::

12/ በዜይቱን (Zeitoun) እና በፓፓዶፑሎ (Papadopoulo) በሚገኙት አብያተ ክርስቲያኖቻችን ላይና በሌሎች ብዛት ባላቸው ቦታዎች ላይ የመገለጧ ተአምር ድንቅ ነው::

አሁንም ቢሆን ብዛት ያላቸው ተአምራት በየሥፍራው እየተፈጸሙ ናቸው:: ይህ ደግሞ ድንግሊቱ ያላትን ክብር የሚገልጥ ምስክርነት ስለሆነ ወደፊትም ሳይቋረጥ ይቀጥላል::

## ምዕራፍ አምስት
## የድንግሊቱ ጾም

የግብጽ ቤተ ክርስቲያን የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ጾም የምትጾመው ከ (Misra) ወር መጀመሪያ ወይም ነሐሴ 1 (August 7) ጀምሮ ነው:: ይህን ጾም ምዕመናን ሁሉ በጉጉት የሚጠብቁትና ራሳቸውን በምናኔ ሕይወት ውስጥ በማስገባት የሚጾሙት ጾም ነው:: ብዙ ምዕመናን ለእመቤታችን ባላቸው ታላቅ ፍቅር የተነሣ የጾሙን ቀናት በመጨመር ይጾሙታል::





በድንግል ማርያም ጾም (በጾመ ፍልሰታ) ወቅት ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መነቃቃት ታሳያለች:: በዚህ ወቅት በስሟ ያልታነጹ አብያተ ክርስቲያናትም ጭምር ለየት ያለ ዕለታዊ የስብከትና የቅዳሴ መርሐ ግብር ያካሂዳሉ:: በተለይም ሞስቶሮድ (Mostorod) በተባለው ስፍራ ላይ በሚገኘው ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ ታላቅ በዓል ይዘጋጃል::

በፍልሰታ ጾም ውስጥ የሌሎች ቅዱሳን በዓላት አብረው ይገቦራሉ:: ከእነርሱም መንከል:-

ሚት ዳምሲስ (Mit Damsis) ውስጥ በሚገኘው ገዳም ውስጥ የቅዱስ ጊዮርጊስ በዓል በጾሙ ሁለተኛ ሳምንት ውስጥ ይከበራል:: የቅዱስ አባ መቃርስ በዓል በዚሁ ገዳም ውስጥ ሲከበር የቅዱስ ጊዮርጊስ በዓል እንዲሁ ሩዜይንት (Ruzeykat) በሚገኘው በራሱ ገዳም ውስጥ ይከበራል::

ከዚሁ በተመሳሳይ በዚሁ የእመቤታችን ቅድስተ ድንግል ማርያም ጾም ውስጥ የሌሎች የግብጽ ቅዱሳን ሰዎች በዓላት ይከበራሉ:: ከእነርሱም መካከል:- ቅድስት ቤይሳ (ነሐሴ 6/በዋዜማው/) ፣ ቅድስት ጁሊታ (ነሐሴ 12) እና ቅድስት ማሪና (ነሐሴ 21) ይገኛሉ::

ታላቁን የደብረ ታቦር በዓል (ነሐሴ 13) የምናከብረውም በዚሁ የድንግል ማርያም ጾም ውስጥ ነው::

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለእመቤታችን አባት ለኢያቄም (Joachim) የድንግል ማርያምን የልደት ብሥራት ያበሰረውም በዚሁ የጾም ወቅት (Misra/ ነሐሴ 7) ነው::

የድንግል ማርያም በዓላት የሚከበሩት በዚህ የጾም ወቅት ውስጥ ብቻ አይደለም:: ኪሆክ (Kiahk/ታኅሣሥ) በተባለው ወር ውስጥ ሌሎች ታላላቅ በዓላቶቿ ለእርሷ በሚቀርቡ መዝሙራት፣ በቅዳሴና በመጽሐፍ ቅዱስ ንባባት ይከበራሉ::

ግብጽ ውስጥ የሚኖሩ ቅብጣውያን (Copts) በተለይም ሴቶቹ የድንግል ማርያምን ጾም የሚጾሙት ለመግለጽ በሚያዳግት ድንቅ የፍቅር ሥርዓት ውስጥ ሆነው ነው::

ብዙዎቹ ሴቶች ይህን ጾም የሚጾሙት ዘይት ያልገባበት ውኃና ጨው በመጠጣት ብቻ ነው:: ብዙዎቹ እንዲሁ ሦስተኛውን ሳምንት በስእለት ጨምረው ይጾማሉ:: አንዳንዶቹ ደግሞ ከዋክብት በሰማይ ላይ እስኪታዩ (እስኪጨልም) ድረስ ምግብ አይቀምሱም ውኃም አይጠጡም::



www.ethiopianorthodox.org

ለመሆኑ ከዚህ ሁሉ ጥንታቂ በስተጀርባ ያለው ምሥጢር ምንድር ነው?

በመጀመሪያ ደረጃ ቅብጦች ሀገራቸውን ለጎበኘችውና ለባረከችው ለድንግል ማርያም ልዩ ፍቅር ስላላቸውና እርሷ ግብጽ ውስጥ በደረሰችባቸው ሥፍራዎች ሁሉ ላይ አብያተ ክርስቲያናት ስለ ታነጹ ነው።

በሁለተኛ ደረጃ ግብጽ ውስጥ ለሚኖሩ ብዙ ክርስቲያኖች በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ብዛት ያላቸው ተአምራት ስለተደረጉላቸው ይህን ምክንያት በማድረግ በስሟ የተጠሩ አብያተ ክርስቲያናትን ስላሳነጹ ነው።

ድንግል ማርያም ዜይቶን ውስጥ በሚገኘው ቤተ ክርስቲያኗ በተገለጠች ጊዜ ይህን መገለጥ ተከትለው ብዙ ተአምራት ተፈጽመዋል። ይህ ደግሞ ቅብጦች ለእመቤታችን ያላቸውን ፍቅር በእርግጠኝነት እንዲጨምሩና በስሟ የሚጾመውን ጾም አጥብቀው እንዲጾሙ አድርጓቸዋል።

**ምዕራፍ ስድስት**
**በዓላቶቿ**

እያንዳንዱ ቅዱስ ሰው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቢያንስ አንድ በዓል ያለው ሲሆን ይህም ዕለተ ሞቱ ወይም ሰማዕትነት የተቀበለበት ወይም ደግሞ ስባረ አፅሙ የፈለሰበት ወይም በስሙ ተአምር የተፈጸመበት ወይም በስሙ ቤተ ክርስቲያን የታነጸበት ሊሆን ይችላል።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ግን ብዙ ታላላቅ በዓላት አሏት። ከእነርሱም መካከል:-

1/ የልደቷ ብሥራት የታወጀበት በዓል።

ለአባቷ ለኢያቄም የልደቷን ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ያበሠረው Misra (ነሐሴ 1) ቀን ነው። በዚህ ዕለት አባቷ ኢያቄምና እናቷ ሐና እጅግ ስለ ተደሰቱ ስትወለድ ለጌታ ሊሰጧት ስእለት ተሳሉ።

2/ የልደቷ በዓል።

ቤተ ክርስቲያን ይህን በዓል የምታከብረው Bashans (ግንቦት) 1 ቀን ነው።





**3/ ወደ ቤተ መቅደስ የገባችበት በዓል (በአታ ለማርያም)።**

**ቤተ ክርስቲያን ይህን በዓል የምታከብረው Kiahk (ታኅሣሥ) 3 ቀን ነው። እርሷ በዚህ ዕለት ወደ ቤተ መቅደስ የገባችው ለደናግል በተዘጋጀ ልዩ ሥፍራ ውስጥ እግዚአብሔርን ለማምለክ ነው።**

**4/ ወደ ግብጽ ያመጣችበት ቀን በዓል።**

**እርሷ በስደት ወደ ግብጽ የመጣችው ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስና በአናጢነት ሙያ ከሚተዳደረው ከቅዱስ ዮሴፍ ጋር ነው። ቤተ ክርስቲያን ይህን በዓል የምታከብረው Bashans (ግንቦት) 24 ቀን ነው።**

**5/ የዕለተ ዕረፍቷ በዓል።**

**ይህ በዓል የሚከብረው Tubah (ጥር) 21 ቀን ነው። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዕለት የተፈጸሙትን ተአምራት ከማስታወሷም በላይ በዕለቱ ህንድ ውስጥ በመስበክ ላይ የነበረውን ቅዱስ ቶማስንና ኢየሩሳሌም ውስጥ ሥጋዋን አጅበው የነበሩትን ቅዱሳን ሐዋርያትን ጨምራ ታስባቸዋለች።**

**6/ ወርኀዊው የድንግል ማርያም በዓል።**

**ይህ ወርኀዊ በዓል የሚከበረው ወር በገባ በ21ኛው ቀን ነው። ከእነዚህ ቀናት አንደኛው በዓለ ዕረፍቷ የሚታሰብበት Tubah (ጥር) 21 ቀን ነው።**

**7/ ቅድስት ሥጋዋ ወደ ገነት ያረገበት በዓል (በዓለ ዕርገቷ)።**

**የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ይህን በዓል የምታከብረው (Misra 16/** August 22/ **ነሐሴ 16) ቀን ነው። ይህ በዓል ከፍልሰታ ጾም በኋላ ተከትሎ የሚከበር ነው።**

**8/ ብረት የቀለጠበት ተአምር በዓል።**

**በዓሉ የሚከበረው Baouna (ሰኔ) 21 ቀን ነው። በዚህ ዕለት ቅድስት ድንግል ማርያም ሐዋርያው ቅዱስ ማትያስና ከእርሱ ጋር የነበሩ ወንድሞቹ እጆቻቸውና እግሮቻቸው ታስረውበት የነበረውን የብረት ሠንሰለት በአማላጅነቷ በማቅለጥ ከእስር ቤት ያስወጣችበት ተአምር ይታሰባል።**



www.ethiopianorthodox.org

*9/ ዜይቶን ውስጥ የተገለጠችበት በዓል::*

በስሟ በተሰየመው ቤተ ክርስቲያኗ ጉልላቶች ላይ የተገለጠችው (2 April 1968/ **Baramhat 24/** *መጋቢት* 24) ቀን ነው:: ከዚህ በኋላ በዓሉ እስከ አሁን ድረስ እየተከበረ ነው::

ከእነዚህ ሁሉ በዓላት በተጨማሪ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ክብር ብቻ የሚያወድሱ መዝሙራት ከኅዳር 21 እስከ ታኅሣሥ 28 ድረስ በዜማ ይዘመራሉ::

*ምዕራፍ ሰባት*
**ድንግል ማርያም በቤተ ክርስቲያን እምነት ውስጥ**

ኦርቶዶክሳዊት የቅብጥ ቤተ ክርስቲያን የቅድስት ድንግል ማርያምን ክብር አታጋንንም ማዕረጓንም አትቀንስም::
1/ እንደ ኦርቶዶክሳዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እምነት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የእግዚአብሔር እናት ናት:: ንስጥሮሳውያን ድንግል ማርያምን «የሰው እናት እንጂ የአምላክ እናት አይደለችም» ብለው በካዱ ጊዜ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ቄርሎስ በኤፌሶን ጉባኤ ላይ ከተቃወማቸው በኋላ በውግዘት ተለይተዋል::

**2/ ቤተ ክርስቲያን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በእግዚአብሔር ኅሊና ስትታሰብ ስለ ቆየች ኢየሱስ ክርስቶስን የፀነሰችው በቅድስና እና በንጽሕና ነው::**

***መጽሐፍ ቅዱስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል:- «. . . መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤የልዑል ኃይልም ይጸልልሻል፤ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል::» ሉቃ 1:35::***

*እርሷ ከአዳም ኃጢአት ተጠብቃ የኖረች የክርስቶስ እናት ናት:: መንፈስ ቅዱስ ወደ እርሷ የመጣው ያለ ተከፍሎ ሥጋን ከመለኮት፤ መለኮትንም ከሥጋ ለማዋሀድ ነው:: ይህ ስለ ሆነላትም ድንግል ማርያም በጸሎቷ «ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፤መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች፤የባሪያውን ትሕትና ተመልክቶአልና::» (ሉቃ 1:47) ብላለች::*

**3/ ቤተ ክርስቲያን በድንግል ማርያም አማላጅነት ታምናለች::**





እርሷ የእግዚአብሔር እናትና ከንጉሡ በስተ ቀኝ የምትቆም ንግሥት ስለ ሆነች አማላጅነቷ የሚቀርበው ከመላእክትና ከሊቃነ መላእክት አማላጅነት በፊት ነው::

4/ መጽሐፍ ቅዱስ ለድንግሊቱ «ጸጋ የሞላብሽ ሆይ» የሚል ቅጽል ስያሜ ሰጥቶአታል::

ሰዎች ሁሉ ሊባረኩ ይችላሉ:: ሰዎች ሁሉ ግን በጸጋ ሊሞሉ አይችሉም:: እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የተሞላች ናት::

5/ ቤተ ክርስቲያን በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዘላለማዊ ድንግልና ታምናለች::

ይህን የማያምኑት የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ድንግል ማርያም ክርስቶስን ከወለደች በኋላ ሌሎች ልጆችንም ወልዳለች ብለው ስለሚናገሩ በዚህ እምነታቸው ከክርስትና እምነት አመለካከት ውጪ ሆነዋል::
6/ የቅድስት ድንግል ማርያም ቅዱስ ሥጋ ወደ ገነት ማረጉን ቤተ ክርስቲያን ታምናለች:: ይህንንም በዓል ነሐሴ 16 **Misra** (ነሐሴ) 16 ቀን ታከብራለች::

*ምዕራፍ ስምንት*
**የቅድስት ድንግል ማርያም የክብር ስሞችና ምሳሌዎች**

1/ ታላቅነቷንና ከእግዚአብሔር ጋር ያላትን ዝምድና የሚያሳዩ የክብር ስሞቿ::

ሀ- ከንጉሡ በስተቀኝ የምትቆም ንግሥት በሚለው የክብር ስሟ እንጠራታለን::

እዚህ ላይ የምንጠቅሰው የቅዱስ ዳዊትን የመዝሙር ቃላት ነው:- «በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋፍና፤ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች::» መዝ 44:9:: ይህ ስለሆነ ነው በሥዕሎቿ ላይ ከጌታችንና ከመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስተቀኝ የምትሣለው:: በቅዳሴያችንም ላይ «የሁላችንም እመቤትና ንግሥት» ብለን እንጠራታለን::

ለ- «እናታችን ቅድስት ድንግል» ብለን እንጠራታለን::



www.ethiopianorthodox.org

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ ለሚወደው ሐዋርያው ለቅዱስ ዮሐንስ «እናትህ እነኋት. . .» (ዮሐ 19:27) በማለት በእርሱ በኩል ስለ ተሰጠችን በዚህ ቅጽል ስም እንጠራታለን::

ሐ- ድንግል ማርያም በያዕቆብ መሰላል ትመሰላለች::

«እነሆም መሰላል በምድር ላይ ተተክሎ፤ራሱም ወደ ሰማይ ደርሶ፤. . .» (ዘፍ 28:12) ተብሎ በተጻፈው ጽሕፈት ውስጥ «መሰላል» ተብሎ የተጠቀሰው ቃል የእመቤታችን ምሳሌ ነው:: እርሷ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ስለ ወለደች የምድር ነዋሪዎች ወደ ሰማይ እንዲወጣጡ የሕይወት መሰላል ሆናለች::

መ- እርሷ የእውነተኛው አምላክ ሙሽራ ስለ ሆነች «ሙሽራ» በሚለው የክብር ስሟ እንጠራታለን::

በመዝሙር ያለው ይህ የእግዚአብሔር ቃል የተጠቀሰው ለእርሷ ነው:- «ልጄ ሆይ፤ስሚ እዩ ጆሮሽንም አዘንብይ፤ወገንሽን ያባትሽንም ቤት እርሺ፤ንጉሥ ውበትሽን ወዶአልና፤እርሱ ጌታሽ ነውና::» መዝ 44:10 እና 11:: ድንግል ማርያም መዝሙሩ ከመዝሙራት ሁሉ የሚበልጥ መዝሙር ተብሎ የተጠራለት የሰሎሞን ዘመድ የተባለችው ለዚህ ነው::

ከዚህ በተጨማሪ በዚሁ የዳዊት መዝሙር ውስጥ ስለ እርሷ እንዲህ ተብሎ የተጻፈ ቃል አለ:- «ለሐሴቦን ንጉሥ ልጅ ሁሉ ክብርዋ ነው፤ልብስዋ የወርቅ መጎናጸፊያ ነው::» 44:13እና14::

ሠ- «ውብ ርግብ» የሚልም የክብር ስም አላት::

ይህን ቅጽል ስም የሰጠናት ለአባታችን ኖኅ የሰላም ምልክት የሆነውን የወይራ ዛፍ ዝንጣፊ ያመጣችለትን ውብ ርግብ በማስታወስ ነው:: ርግቢቱ በዚህ የምሥራች ዜናዋ የጥፋት ውኃ በምድር ላይ ጎድሎ መጥፋቱን አብስራለታለች:: ዘፍ 8:11:: በዚህ የክብር ስሟ ካህኑ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚገኝ ስዕሏ ፊት ዕጣን ሲያጥን «ውብ ርግብ የሆንሽው ድንግል ሆይ፤ሰላምታ ይገባሻል» ይላል::

ድንግል ማርያም በዚህች ርግብ የተመሰለችው በየዋህነቷ፣ በንጽሕናዋና የመንፈስ ቅዱስ አሠራር ከእርስዋ ጋር በመሆኑ ነው:: ከጥፋት ውኃ በኋላ መልካሙን የምሥራች ዜና ይዛ በመጣችው ርግብ የምትመሰለው እርሷም በክርስቶስ የሆነ የድኅነታችንን ዜና ይዛልን ስለ መጣች ነው::





ረ- ድንግል ማርያም በሰማይ ደመና ትመሰላለች::

ከፍ ያለ ግርማ ያላት መሆኗና ከልጅዋ ጋር ወደ ግብጽ የመምጣቷ ትንቢት እዚህ ላይ የሚነጻጸር ምሳሌ ነው:: ይህ ምሳሌ የተጠቀሰው በኢሳይያስ የትንቢት መጽሐፍ ውስጥ ነው:-

«ስለ ግብጽ የተነገረ ሸክም:: እነሆ እግዚአብሔር በፈጣን ደመና እየበረረ ወደ ግብጽ ይመጣል፤የግብጽም ጣዖታት በፊቱ ይርዳሉ፤የግብጽም ልብ በውስጧ ይቀልጣል::» ኢሳ 19:1::

በዚህ ጥቅስ ውስጥ «ደመና» የሚለው ቃል በሰማያት ደመና ተጭኖ የሚመጣው የኢየሱስ ክርስቶስም ምሳሌ ነው:: ማቴ 24:27::

2/ የክብር ስሞቿና ምሳሌዎቿ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ያላትን እናትነት የሚያመላክቱ ናቸው::

ሰ- ድንግል ማርያም ከተጠራችባቸው ክቡር ስሞች መካከል «የእግዚአብሔር እናት» የሚለው አንዱ ነው:: ይህ የክብር ስም እ.አ.አ. በ431 ዓ.ም. በይፋ የጸናው በተቀደሰው የኤፌሶን ጉባኤ ላይ ነው:: ታላቁ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ቄርሎስ ለንስጥሮስ በሰጠው መልስ ላይ ይህን ስሟን በገሃድ ተጠቅሞበታል::

ቅድስት ኤልሳቤጥ ድንግሊቱ ማርያምን በዚህ የክብር ስም ጠርታታለች:- «የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንደ ምን ይሆንልኛል?» ሉቃ 1:43::

ሸ- ሌላው ቅጽል ስሟ «የወርቅ ጥና» የሚል ነው::

ቅብጣውያን ጥናን (የዕጣን ማጨሻን) በቋንቋቸው የሚጠሩት ቴ ሹሪ (Te shury) ብለው ነው:: አንዳንድ ጊዜ ደግሞ «የአሮን ጥና» ብለው ይጠሩታል::

በእርሷ ማኅፀን ያደረው እሳት ምሳሌነቱ የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት ሲያመለክት ፍሙ ደግሞ ሰው መሆኑን ያመለክታል:: አምላካችን እግዚአብሔር እሳት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ሲገልጽ «. . . አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነውና::» (ዕብ 12:29) ብሏል::

ጥናው ሰውና መለኮት የተዋሀደበት የድንግል ማርያም ማኅፀን ነው:: ጥናው የወርቅ መሆኑ ደግሞ የእርሷን ንጽሕና፣ ክብርና ታላቅነት ያመለክታል:: የድንግል ማርያምን ንጽሕና እና ቅድስና በተመለከተም



www.ethiopianorthodox.org

ለእርሷ በምናቀርበው መዝሙር ውስጥ «የወርቅ ጥና» ብለን እንጠራታለን፡፡ በቅብጥ ቋንቋ የወርቅ ጥና የሚጠራው «ቴ ሹሪ ኤነብ» (Te shury ennub) ተብሎ ነው፡፡

ቀ- ድንግል ማርያም በክብር ስሟ «ሁለተኛ ሰማይ» ተብላ ተጠርታለች፡፡

ሰማይ የእግዚአብሔር ማደሪያ እንደ ሆነ ሁሉ ድንግል ማርያምም የእግዚአብሔር ማደሪያ ሆናለች፡፡

በ- ድንግሊቱ «የእግዚአብሔር ከተማ» ተብላ ተሰይማለች፡፡

በዳዊት መዝሙር የተጠቀሰው የትንቢት ቃል የተነገረው ለእርሷ ነው፡- «የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ፤በአንቺ የተከበረ ነገር ይባላል፡፡» መዝ 86:3፡፡

ከዚህ በተጨማሪ «የታላቁ ንጉሥ ከተማ» እና ሌሎች በሰማቸው ለኢየሩሳሌም በወርቃቸው ወይም በምሳሌያቸው ደግሞ ለድንግል ማርያም የተነገሩ ቃላት አሉ፡፡ ከዚህ በተመሳሳይ «ጽዮን» የሚለው ስም ምሳሌነቱ የድንግል ማርያም ነው፡- «ሰው እናታችን ጽዮን ይላል፤በውስጧም ሰው ተወለደ፤እርሱ ራሱም ልዑል መሠረታት፡፡» መዝ 86:5፡፡

ተ- በፊደል «ቀ» ከተጠቀሰው በተመሳሳይ ቅድስት ድንግል ማርያም «ሕይወት የሚያድለውን ያፈራች የወይን ተክል» ተብላ ተሰይማለች፤እርሱም ክርስቶስ ነው፡፡

**ቤተ ክርስቲያን በሦስት ሰዓት ጸሎቷ ውስጥ እርሷን በክብር ስሟ እንዲህ እያለች ትጠራታለች፡- «የእግዚአብሔር እናት ሆይ፤አንቺ ሕይወት የሚያፈራውን እውነተኛ ወይን ያቀፍሽ ነሽ፡፡»**

**ቸ- እናትነቷን የሚያጎሉ ሌሎች ተመሳሳይ ምሳሌዎችም አሏት፡-**

**† ስለ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ለሰው ሁሉ የሚያበረው እውነተኛው ብርሃን ወደ ዓለም ይመጣ ነበር፡፡» (ዮሐ 1:9) ተብሎ ስለ ተጻፈ እናቱ ድንግል ማርያም በክብር ስሟ «የእውነተኛው ብርሃን እናት» ተብላ ተጠርታለች፡፡**

**† ብርሃኑን እግዚአብሔር ስለ ያዘች በክብር ስሟ «የወርቅ መቅረዝ» ተብላ ተጠርታለች፡፡**



ቅድስት ድንግል ማርያም

† መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከእርሷ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ሲያበሥራት «. . . ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል፡፡» (ሉቃ 1:35) ስላላት «የቅዱሱ እናት» ተብላ ተጠርታለች፡፡

† መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ሁሉ አዳኝ ስለሆነ «የአዳኙ እናት» ተብላ ተጠርታለች፡፡ «እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ፡፡» ማቴ 1:21፡፡

ኀ- ከምሳሌዎቿ አንዱ «ሙሴ ያየት ቁጥቋጦ» ወይም «የሲና ሐመልማል» የሚለው ነው፡፡ ዘጸ 3:2፡፡

ምስጋና ይድረሳትና ነቢዩ ሙሴ በበረሀ የተመለከተው ቁጥቁጦ የብርሃን እናት የሆነችው የድንግል ማርያም ምሳሌ ነው፡፡ አምላካችን የሚያጠፋ እሳት ቢሆንም (ዕብ 12:29) በመዝሙራችን «እርሷ ምንም ዓይነት ጉዳት ሳይደርስባት እሳት መለኮትን በማኅጸኗ ይዛለች፡፡» እያልን እንዘምራለን፡፡ በቁጥቋጦው ውስጥ የሚነደው እሳት የመለኮት ምሳሌ ሲሆን ያልተቃጠለው ቁጥቋጦ ደግሞ የድንግል ማርያም ምሳሌ ነው፡፡

ነ- ከምሳሌዎቿ አንዱ «የቃል ኪዳኑ ታቦት» መሆኗ ነው፡፡

ከግራር እንጨት የተቀረጸው የቃል ኪዳኑ ታቦት ብል የማይበላው ከመሆኑም በላይ ከውስጥም ሆነ ከውጪ በወርቅ ተለብጧል፡፡ ዘጸ 25:10እና22፡፡ ይህ ምሳሌነቱ የሚያመለክተው የቅድስት ድንግል ማርያምን ታላቅነትና ንጽሕና ነው፡፡ በታቦቱ ውስጥ ያሉት ነዋየ ቅዱሳት የአምላካችን የክርስቶስ ምሳሌ ናቸው፡፡

በታቦቱ ውስጥ ያሉት፡- መናውን የሚይዘው የወርቅ ማሰሮ፤ የለመለመችው የአሮን በትርና ጽላቶቹ ናቸው፡፡ ይህ ምሳሌነቱ ሥጋ ለለበሰው የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡

ኘ- የማሰሮው መና ለድንግል ማርያም በምሳሌነቱ ይነጻጸራል፡፡

መናው የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው፤እርሱ ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ ነውና፡፡ ከእርሱ የሚበላ ሁሉ የዘላለም ሕይወት አለው፡፡ ይህ በመሆኑም የሕይወት እንጀራ ተብሎ ተጠርቷል፡፡ ዮሐ 6:32ነ48እና49፡፡ መናው የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ከሆነ ድንግል ማርያምም በምሳሌ ከቀረበው የማሰሮ መና ጋር ትነጻጸራለች፤እርሷ ይህን ሰማያዊ መና በማኅጸኗ ይዛለችና፡፡



www.ethiopianorthodox.org

ለ- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በለመለመችው በአሮን በትር ትመሰላለች።

ምንም እንኳ ይህች የአሮን በትር ሕይወት ባይኖራትም ድንቅ በሆነ የእግዚአብሔር ተአምር ለምልማ አድራለች ፍሬም አፍርታለች። ዘኁ 17:8። ድንግል ማርያምም ያለ ወንድ ዘር መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በተአምር በድንግልና ጸንሳ ወልዳለች። ይህ በመሆኑም በለመለመችው በአሮን በትር ተመስላለች።

ከ- ድንግል ማርያም በመገናኛው ድንኳን ትመሰላለች።

እግዚአብሔር አምላክ በመገናኛው ድንኳን ይገለጥ እንደ ነበር ኢየሱስ ክርስቶስም በድንግል ማርያም ተገልጦአል። እግዚአብሔር ፍቅሩን ለሕዝቡ በሁለት መንገድ ገልጦአል። ይህ በመሆኑም በጸሎት መጽሐፋችን ውስጥ እንዲህ እያልን እንጸልያለን:- «ድንግል ማርያም ሆይ፤አንቺ በምሳሌ የምትነጻጸሪው ሙሴ በሲና ተራራ ላይ ካዘጋጀውና እግዚአብሔር ካደረበት ጽላት ጋር ነው።»

ኸ- ቅድስት ድንግል ማርያም በምሥራቅ ደጅ ትመሰላለች።

ነቢዩ ሕዝቅኤል ስለ ተመለከተው የተዘጋ የምሥራቅ ደጅ እግዚአብሔር የተናገረው እንዲህ በማለት ነው:- «ወደ ምሥራቅም ወደሚመለከተው በስተ ውጭ ወዳለው ወደ መቅደሱ በር አመጣኝ፤ ተዘግቶም ነበር። እግዚአብሔርም ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፤ሰውም አይገባበትም፤የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል።» ሕዝ 44:1-2። ነቢዩ በስተምሥራቅ አቅጣጫ ያለው በር በእግዚአብሔር ክብር የተሞላ መሆኑን ተመልክቷል። ሕዝ 44:2፣4እና5።

በስተምሥራቅ አቅጣጫ ያለው ይህ በር የተዘጋና ማንም የማይገባበት መሆኑ በምሳሌነቱ የሚያመለክተን የድንግል ማርያምን ዘላለማዊ ድንግልና ነው። እርሷ የምሥራቅ ደጅ ስለ ሆነች የሕይወት በር ተብላ ተጠርታለች።

ወ- ድንግል ማርያም የሕይወት በርና ነጻ የመውጫ በር ናት።

በነቢዩ ሕዝቅኤል የትንቢት መጽሐፍ ውስጥ ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እንዲህ ተብሎ የተጻፈ ቃል አለ:- «አለቃው ግን እርሱ በእግዚአብሔር ፊት እንጀራ ይበላ ዘንድ ዘንድ ይቀመጥበታል፤በበሩ ደጅ ሰላም መንገድ ይገባል፤በዚያም መንገድ ይወጣል።» ሕዝ 44:3።





መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ስለሆነ እርሷ ደግሞ የሕይወት በር ናት። ኢየሱስ ክርስቶስ «ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤. . .» (ዮሐ 11:25) ብሏል። እመቤታችን የሕይወት በር የተባለችው ለዚህ ነው፤በእርሷ ያደረውና የተወለደው (የገባውና የወጣው) አምላክ በእርሱ ለሚያምኑት ሕይወትን ያድላቸዋልና።

ዐ- ድንግል ማርያም ቅድስተ ቅዱሳን በሚለው የክብር ስም ትጠራለች።

**ምዕራፍ ዘጠኝ**
**የድንግል ማርያም የቅድስና ጠባያት**

❖ **የትሕትና ሕይወት።**

የክብር አምላክ ለሚወለድባት ድንግል ትሕትና ወሳኝ ጉዳይ ነበር።

ኢየሱስ ክርስቶስ ትሑት ከሆነች ሰው መወለዱ አስፈላጊ ጉዳይ ነበር። እርሷ ትሑት ስለ ሆነች ክርስቶስ መለኮታዊውን ሥጋ ከእርሷ በክብር ነሥቷል፤ትሑት ስለ ሆነች የመንፈስ ቅዱስ ክብር በእርሷ ላይ አድሯል፤ትሑት ስለ ሆነች ክቡር ኢየሱስ ክርስቶስ ከእርሷ ተወልዷል፤ ትሑት ስለ ሆነች ትውልድ ሁሉ እርሷን በክብር ያመሰግናታል፤ትሑት ስለ ሆነች ኤልሳቤጥ ትሕትናን ተጎናጽፋ «የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል?» (ሉቃ 1:43) ብላለች።

ከዚህ በተጨማሪ ትሑት ስለ ሆነች በክብር የተሞላ የመላእክት ውዳሴ ለእርሷ ቀርቧል፤ሰብዓ ሰገል ለልጇ ለኢየሱስ ክርስቶስ አምልኮት አቅርበዋል፤ብዛት ያላቸው ተአምራት ግብጽ ውስጥ በልጇ አማካይነት ተፈጽመዋል፤ብርሃን የሆነ ልጇም ብርሃኑን በማኅጸኗ ውስጥ አብርቷል።

«የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ. . .» (ገላ 4:4) ተብሎ የተነገረው ቃል የእግዚአብሔር ልጅ የሚወለድባትን ድንግል ለዘመናት የጠበቀው ለዚህ ነው።

ትሕትና በድንግሊቱ ሕይወት ውስጥ ተገልጦአል።

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል የእግዚአብሔር እናት እንደምትሆን ሲያበሥራት «እነሆኝ የጌታ ባሪያ. . .» (ሉቃ 1:38) በማለት ነው የብሥራቱን ዜና በትሕትና የተቀበለችው። እርሷ ይህን ያለችው በእርግጥም እናቱም አገልጋዩም ስለ ሆነች ነው።



www.ethiopianorthodox.org

ለእርሷ የተሰጣትን ድንቅ የሆነ ክብር ትሕትናዋ ፈጽሞ አልቀነሰውም፡፡ ይልቁንም ትሕትና ስላላት ነው እግዚአብሔር ይህን ክብር ያደላት፡፡ «የባሪያውን ትሕትና ተመልክቶአልና፡፡ . . . ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጎአልና፤. . .» ሉቃ 1:48-49፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ድንቅ ትሕትና የተገለጠው ኢየሱስ ክርስቶስን ከፀነሰች በኋላ ኤልሳቤጥን ለመጠየቅና ለማገልገል ወደ እርሷ በሄደች ጊዜ ነው፡፡ ጌታን መፅነሷን ከሰማች በኋላ ነው ወዲያውኑ ኤልሳቤጥን ለማገልገል አድካሚ ወደ ሆነው ወደ ተራራማው አገር ወደ ይሁዳ የወጣችው፡፡ ከዚህ በኋላ ኤልሳቤጥ እስክትወልድ ድረስ ለሦስት ወራት ያህል በዚያ ተቀምጣለች፡፡ ሉቃ 1:39-56፡፡

እናታችን ይህን ያደረገችው እርሷ ጌታን ባረገዘችባቸው የመጀመሪያ ሦስት ወራት ውስጥ ነው፡፡ ክርስቶስ ከእርሷ ሥጋና ደም የነሣበትን በክብር የተሞላ የሥጋዌ ምሥጢር ለማንም አለመናገሯ ደግሞ ሌላው ድንቅ የትሕትናዋ መገለጫ ነው፡፡

❖ የመታዘዝና የአርምሞ ሕይወት፡፡

ቅድስት ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ ውስጥ የኖረችው በቅድስና እና በንጽሕና ነው፡፡ ሰዎች ግን ከቤተ መቅደስ እንድትወጣ ጠይቀው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ጥያቄ ሲቀርብ ሌሎች ሴቶች ወደ ቤተ መቅደስ መግባት በማይችሉባቸው ቀናት እንኳ መግባት እንደሌለባቸው ሲነገራቸው አጥብቀው እንደሚገቱትና ብዙ ረብ የሌለው ወሬ እንደሚናገሩት እርሷ ማንንም አልተቃወመችም ከማንም ጋርም አልተጣላችም፡፡

እርሷ በትዳር የመኖር ፍላጎት ስላልነበራት በወቅቱ በነበረው ልማድ መሠረት በአንድ ሰው ጠባቂነት ሥር እንድትኖር ተደርጎ ነበር፡፡

ከቤተ መቅደስ እንድትወጣ በተጠየቀ ጊዜ እንዳልተቃወመች ሁሉ በአንድ ሰው ጠባቂነት ሥር እንድትኖር በተነገራት ጊዜም አንዳችም የተቃውሞ አሳብ አላቀረበችም፡፡

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የኖረችው ማንንም ሳትቃወም፣ በማንም ላይ ሳታጉረመርምና በሰው ሁሉ ላይ ሳታንጎራጉር ከእግዚአብሔር ፈቃድ በታች ባለ የጸጥታ ታዛዥነት ውስጥ ነበር፡፡ በድንግልና ሕይወት ለመኖር ወስና ስለ ነበር በማንኛውም ጊዜ ውስጥ ለአፍታ እንኳ እናት ሆና የመኖር አሳብ በኅሊናዋ ውስጥ አልነበረም፡፡





በመንፈስ ቅዱስ አሠራር በድንግልና እናት እንድትሆን እግዚአብሔር ሲፈቅድ (ሉቃ 1:35) ሰፊ የውይይት አጀንዳ እንዲከፈት አልፈቀደችም፤ ይልቁንም ባልተቀየረ ቃሏ እንዲህ አለች እንጂ:- «እነሆኝ የጌታ ባሪያ፤ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ. . .» ሉቃ 1:38፡፡ ይህን በማለቷም እግዚአብሔር እስከ መጨረሻ ድረስ በድንግልና እንድትኖር አሳቧን አጸናላት እናትነትቷንም አጸደቀላት፡፡ ከዚህ በኋላ ፈጽሞ አስባው በማታውቀው መንገድ እናት ሆነች፡፡ በመታዘዟም የእግዚአብሔር እናት ሆነች፡፡ ይህ ደግሞ ለማንኛዋም እናት ያልተሰጠ የእናትነት ክብር ነው፡፡

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በመልአኩ አማካይነት ወደ ግብጽ እንድትወርድ በታዘዘች ጊዜም ከዝምታዋ ጋር ነው የወረደችው፡፡ ከግብጽ ወደ ቅድስት ሀገር እንድትመለስ ይኸው ተመሳሳይ ትእዛዝ ሲደርሳት ትእዛዙን በዝምታ ነው የፈጸመችው፡፡ ከቤተልሔም ወጥታ ወደ ናዝሬት በመሄድ በዚያ እንድትኖር በታዘዘች ጊዜም ከፍጹም ጸጥታዋ ጋር ነው የሄደችው፤እርሷ እነዚህ ሁሉ ትእዛዛት ከእግዚአብሔር የመጡ መሆናቸውን አውቃለችና፡፡

እናታችን ያለ ምንም ውይይት በመታዘዝ ሕይወት ውስጥ በእርጋታ ያለፈች የሰው ዘር ናት፡፡ ይህ ስለሆነ ነው እርሷ «. . . የባሪያውን ትሕትና ተመልክቶአልና . . . ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጓልና፤» (ሉቃ 1:49) በማለት የተናገረችው፡፡

**የጽናት ሕይወት፡፡**

እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ወላጆቿ በሞት የተለዩአት ገና የስምንት ዓመት ብላቴና ሳለች ስለሆነ ያደገችው ያለ ወላጅ ነው፡፡ ይህ በመሆኑም ያለ ወላጅ የማደግን ችግር በጽናት ተቋቁማለች፡፡ በቤተ መቅደስ መኖር የጀመረችውም ገና በሕፃንነት ዕድሜዋ ስለ ነበር ብቸኝነትንም ተጋፍጣለች፡፡ በአንድ ጠባቂ ሰው ጥላ ሥር ለማደግ ከቤተ መቅደስ ከወጣች በኋላም የድህነትን ሕይወት ተቋቁማለች፡፡ «በዚያም ሳሉ የመውለጃዋ ወራት ደረሰ፤የበኵር ልጅዋንም ወለደች፤በመጠቅለያም ጠቀለለችው፤በእንግዶችም ማደሪያ ሥፍራ ስላልነበራቸው በግርግም አስተኛቸው፡፡» (ሉቃ 2:7) ተብሎ ስለ ተጻፈ ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው አንድ ልጇን ከወለደች በኋላም መከራን በጽናት ተቀብላለች፡፡ በጠባቂዋ በቅዱስ ዮሴፍ ጠባቂነት ሥር ሳለችም የኃላፊነትን ቀንበር ተሸክማለች፡፡ እርሷ በዙሪያዋ እንደ ደመና የከበባትን ድንቅ ክብር በታላቅነት አሳብ በመሰናከል አላጣችውም፤እንዲህ ያለውን ስሕተት ሳለመፈጸምም ጽኑ ነበረችና፡፡



www.ethiopianorthodox.org

እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና የመውለዷን ዜና በይፋ ከማወጅ ይልቅ በጽናት አርምሞን የመከተል ሕይወትን መርጣለች።

ድንግል ማርያም ገና ብላቴና ሳለች የግብጽን የደርሶ መልስ አድካሚ ጉዞ በጽናት ተወጥታለች። በዚያ ከልጇ ጋር ለሦስት ዓመት ተኩል በስደት ስትቀመጥ የግብጽ ጣዖታት በልጇ ፊት እየተሰባበሩ ይወድቁ ስለ ነበርና (ኢሳ 1:9) ጣዖት አምላኪዎች ከአንዱ ከተማ ወደ ሌላው ከተማ ያሳድዷቸው ስለ ነበር ይህንንም መከራ በጽናት ተቋቁማለች። ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ በልጇ ላይ የወረደውን ስድብ፣ እንግልት፣ ግርፋትና ሕማማት መስቀል እየተመለከተች ከመሪር እንባ ጋር በጽናት ቆይታለች።

ድንግሊቱን እነዚህ ሁሉ መከራዎች ቢገጥሟትም በልጇ የሚሆን ደስታዋን ስላላጣችው በምስጋና ጸሎቷ ውስጥ እንዲህ ብላለች:- «. . . መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች፤» ሉቃ 1:47።

**የእምነትና ያለማጉረምረም ሕይወት።**

እርሷ ስለ ተቀበለቻቸው መከራዎች አንድ ጊዜ እንኳ አላጉረመረመችም። ሄሮድስ ልጇን ለመግደል አውሬ ሆኖ ሲነሣበትነ ይዛው ወደ ግብጽ ስትሰደድና አይሁድ ያን ሁሉ መከራና ሥቃይ ሲያደርሱበት ስትመለከት 'በአባቱ በዳዊት ዙፋን ላይ ይነግሣል፤ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም ተብሎ የተጻፈው ቃል ወዴት ደረሰ?' ብላ አልተናገረችም። ሉቃ 1:32-33። ዘመዷ ኤልሳቤጥ «ከጌታ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብፅዕት ናት።» (ሉቃ 1:35) ብላ ስለ እርስዋ ምስክርነት ስታቀርብላትም በትዕግሥት ጸንታ ቆየች እንጂ አንዲትም ቃል አልተናገረችም።

እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስን በድንግልና እንደምትወልደው ፍጹም አምናለች፤ይህም ተከናውኖላታል።

ምንም እንኳ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ በከብቶች በረት ቢወለድም ስለ እርሱ «. .. . ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል።» (ሉቃ 1:35) ተብሎ በተነገራት የምሥራች ቃል አምናለች። አስቀድማ በእምነት የተቀበለችው ሁሉ ተከናውኖላታል። ይህ የተከናወነላትም በራእይ፣ በተመለከተቻቸው መላእክትና ልጇ በፈጸማቸው ተአምራት ውስጥ ነው። ከዚህ በተጨማሪ እርሱን ሕመማት መስቀል እንደሚገጥመው አምናለች።





በመስቀል ተሰቅሎ እንደሚሞትና ሞትን ድል አድርጎ እንደሚነሣ ስላመነች ይህን በዓይኗ ተመልክታለች። ማቴ 28።

**ዝምታ፣ ጸሎትና ተመስጦ።**

ወላጆቿን በሕፃንነቷ እንድታጣና በቤተ መቅደስ እንድታደግ ሁሉንም ነገር ያሰናዳው እግዚአብሔር ነው።

እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ ውስጥ ስላደገች የብቸኝነትን፣ የዝምታንና በጸሎትና በተመስጦ ራሷን ባተሌ የማድረግን ሕይወትን በዚያ ሳለች ተምራለች። እርሷ የወላጆቿን ፍቅርና እንክብንቤ ብታጣም ፍቅሯን ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር ብቻ በማድረግ አድጋለች።

ድንግል ማርያም ብቸኝነትን ከጸሎት፣ ከዜማ፣ ከመዝሙራት፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከማንበብ፣ ያነበበቻቸውን ጥቅሶች በተለይም መዝሙረ ዳዊትን በተመስጦ ውስጥ ሆና በቃሏ በመወጣት ሙሉ ጊዜዋን በዚያ ታሳልፍ ነበር።

ዝምታ ወይም ፀጥታ ከመንፈሳዊ ጠባያቶቿ መካከል አንዱ ነው።

እርሷ ቅዱስ ልጇን በወለደችው ጊዜ ገና ታናሽ ብላቴና ብትሆንም ከዕድሜዋ ጋር ሲነጻጸሩ ከኀሊና በላይ በሆኑ ድንቅ ተአምራት ተከባ ነበር። እርስዋ የመላእክትን፣ የእረኞችንና ከሩቅ ምሥራቅ የመጡ የጥበብ ሰዎችን (ሰብዓ ሰገል) ድንቅ ቃላት አድምጣለች። ይህ ይሁንላት እንጂ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስን ስትወልድ ስለ ተመለከተቻቸው ድንቅ ነገሮች በኩራት አልተናገረችም። ስለዚህ ጉዳይ አስመልክቶ በወንጌል የተጻፈው ቃል እንዲህ የሚል ነው:- «. . . ማርያም ግን ይህን ነገር ሁሉ በልብዋ እያሰበች ትጠብቀው ነበር።» ሉቃ 2:19እና52።

በእናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዘንድ ያለው ዝምታ ለእኛ ትምህርት ሰጪ ነው። እናም እባካችሁ፤እርሰዋን ጥቂት በመናገርና ብዙ በተመስጦ ውስጥ በመቆየት እንምሰላት።

ይህ ይሁን እንጂ እናታችን መናገር በሚገባት ጊዜ ስትናገር የተናገረቻችው ንግግሮቿ ለትውፊታዊ ስብከት ምንጮች ነበሩ። ሐዋርያትና ወንጌላውያን ባቀረቧቸው ዜናዎቻቸው ላይ ከእርሷ ብዙ እንደ ተማሩ ገልጠዋል። ከልጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በስደት ወደ ግብጽ በወረደች ጊዜ በተናገረችው ቃል ውስጥና ልጇ ገና ብላቴና ሳለ (በ12 ዓመቱ) በቤተ መቅደስ ውስጥ ተገኝቶ ከሊቃውንትና ከመምህራን ጋር ባደረገው ውይይት ውስጥ የንግግር ድርሻ ነበራት ብዬ አምናለሁ።



www.ethiopianorthodox.org

**ሌሎች የቅድስና ጠባዮቿ::**

እግዚአብሔር ወላጆቿን በሕፃንነት ዕድሜዋ ያጣችውን ድሀ ድንግል እናት አድርጎ የመረጠው በሕልውናዋ ከሴቶች ሁሉ የምትልቅ እናት ሊያደርጋት ስለ ወደደ ነው:: እርሷ በጠባዮቿ ከገንዘብ ብልጽግና የሚልቁ ልዩ ጠባያት አሏት::

ቅድስና፣ ንጽሕና፣ ድንግልና፣ መንፈሳዊ ዕውቀት፣ ሌሎችን ማገልገልና ለሐዋርያት አባቶች ያሳየቻቸው መንፈሳዊ እናትነት ከዋና ዋና ጠባዮቿ መካከል ጥቂቶቹ ናቸው::

**በረከቶቿ**

ለድንግሊቱ ማርያም የታደሏት በረከቶች ምንኛ የበዙ ናቸው!

እነዚህ በረከቶቿ በቤተ ክርስቲያን ጥዑመ ዜማዎች፣ በማኅሌቶች፣ ለእግዚአብሔር እናት በሚቀርቡ ውዳሴዎች፣ በአጽዋማት ቀናቶቿና በጸሎት መጻሕፍቶቿ ውስጥ ተካተው ይገኛሉ::

ቤተ ክርስቲያን የቅድስት ድንግል ማርያምን ስም የምታወድሰው በማኅበረ ቅዱሳን ውስጥ ከሚገኙት ከሊቃነ መላእክትና ከሰዎች ሁሉ በፊት ነው:: የምልጃ ጸሎቶቿን የምንደግመውም ከሁሉም የምልጃ ጸሎት አስቀድመን ነው:: ቤተ ክርስቲያን ድንግልን በመባረክ ውስጥ በጸሎቷ የተናገረችውን የትንቢት ቃል «እነሆም ከዛሬ ጀበሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤» (ሉቃ 1:48) እያለች ትደግማለች::

ቤተ ክርስቲያን በድንግል ማርያም ስም ዕጣን ታሳርጋለች በስሟም መባ ታቀርባለች:: «ለማርያም ሰላምታ ይገባል» ወይም «ሻራ ና ማሪና /Shara na Maria» (በቅብጥ) ወይም «ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ» በሚሉት ቃላት የሚጀምሩት የሰላምታ መዝሙራትና አገላለጦች እጅግ ብዙ ናቸው:: ነቢዩ ዳዊት በሚመታው በገና ላይ የተደረደሩት የዜማ ጅማቶች እያንዳንዳቸው በድንግል ማርያም ምስጋና የተቃኙ የቅኝት ስያሜዎች አሏቸው::

በየሰዓቱ የሚደርሱ ጸሎቶችን ባቀፈው የጸሎት መጽሐፍነ በቅዳሴ መጻሕፍትና በሌሎቹም የቤተ ክርስቲያን የጸሎት መጻሕፍት ውስጥ ስሟን እንጠራለን:: በዜማዎቻችንም ውስጥ እንዲሁ::

በየሰዓቱ በሚደርሰው በእያንዳንዱ ጸሎት ውስጥ የሚገኘው ሦስተኛ አንቀጽ የሚማጸነው የድንግል ማርያምን ምልጃ ነው:: በቀኖና ጽሑፋችን ውስጥ በሚገኘው መቅድም ላይ «የእውነተኛው ብርሃን እናት የሆንሽ ሆይ፤እናከብርሻለን ከፍ ከፍም እናደርግሻለን፤የእግዚአብሔር እናት የሆንሽ ቅድስት ድንግል ሆይ . . .» እያልን እናወድሳታለን::





በቡራኬ ጸሎቶቻችን መግቢያና መደምደሚያ ላይ እርሷን እናነሳለን::

ቡራኬያችንን የምንጀምረው «በእግዚአብሔር እናት በኩል የሚቀርቡ ጸሎቶቻችንን፣ ልመናዎቻችንንና ምልጃዎቻችን ቅድስትና ንጽሕይት የሆነችው ድንግል ስለ እኛ ስትል በየጊዜው በእግዚአብሔር ፊት ታቀርባለች:: የመላእክትን፣ የነቢያትን፣ የሐዋርያትን፣ የሰማዕታትንና የሌሎች ቅዱሳንን ስም ከጠራን በኋላም መጨረሻ ላይ «የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም በረከት በመጀመሪያና በመጨረሻ ይድረሰን» እንላለን::

**ምዕራፍ አሥር**
**እርስዋንም ሆነ ሥዕላቷን ቀድሱ**

**የቅድስት ድንግል ማርያም ሥዕል**

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የእግዚአብሔን እናት ስለ ሆነች ምንጊዜም ቢሆን የምትሳለው ከልጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው::

በዳዊት የመዝሙራት መጽሐፍ ውስጥ «በወርቅ ልብስ ተጎናጽፋና ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች::» (መዝ 44) ተብሎ እንደተገለጸው ድንግሊቱ የምትሳለው ከልጇ በስተ ቀኝ በኩል ነው:: ንግሥት ስለሆነችም በራሷ ላይ አክሊል መኖሩ ግድ ነው፤በልጇም ላይ እንዲሁ::

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ::» (ማቴ 5:14) ብሎ በተናገረው ቃል መሠረትና ስላላት ቅድስና በራስዋ ዙሪያ የክበብ ብርሃን ቀርጽ ይሳላል::

ሁለተኛ ሰማይ ስለሆነችም ከዋክብት፣ መላእክትና ደመና በዙሪያዋ ይሳላሉ::

ቅድስት ድንግል ሆይ፤ልጅሽ በምሕረቱ ውስጥ ይደምረን ዘንድ ስለ እኛ አማልጂ::

**በጎውን ሁሉ ለእኛ ያደረገና የሚያደርግ እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን!**



www.ethiopianorthodox.org

## መጽሐፍ ሁለት

# በዘመናችን የተገለጡ የድንግል ማርያም ተአምራት

(ተአምራቷ)

አዘጋጆች፦ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ፮ኛ ልጆች

1. ለሴቶች የሆኑ ምሕረትና ተአምራት::
2. የሴቶች የክብር ታሪኮች::
3. ቅዱሳት ሴቶች::
4. ታላቋ እመቤት::
    ሀ. ድንግሊቱ በክሊቭላንድ::
    ለ. ድንግሊቱና መነኩሴው::
    ሐ. ድንግሊቱና አንል ጉዳተኛዋ ብላቴና::
    መ. ከድንግል ማርያም የቀረበ ስጦታ::
    ሠ. ራእይና ቃል ኪዳን::
    ረ. ሲፈጠር ጀምሮ ዓይነ ሥውር ለነበረው ሰው የሆነ የድንግሊቱ አማላጅነት::
    ሰ. መለኮታዊው መልእክት::
    ሸ. ድንግል ማርያም አባ ገብርኤልን እንደረዳቸው::
    ቀ. ድንግል ማርያም፤ትቀበያታለሽ?
    በ. የገዳሙ እድገት::
    ተ. ድንግል ማርያም በስጦታ ከተማ::
    ቸ. ድንግል ማርያምና አባ ስምያን::
    ኀ. የጠፋችውን ልጃገረድ ድንግል እንደመለሰቻት::
    ነ. የአባ ሚካኤል ሕይወት::
    ኘ. ድንግል ማርያም በአቡ ዛቢ::
    አ. የድንግል ማርያም ሥዕል::
    ከ. ታማኙ ተጠርጣሪ::
    ኸ. ድንግል ሆይ ይቅር በዬኝ::
    ወ. ውቢቷ ርግብ ድንግል ማርያም::
    ዐ. ድንግል ማርያም በአሱዩት::
    ዘ. ቅድስት ማርያምና አባ አባኑብ::
    ዠ. ከድንግል ማርያም የተላከ መልዕክት::
5. ይህ ሁሉ ምን ማለት ነው?





### 1/ ለሴቶች የሆኑ ምሕረትና ተአምራት::

ሴቶች እንደ ሁለተኛ ክፍል ዜጋ በሚቆጠሩበት ጊዜ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕድሜ ደረጃ እንኳ ሳይቀር እውቅና ሰጥቶአቸው ነበር:: አምላካችን እግዚአብሔር ፍቅርና ምሕረትን ለማደል በወንዶችና በሴቶች መካከል ምንም ዓይነት አልፈጠረም::

ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ መግደላዊት ማርያም ያሉና በክፉ ርኩሳን መናፍስት የተያዙ ሴቶችን ፈውሷል:: ስለ እነርሱ በወንጌል የተጻፈው ቃል እንዲህ የሚል ነው:- «. . . ከክፉዎች መናፍስትና ከደዌም ተፈውሰው የነበሩ አንዳንድ ሴቶች፤እነርሱም ሰባት አጋንንት የወጡላት መግደላዊት የምትባል ማርያም፤የሄሮድስ አዛዥ የኩዛ ሚስት ዮሐናም፤ሶስናም፤ ብዙዎች ሌሎችም ሆነው በገንዘባቸው ያገለግሉት ነበር::» ሉቃ 8:2-3::

አምላካችን እግዚአብሔር ለሌሎች ብዙ ሴቶች ሌሎች ተአምራትን ፈጽሟል:: እርሱ የጴጥሮስን እማት ከንዳድ ሕመም ፈውሷል:: ማቴ 8:14እና15:: እርሱ የአሥራ ሁለት ዓመቷን ልጃገረድ እጅ ይዞ «ጣሊታ ቁሚ. . .» (ማር 5:41) በማለት ከሞት አስነስቷል:: እርሱ ናይን የተባለች ከተማ ውስጥ ስለ ሞተ ልጇ ስታለቅስ ለተመለከታት ሴት ስላዘነላት አስከሬኑ ተጋድሞበት የነበረውን ቃሬዛ በእጁ በመንካት ካስነሣው በኋላ ለእናቱ መልሶ ሰጥቶአታል:: ሉቃ 7:11-17:: ለአሥራ ሁለት ዓመታት ደም ይፈስሳት የነበረችው ሴት በእርሱ ላይ በነበራት ታላቅ እምነት ከበሽታዋ ልትፈወስ ችላለች:: ማነ 9:20-22::

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢአተኛ ሴቶች ምሕረት ስለ ሰጣቸው ንስሓ ገብተው ይቅርታ አግኝተዋል:: ለዚህ ምሳሌ የምትሆነን በኃጢአት ውስጥ ትኖር የነበረችው ሣምራዊት ሴት ናት:: ዮሐ 4:5-29::

እንደ ሕጉ ቢሆን ኖሮ ስታመነዝር የተገኘችው ሴት በድንጋይ ተወግራ ትሞት ነበር:: ይሁን እንጂ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሷን የተናገራት እንዲህ ብሎ ነው:- «. . . እኔም አልፈርድብሽም፤ሂጂ ከአሁንም ጀምረህ ኃጢአት አትሥሪ አላት::» ዮሐ 8:11::

ኢየሱስ ክርስቶስ በፈሪሳዊው ቤት ውስጥ ተቀምጦ ሳለ በፊቱ ወድቃ እግሮቹን በእንባዎቿ ስታብስ ስለነበረችው ዘማዊት ሴት እንዲህ በማለት ነው የተናገረው:- «. . . እጅግ ወዳለችና ብዙ ያለው ኃጢአቷ ተሰርዮላታል፤ጥቂት ግን የሚሰረይለት ጥቂት ይወዳል:: እርሷንም:- ኃጢአትሽ ተሰርዮልሻል አላት::» ሉቃ 7:47እና48::

### 2/ የሴቶች የክብር ታሪኮች::

አዲስ ኪዳን በሴቶች ማንነትና ክብር ዙሪያ የተጻፉ ብዙ ታሪኮችን ያስነብበናል:: በመስቀሉ ዙሪያ በነበረው የክብርን ቦታ ሦስት ሴቶች ነበሩ::



www.ethiopianorthodox.org

እነርሱም:- እናቱ ድንግል ማርያም፤የቀለዮጳ ሚስት የሆነችው የእናቱ እኅት ማርያምና መግደላዊት ማርያም ናቸው:: ዮሐ 19:25:: ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ ከሙታን መካከል ከተነሣ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገለጠው ለመግደላዊት ማርያም ነበር:: ማቴ 28:10:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለማርያምና ለማርታም ክብር ሰጥቶአል:: ጌታ እነርሱን በተደጋጋሚ ከመጎብኘቱም በላይ የሚወዱት ወንድማቸው አልዓዛርን ከሞት አስነስቶላቸዋል:: ዮሐ 11:35:: እንደ ማርቆስ እናት እንደ ማርያም ያሉ ብዙ ሴቶች ቤታቸውን ለጸሎት መሰብሰቢያ አድርገው ሰጥተው ነበር:: ሐዋ 12:12:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ መዝጊያ ላይ ስለ ክርስቶስ ሲሉ ከእርሱ ጋር አብረው ይሠሩ ለነበሩት ለጵርስቅላ፣ ለአቂላና በቤታቸው ለነበረች ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ አቅርቦላቸዋል:: ሮሜ 16:3:: ወንጌላዊው ፊልጶስ ትንቢት በመናገር የእግዚአብሔርን መልእክት የሚያስተላልፉ አራት ደናግል ሴቶች ልጆች ነበሩት:: ሐዋ 21:9:: በግብረ ሐዋርያት መጽሐፍ ውስጥ ልድያ ስለተባለችው ሴት የተጻፈውም ቃል እንዲህ የሚል ነው:- «ከትያጥሮን ከተማም የመጣች ቀይ ሐር ሻጭ እግዚአብሔርን የምታመልክ ልድያ የሚሉአት አንዲት ሴት ትሰማ ነበረች፤ጳውሎስም የሚናገረውን ታዳምጥ ዘንድ ጌታ ልብዋን ከፈተላት::» ሐዋ 16:14::

### 3/ ቅዱሳት ሴቶች::

በታሪክ ውስጥ ብዛት ያላቸው ቅዱሳት ሴቶች እንደ ነበሩ እናውቃለን:: ከእነርሱም መካከል:- የቅድስት ሬፍቃ እናት የሆነችው ቅድስት ዴሚያና (St. Demiana) እና አርባው ደናግል ሰማዕታት፤ ንግሥቲቱ ቅድስት አናሲሞን (St. Anasimon)፤ቅድስት አሬጥሲማ (St. Arestsima)፤ቅድስት ዕሌኒ (St. Helena)፤ቅድስት ማሪና (St. Marina)፤ ቅድስት ባርባራ (St. Barbara)፤ቅድስት ቬሬና (St. Verena) እና ሌሎች ቅዱሳት ሴቶች ይገኛሉ:: እነዚህና እነዚህን የመሰሉ ሴቶች በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ጽኑ እምነት ስለ ነበራቸው ሰማያዊ አክሊሎቻቸውን ከእርሱ ተቀብለዋል:: እነዚህ ሁሉ ሴቶች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለሴቶች ሊሰጣቸው የሚገባቸውን የምትሰጥ መሆኗን የሚያረጋግጡ ምስክሮች ናቸው::

በማንኛውም ጊዜ ውስጥ ተአምራት ቅድስት ድንግል ማርያምን እንደከበቧት ነው:: ተአምር ለንስሓና ለድኅነት የሚሆን ግብዣ ነው:: ድንግል ማርያም የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ስለ ሆነች ለሰው ልጆች ድኅነት ትሠራለች:: «ልጆችዋ ይነሣሉ፤ምስጋናውንም ይናገራሉ፤. . .» (ምሳ 31:28) የሚለው ምሳሌያዊ ቃል የተጻፈው ለእርሷ ነው:: ሰዎች ከኃጢአት ላይ ተነሥተው እንደ ድንግል ማርያም ንጹሕና ትሑት ሊሆኑ እስካልቻሉ ድረስ የክርስቶስ ልጆች ሊሆኑ አይችሉም::





እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እ.አ.አ. በ2000 ዓ.ም. አሱዩት (Assuit) ውስጥ በሚገኘው የቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ላይ በተደጋጋሚ ተገልጣለች:: እንደ ሌሎቹ ተአምራት የእኛም ትውልድ ለዚህ ምስክር ሊሆን ችሏል:: ይህ ሰማያዊ መልእክት ለመላው ዓለም በይፋ ታይቷል:: ይህ ምልክት ድንግል ማርያም የዓለም ሁሉ አዳኝ የሆነው ብርሃን ክርስቶስን የወለደች የብርሃን እናት መሆኗን አስረግጧል:: ይህ ደግሞ ሐዋርያዊት የሆነችውን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መሠረትና የክርስትና እምነታችንን በሚገባ አጠናክሯል::

ይህን መጽሐፍ ለሚያነብ ሁሉ መጽሐፉ የሚረዳ ጠቃሚ የእጅ መሣሪያ፣ የጸጋና የመነሣሣት ምንጭ ሊሆነው ይችላል:: ይህ የሚሆነውም በእግዚአብሔር እናት በድንግል ማርያም፣ በቅዱሳን፣ በቅዱስነታቸው አቡነ ሣልሳዊ 3ኛ፣ በጳጳሳትና በካህናት በሚቀርብ ጸሎትና ምልጃ ነው::

### 4/ ታላቋ እመቤት::

> «እንዲህም ይሆናል፤ሳይጠሩ እመልስላቸዋለሁ፤ገናም ሲናገሩ እሰማለሁ::» ኢሳ 65:24::

ኋላ ላይ ካህን ሆኖ የተሾመው ሀቢብ ፋሪግ (Habib Farig) ከድንግል ማርያም ጋር የጠበቀ ዝምድና ስለ መሠረተ እርሷን የሚጠራት «ታላቋ እመቤት» እያለ ነበር:: ይህ ሰው ስለ እርሷ ሲናገር:- እንደ እናትነቷ ለእኛ ለልጆችዋ የሚያስፈልጉንን ነገሮች ሁሉ እኛ ከምናውቀው የበለጠ ታውቃለች ብሏል:: ከዚህ በተጨማሪ ክርስቶስ ለእኛ ሊያደርገው ያሰበውን ታውቃለች ብሎ ተናግሯል:: የድንግሊቱ በሕይወታችን ውስጥ መኖር የክርስቶስን ተአምራታዊና መለኮታዊ ጣልቃ ገብነት በተስፋ እንድንጠብቅ ያስችለናል ብሎ ያምናል:: በአማላጅነቷ ውስጥ በእርሱ ዘንድ ያለውን መለኮታዊ ኃይልና በረከት እንመለከታለን::

ሀቢብ ገና ወጣት ሳለ በድንግል ማርያም በኩል እግዚአብሔር የሠራውን ሥራ ለመመስከር በቅቶአል:: አያቱ በሕልሟ መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት ማንበብ እንዳለባት ድንግል ማርያም እንዳስተማረቻት ተመልክቷል:: ይህች አያቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሌላ ምንም ዓይነት መጽሐፍ ማንበብ አትችልም:: አሥራ ሰባት ዓመት ሲሞላው ከክርስቶስ ጋር ይኖር ዘንድ «ታላቋ እመቤት» ስትጠራው ለጥሪዋ የሰጠው መልስ ቆጽበታዊ ነበር:: «. . . የመጀመሪያ እምነታችንን እስከ መጨረሻው አጽንተን ብንጠብቅ የክርስቶስ ተንፋዮች ሆነናልና፤እየተባለ:- ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት፤በማስመረር እንደ ሆነ፤ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ::» ዕብ 3:14-15::



www.ethiopianorthodox.org

ከዕለታት አንድ ቀን ድንግል ማርያም ኃጢአተኞች የሚላኩበትን ሥፍራ ለሀቢብ በራእይ አሳየችው። ሥፍራው በፈሳሽ እሳት የተሞላ ገደል ነበር። በደለኞች በዚያ ገደል ውስጥ ተጥለው የጩኸት ሰቆቃ ያሰሙ ነበር። ነፍሱ ስለተጨነቀችበት ድንግል ማርያም ከዚያ ሥፍራ አርቃ እንድትወስደው ይጠይቃታል። በዚህ ጊዜ በትዕምርተ መስቀል እንዲያማትብ ስትነግረው ራሱን በዙፋናት ላይ የተቀመጡ ቅዱሳን ሰዎች ያሉበት ሰማያዊ ቦታ ላይ ያገኘዋል። ሀቢብ ከእነዚያ ሁሉ ዙፋናት መካከል አንድ ሰው ያልተቀመጠበት ዙፋን ስለ ተመለከተ «ይህ ዙፋን የማነው?» ብሎ ይጠይቃታል። እርሷም «የጌታዬን፣ የአምላኬንና የልጄን ፈቃድ የምትከተል ከሆንህ ለአንተ ይሆናል።» አለችው። ከዚያች ቀን አንስቶ ከዚህ ዓለም ላይ በ27 ዓመቱ በሞት እስኪለይ ድረስ ስለ ክርስቶስ ኖረ።

ለሀቢብ የቀረበለት ግብዣ ዛሬ ለእኛም ቀርቦልናል። ለድኅነታችን የሚበጀውን ይህን ግብዣ ከድንግል ማርያም ለመቀበል ልባችንን የምንከፍትበት ትክክለኛ ጊዜ አሁን ነው። ቀጣይነት ያላቸው ተአምራቷን ስንከተል በሰማያዊው ሥፍራ ላይ የሚጠብቀንን ሰማያዊ ዙፋን እንሞላ ዘንድ እየጠበቀችን መሆኗን እንመለከታለን።

### ሀ. ድንግሊቱ በክሊቭላንድ (Cleveland)።

> «አቤቱ፤አንተ አምላኬ ነህ፤ድንቅን ነገር የዱሮ ምክርን በታማኝነትና በእውነት አድርገሃልና፤ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ፤ ስምህንም አመሰግናለሁ።» ኢሳ 25፡1።

ምንም እንኳ የአየሩ ሁኔታ በጣም ሞቃት ቢሆንም ለሥራው ፍቅር ያለው አንድ መሐንዲስ በታላቋ ካይሮ ውስጥ በመገንባት ላይ ያሉትን 700 መኖሪያ ቤቶች እየተቆጣጠረ ነው። አንድ ቀን እንዲሁ ንዳድ ከሆነችው ፀሐይ በታች ሳለ ድንገት መተንፈስ ያቅተዋል፤የግራ እጁ ላይም ከፉኛ ሕመም ሊሰማው ይጀምራል። በዚህ ጊዜ አፋፍሰው በቅርቡ ወደሚገኝ አንድ ሆስፒታል ይወስዱትና በዚያ በተደረገለት ሕክምና ከደም ሥሮቹ በአንደኛው ላይ የደም መርጋት (thrombosis) ይገኝበታል። ተከታታይና ከባድ ውጋት ስላጣደፈውም የጤናው ሁኔታ አስጊ ደረጃ ላይ ይደርሳል።

እንክብካቤና እረፍት እያገኘ ባለበት ሁኔታ ውስጥ አንዳንድ ቀን እስከ አምስት የሚደርሱ ከባድ ውጋቶች ይሰሙት ነበር። አንድ ምሽት የሚስበው ንጹሕ አየር አተነፋፈሱን እያስተካከለለት ስለ መጣ ይህንኑ በስፋት ያገኝ ዘንድ ወደ ሆስፒታሉ ሰገነት ተሸክመው ያወጡታል። በዚያ ሳሉ ሁሉም አንዲት ትልቅና አንጸባራቂ ርግብ እነርሱ ወደቆሙበት ሥፍራ ስትመጣ ይመለከታሉ። በጣም ከቀረበቻቸው በኋላ ብሩኅ የብርሃን ዓምድ





ከርግቢቱ ሰውነት በመውጣት የመሐንዲሱን ደረት ሰንጥቆ ይገባል። ይህ ከሆነ በኋላ ርግቢቱ በመጣችበት አኳኋን ተመልሳ ትሄዳለች።

ከዚህ ክስተት በኋላ ውጋቱ ሙሉ ለሙሉ ሊጠፋ ባይችልም መጠኑ እየቀነሰ ይመጣል። ራጂና ቀዶ ጥገና ሕክምና ስለታዘዘለትም አሜሪካን ሀገር ወደሚገኘው ወደ ክሊቭላንድ ሆስፒታል ይወሰዳል። ቀዶ ጥገናው ነገ ሊሆን እንደ ዛሬ መለኮታዊው እርዳታ ይደርስለት ዘንድ ድንግል ማርያምን ይማጸናታል። ጥልቅ በነበረው በዚህ ጸሎቱ መካከል «እኔ ከአንተ ጋር ስለ ሆንሁ ምንም አትፍራ!» የሚል አበረታታች ድምፅ ይሰማል። በሰውነቱ ውስጥ አንድ የማይታይ ነገር ማለፉ ከታወቀው በኋላ በሰላም ይሞላል።

ከዚያች ቀን በኋላ መሐንዲሱ ምንም ዓይነት ሕክምና ሳይከታተል ወደ አገሩ ተመልሶ ሥራውን ይቀጥላል። ይህ ሰው ሙሉ ለሙሉ የተፈወሰው በድንግል ማርያም አማላጅነት ነበር።

### ለ. ድንግሊቱና መነኩሴው።

እንደ እ.አ.አ. ከ1935-1992 ዓ.ም. ድረስ የኖረው የአንጦንያኑ አባ ታድሮስ (Father Tadros The Antonian) ምንኩስናን የተቀበለው በ1959 ዓ.ም. ሲሆን በዚህ ምድር ላይ የኖረው እንደ ሰማያዊ ሰውና እንደ ምድራዊ መልአክ ነበር። እርሱ የዘመናቱን ቀናት ያሳለፈው ታላላቆችን በማገልገል፣ ዜማዎችን በማዜምና በመጸለይ ነበር።

ኑሮውን በምንኩስና ሕይወት ስላሳለፈ ከፍተኛ ማዕረግ መቀበልን ፈጽሞ አያስብም ነበር። የመነኩሴ ኃላፊነት የራሱን ድርጊት መጠበቅ ላይ ሲሆን የካህን ኃላፊነት ግን የብዙ ሌሎች ሰዎች ድኅነት መጠበቅ ላይ ነው ብሎ ያምናል። ይህ በመሆኑም ነው ቅዱስነታቸው አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ ያቀረቡለትን የክህነት ሥልጣን «እኔ የምሻው እንደ አንድ ተራ መነኩሴ ኖሬ መሞትን ነው።» በማለት ለመቀበል አሻፈረኝ ያለው።

አባ ታድሮስ ብዙ ፈተናዎችና መከራዎች ቢገጥሙትም ያሳለፋቸው በትዕግሥትና ዘወትር ለፈጣሪው ምስጋና በማቅረብ ነበር፤ መከራዎቹ እጅግ ከባድ ቢሆኑም። በትዕምርተ መስቀል ሲያማትብ ርኩሳን መናፍስትን ድል ይነሳቸው ነበር። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚፈውሰው በሽታ በመስጠት የሰዎችን የእምነት ደረጃ ይፈትሻል ብሎ ያምናል።

በአንድ ወቅት አባ ታድሮስ ሊሸከሙት የማይቻል ከባድ የሆድ ህመም ሲያመው መነኮሳት ወንድሞቹን ለማስደሰት ሲል ብቻ ከእነርሱ ጋር ወደ ሆስፒታል ለመሄድ ይስማማል። እዚያ ሲደርስ የተደረገለት



www.ethiopianorthodox.org

ምርመራም በሆዱ ውስጥ በቀዶ ጥገና ሲወገድ የሚገባው ዕጢ መኖሩን ያሳያል:: ይህ ቀዶ ጥገና ከመካሄዱ በፊት ግን አባ ታድሮስ በገዛ ፈቃዱ ሆስፒታሉን ለቆ ይወጣል:: ይህን ካደረገ በኋላ ግን ሰዎችን ሁሉ በሚያስደንቅ ሁኔታ የጤንነቱ ሁኔታ እየተሻሻለ ይሄድ ጀመር:: እርሱ እንደሚናገረው ከሆነ የጤንነቱ ሁኔታ ያለ ቀዶ ጥገና እየተሻሻለ የመጣው በቅድስት ድንግል ማርያምና በሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ አማላጅነት ነው::

በዚህ ምድር ላይ የሚኖርባቸው ቀናት መጨረሻ እየተቃረበ ሲመጣ ምግብና መድኃኒት መውሰዱን ያቆምና በአጠገቡ ለሚገኙት ለወዳጆቹ መነኮሳት «ታፎስ፤ታፎስ» ወይም «የመቃብር ስፍራ፤የመቃብር ስፍራ» ይላቸው ነበር:: በመጨረሻም ድንግል ማርያም ባለችበት ነፍሱን ለጌታው እንዲህ በማለት ያስረክባል:- «ወደ እኔ ነይና ነፍሴን ነጻ አስወጪያት፤ ጠላቶቼን ከእግሬ በታች ጣያቸው፤ነፍሴን እንዳያፍኗት የሲዖልን ደጃፍ በላያቸው ላይ ዝጊባቸው፤የእውነተኛው ሙሽራ ፍጹም ሙሽሪት አንቺ ነሽና::»

## ሐ. ድንግሊቱና አካል ጉዳተኛዋ ብላቴና::

እ.ኤ.አ. ከ1905-1988 ዓ.ም. በካይሮ ይኖር የነበረው አባ ሩፋኤል ቄርሎስ (Father Rafael Kyrollos) ሙሉ ለሙሉ ሕይወቱን ለእግዚአብሔር የሰጠ አባት ነበር:: የምንኩስናን ሥልጣነ ክህነት ከመቀበሉ አስቀድሞ በድቁና ከጳጳሱ ከአባ ቄርሎስ ጋር ያገለግል ነበር:: በዚያን ጊዜም «ምሥጋና ለድንግል ማርያም፤ለመላእክት፤ለሐዋርያትና ለቅዱሳን ሰዎች ይሁን::» እያለ ያዜም ነበር:: ከእለታት አንድ ቀን ጳጳሱ አባ ቄርሎስ ይህን ዜማ የሚያዜመው ማን እንደሆነ ይጠይቁና ከእርሳቸው ጋር ያዜም ዘንድ ይጠይቃሉ:: ሰዎቹም ሁልጊዜ ረፋዱ አምስት ሰዓት ላይ ቅዳሴ የሚያስቀድሰው ዲያቆኑ ሰዒድ መሆኑ ይነገራቸዋል::

ከዚህ በኋላ መጋቢት 4 ቀን 1968 ዓ.ም. (እ.አ.አ.) ጳጳሱ አባ ቄርሎስ ቅዳሴ እንዳለቀ ዲያቆኑ ሰዒድን እንደሚፈልጉት ተናግረው ያስጠሩታል:: በዚህ ጊዜ ዲያቆን ሰዒድ ጳጳሱ እንደሚፈልጉት ሲነገረው በጣም ይደነቃል:: እጅግ የተደነቀው ግን ለምንኩስና ማዕረግ የተመረጠ መሆኑን ሲነግሩት ነበር:: የቀረበለትን ጥያቄ በትሕትና ውስጥ ሆኖ «እኔ ጌታዬን ለማገልገል የምበቃ ሰው አይደለሁም::» ብሎ አልቀበልም ቢልም መጋቢት 12 ቀን 1968 ዓ.ም. የምንኩስና ማዕረግን አባ ሩፋኤል ከሚለው ስም ጋር ይቀበላል::

ከዚህ በኋላ አባ ሩፋኤል የተቀደሰውን ዐቢይ ጾምና ሌሎች አጽዋማትን ለራሱ ይበልጥ በመቀደስ እግዚአብሔርን ከበፊቱ ይበልጥ ማገልገል ይጀምራል:: በገዛ ራሱ ፈቃድም በድህነት መኖርን መርጦ





አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያሳለፈውን ይህን የድህነት ሕይወት ገንዘቡ ያደርጋል:: ይህን በማድረጉም ዲያብሎስን ድል ይነሣው ጀመር:: «. . . እርሱም መልካም እያደረገ፤ለዲያብሎስ የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፤ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና፤. . .» ሐዋ 10:38::

አንድ ቀን አንድ ትንሽ ልጅ ወደ አባ ሩፋኤል ቀርቦ የአካል ጉዳት ለደረሰባት እኅቱ እንዲጸልይላት ይነግራቸዋል:: ይህቺን ልጅ ብዙ የሕክምና ባለሙያዎች ቢመለከቷትም የጤናዋ ሁኔታ ከዕለት ወደ ዕለት ይበልጥ እያሽቆለቆለ ይሄድ ጀመር እንጂ ምንም ዓይነት መፍትሔ ልታገኝ አልቻለችም:: አባ ሩፋኤል በሽተኛዋን ልጅ ሲመለከት በጣም መታመሟንና ከወገቧ በታች ያለ የሰውነቷ ክፍል የማይላወስ መሆኑን ያጤናል:: በዚህ ጊዜ በልጅቱ ግርጌ እንደ ቆመ አቀርቅሮ በመጸለይ ኢየሱስ ክርስቶስ ብላቴናዋን ይፈውሳት ዘንድ ይጠይቃል::

ይህን ካደረገ በኋላ ለልጅቱ እንዲህ ይላታል:- «እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ድንግሊቱ ትፈውስሻለች በአንቺም ትከብራለች:: ለእግዚአብሔር የሚሳነው ምንም ነገር የለም፤ድንግሊቱ ደግሞ ፍጹም ርኅሩኅ ናት::» ይህን ብሎ ሲያበቃ ብላቴናዋን ለበሽተኞች የሚዘጋጀውን ቅባዐ ቅዱስ ከቀባት በኋላ ፀጥ ብሎ ወጥቶ ይሄዳል::

ከሦስት ቀናት በኋላ አባ ሩፋኤል ልጅቱን ቅባዐ ቅዱስ በቀባበት ተመሳሳይ ሰዓት ላይ በሽተኛዋ የተኛችበት ክፍል መዝጊያ በዝግታ ሲቆረቆር ከሰማች በኋላ እመቤታችን ሙሉ ሰማያዊ ቀለም ያለው ረዥርም ቀሚስ ለብሳ በራሷም ላይ አክሊል አጥልቃ ትገባለች:: ከዚያም አባ ሩፋኤል ቆሞ የነበረበት ቦታ ላይ ቆማ እጇን ወደ ልጅቱ በመዘርጋት ከአልጋዋ ላይ ታነሣታለች:: ልጅቱ ለረዥርም ጊዜ በአልጋዋ ተኝታ ከኖረች በኋላ በሁለት እግሮቿ ቀጥ ብላ ትቆማለች:: በዚህ ጊዜ በአግራሞት ተውጣ «እመቤቴ ሆይ፤ ምስጋና ይገባሻል! ድንግል ሆይ፤ምስጋና ይገባሻል!» በማለት ታመሰግን ጀመር:: ከዚያም «ድንግል ማርያም መጥታ አዳነችኝ!» በማለት ስቅስቅ ብላ አለቀሰች:: መላው ቤተሰብም ለቸሩ እግዚአብሔርና ለርኅርኂቱ ድንግል ምስጋና አቀረበ::

## መ. ከድንግል ማርያም የቀረበ ስጦታ::

ይህ ተአምር የጀመረው እ.አ.አ. በ1995 ዓ.ም. አሜሪካን አገረ ውስጥ ነው:: አንድ ባል የ22 ዓመት ሚስቱንና አዲስ የተወለደ ልጁን ጥሎ ይጠፋል:: በዚህ ጊዜ ወጣት ሚስቱ ከፊት ለፊቷ ከጨለማ በስተቀር ሌላ ተስፋ አልታይሽ ይላታል:: ቤተሰቦቿ በልጃቸው ላይ የደረሰውን መራር ኀዘንና ጉዳት ማሳለፍ ትችል ዘንድ እግዚአብሔር ችግሯን



www.ethiopianorthodox.org

እንዲያቀልላት ድንግል ማርያምም በምልጃዋ እንድትረዳቸው አጥብቀው ይማጸኗታል።

በዚህ ጊዜ ውስጥ ድንግሊቱ በወጣት ልጃገረድ ተመስላ ሰማያዊ መልእክት ስትነግራት በራእይ ትመለከታለች። ድንግሊቱ ለዚህች ሴት የሰጠቻት ምክር ወደ ባሏ ተመልሳ እንዳትሄድና ከነጭራሹ እንድትረሳው ነበር። «. . . እኔ ግን ገና እንዳልያዝሁ እቆጥራለሁ፤ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴም ወዳለው እየተዘረጋሁ፤. . .» ፊልጵ 3:13። ከዚህ በኋላ ሴቲቱ ድንግል ማርያምን ትከተላት ዘንድ ታሳስባታለች። ከዚያም ወደ አንድ የተዋበ የአትክልት ሥፍራ እየመራቻት ትገባና በዚያው ውስጥ የሚገኝ በረንዳ ላይ ይዛት ትወጣለች። እዚያ ላይ እያሉም ድንግሊቱ በቀይ ጨርቅ የተጠቀለለና አምስት ስፍራ የተከፋፈለ ስጦታ ታበረክትላታለች። ከዚያም ይህ ስጦታ ያለባትን ሕማምና መከራ እንደሚያጠፋላት ትነግራታለች።

ከአንድ ወር በኋላ ሴቲቱ በአንድ ስመጥር ከፍተኛ ተቋም ውስጥ የምርምር ሥራ እየሠራች የዶክትሬት ትምህርቷን እንድታጠና ጥሪ ይደርሳታል። እርሷም የተሰጣትን ማዕረግ ያለ ማመንታት ትቀበላለች። አዲስ ሥራዋና ለልጅዋ የነበረባት ኃላፊነት ሙሉ ለሙሉ ባተሌ አደረጓት። በእግዚአብሔርና በማኅበረሰቡ ላይ ያላትን እምነት መልሳ ስላገኘችው ድንግል ማርያም ስለምትፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ እንድታማልዳት በጸሎት ትጠይቃት ጀመር።

ከአምስት ዓመታት በኋላ የሴቲቱ የመመረቂያ ጽሑፍ ተጠናቆ ለኅትመትና ለጥረዛ ዝግጁ ሆነ። የመመረቂያ ጽሑፏን ለመቀበል ስትሄድ ድንግል ማርያም ከዓመታት በፊት የሰጠቻት ስጦታ የጠቀለለበት ጨርቅ ቀይ ቀለምና የመመረቂያ ጽሑፏ ሽፋን ቀለም ፍጹም ተመሳሳይ ሆኖ ስላገኘችው እጅግ ትደነቃለች። ይህ በመሆኑም የዶክትሬት ዲግሪዋን በቀይ ጨርቅ ጠቅልላ የሰጠቻትን ቅድስት እናቱን የሚንከባከበውን እግዚአብሔር አመሰገነች።

**ሠ. ራእይና ቃል ኪዳን።**

ላሚ (Lamyee) የእርሻ ሥራ ንግድ በመሞከር ኮም ኦምቡ (Kom Ombou) ውስጥ የተለያዩ ሽቀጣ ሽቀጦች የሚሸጡበትን የገበያ አዳራሽ ይከፍታል። ይሁን እንጂ በሚያሳዝን ሁኔታ ስለ ከሠረ ከፍተኛ ዕዳ በራሱ ላይ ይቆለላል። በዚህ ጊዜ ሌላ አማራጭ ለመፈለግ ከአንድ ባልንጀራው ጋር በቀጥታ ወደ እስክንድርያ ይሄዳል።

በእስክንድርያ ሳሉ የላሚ ባልንጀራ በእንቅልፉ አንድ ራእይ ይመለከታል። በዚህ ራእዩ ውስጥ አንድ ታዋቂ የሚመስል መኮንን አንዲት





ድንቅ ሴት ወደ ተቀመጠችበት ክፍል እየመራ ይወስደዋል። ከዚያም ይኸው መኮንን እንዲህ በማለት ይናገራል፦ «እርሱ እርግጠኛ ባይሆንበትም ፈቃደኛነቱ ካለው እግዚአብሔር በደሉን ሊያርቅለት ይችላል። እግዚአብሔር ስለ መረጠውም ከእርሱ ውስጥ የማይደርቅ ባሕር ያፈልቃል። ብዙዎችም ወደ እርሱ በመቅረብ ጥማቸውን ያረካሉ።» ከዚህ በኋላ መኮንኑ ላሚ ባልንጀራውን በመያዝ ወደ ኮም ኦምቡ ተመልሶ እንዲሄድ ያዝዘዋል።

በእግዚአብሔር ምሪት ላሚ የንግድ ሥራውን አቅጣጫ ወደ ቤት ግንባታ ያዞራል። ይህን የሥራ ስፍራውንም «የነጻነት መንደር» ብሎ ይሰይመዋል። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ቤት ለመግዛት ወደዚያ ስፍራ መጉረፍ ይጀምራሉ። ይህ ሰው ክርስቲያን ወይም እስላም ብሎ ሳይለይ ሰዎችን ሁሉ በእኩል ዐይን ስለሚመለከት በእያንዳንዱ ሰው ዘንድ ተወዳጅነትን ያተርፋል።

ላሚ ይህን ቢያደርግም ለድንግል ማርያም ሊያንጽ ያሰበውን ቤተ ክርስቲያን ፈጽሞ አልዘነጋም። ስለሆነም ለዚህ ፕሮጀክት የሚውል ሰፋ ያለ መሬት አዘጋጅቶ ነበር።

ላሚ ያቀደው ዋናው መሠዊያ የምሥራቁን አቅጣጫ ተከትሎ እንዲገነባ ከመሆኑም በላይ የቤተ ክርስቲያኑ መሠረት እዚያው ላይ እንዲጣል ነበር። ይሁን እንጂ ባልንጀራው አስቀድሞ የተመለከታት ድንቅ እመቤት በድጋሚ በራእይ ተገልጣ ሌላ ራእይ ትገልጥለታለች። በዚህ ራእይ ውስጥ እርሷና ሌሎች ሁለት ሰዎች በፈረስ ላይ ተቀምጠው ይመለከታል። ይህችው ሴት መሠረቱ የተጣለበት ቦታ ላይ ሄዳ ከፈረሷ ላይ በመውረድ ጸሎት መጸለይ ትጀምራለች። ከዚያም (Morcos,Girgis) «ምርቆስ፤ጊርጊስ» (ቅዱስ ማርቆስና ቅዱስ ጊዮርጊስ) በማለት የሁለት ሰዎችን ስም ትጠራለች። በመቀጠልም የራሷን እጆች በመጠቀም የመጀመሪያውን ሸክላ በስተ ሰሜን አቅጣጫ ታኖራለች። በዚህ ጊዜ የላሚ ባልንጀራ «አይሆንም የእኔ እመቤት፤ሴት ልጅ የቀን ሠራተኛ ሆና እንድትሠራ አንፈቅድም።» በማለት ይከለክላታል። ሴቲቱም እንዲህ ብላ ትመልስለታለች፦ «ሴት ልጅ በቤቷ ውስጥ ብትሠራ ምንም ነውር የለበትም። ባለቤትህ በቤትህ ውስጥ እንደምትሠራ ሁሉ እኔም የአባቴን ቤት እገነባለሁ።»

በነጋታው የላሚ ባልንጀራ ለላሚ ስላየው ራእይ ይነግረዋል። ላሚም ቅድስት ድንግል ማርያም ከቅዱስ ማርቆስና ከቅዱስ ጊዮርጊስ ጋር በመምጣት ቦታውን እንደ ባረከችውና ሥራው በእርሷ አማላጅነት ተጀምሮ የሚጠናቀቅ መሆኑን ያምናል።



www.ethiopianorthodox.org

በቀጥታ ወደ ሴት ልጃቸው ቤት ሲሄዱ ቤተሰቡ ወደዚሁ ገዳም መሄዱ በመልእክት ይነገራቸዋል።

የማሪና ቤተሰቦች ወደ ገዳሙ እንደ ደረሱ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ምልጃና ጸሎት እግዚአብሔር አምላክ የልጃቸውን ዓይኖች እንዲያበራ አጥብቀው ይማጸኑታል። ከዚህ በኋላ ልጃቸው ማሪና ቅባዕ ቅዱስ ትቀባለች። አብዛኛዎቹ መነኮሳይያት እግዚአብሔር በልጃቸው ላይ እንደሚከብርና ልጃቸውም ማየት እንደምትችል ያረጋግጡላቸው ጀመር። ከጥቂት ጊዜ ቆይታ በኋላ ለምስጋና ጸሎት እንደሚመለሱም ይነግሯቸው ነበር።

በሚቀጥለው ቀን ጠዋት የክፍሉን መጋረጃዎች ሲገልጡ ልጃቸው ወደ ክፍሉ ለገባው ብርሃን ምላሽ ስትሰጥ ተመለከቷት። ማሪና ከዚህ ቀደም አድርጋው የማታውቀውን ነገር አጠገቧ ሆኖ ወደሚያጫውታት ሰው ፊቷን ስትመልስም ታየቻቸው።

ከዚህ በኋላ ማሪናን ወደ ዐይን ሕክምና ተቋም በመውሰድ በዚህ ሙያ የላቀ እውቀት ወዳለው የሕክምና ባለሙያ ቀርበው ስላለፈ የሕክምና ታሪኳ አንድም ነገር ሳይናገሩ እንዲመረምራት ያቀርቡለታል። ታዋቂው የሕክምና ባለሙያ ምርመራውን ካጠናቀቀ በኋላ፡- «ይህቺን ልጅ ወደ እኔ ያመጣችኋት ለምንድር ነው? ልጅቱ እኮ ምንም የሆነችው ነገር የለም።» ይላቸዋል። በዚህ ጊዜ የማሪና አባት የቀድሞውን የምርመራ ውጤት ለሐኪሙ ሲያቀርብለት ምላሹ እንዲህ የሚል ነበር፡- «ለፕሮፌሰሮቹ ሊሰጣቸው የሚገባ ክብር ምንም ሳይጓደል አሁንም ቢሆን ልጅቱ ምንም የሆነችው ነገር የለም።»

በዚህ ጊዜ የመጀመሪያውን ምርመራ ወዳካሄደላት ታዋቂ ፕሮፌሰር ይዘዋት ይሄዳሉ። እርሱም በከፍተኛ አድናቆት ተውጦ «አሁን ምን እንደ ተፈጠረ ማወቅ አልችልም! ሌላ አይታ ድራብ የተፈጠረላት ነው የምትመስለው! አዲስ አይታ ድራብ ስለ ተፈጠረ ይህ በእርግጥ ተአምር ነው! ለዚህ ራሱን የቻለ መግለጫ ያስፈልገዋል።» አለ።

የማሪና ወላጆች ልባቸው በደስታ እየፈነደቀ ከሕክምናው ተቋም ወጡ። እግዚአብሔርን ስለ በረከቱ፣ ስለ ቸርነቱና የብርሃን እናት በሆነችው በእናቱ በቅድስት ድንግል ማርያም በኩል ላከናወነው የአማላጅነቷ ተአምር አመሰገኑት።

ሰ/ መለኮታዊው መልእክት።

«እነሆ በትዕግሥት የጸኑትን ብፁዓን እንላቸዋለን፤ኢዮብ እንደ ታገሠ ሰምታችኋል፤ጌታም እንደ ፈጸመለት





አይታችኋል፤ጌታ እጅግ የሚምር የሚራራም ነውና።» ያዕ 5:11።

አንድ የግንባታ ሥራ የሚያከናውን ባለሙያ ሚስቱ ከጊዜ በኋላ ከወገቧ በታች ሽባ ስለ ሆነች ሲፈታት የፍቺውን ደብዳቤ ሲያቀርብላት ያስባል። እንደ ምርመራው ውጤት ከሆነ በሽታዋ ሊድን የማይችል በሽታ ነው። ባለቤቷ ገና ወጣት ስለ ነበር የምትረዳ የትዳር ጓደኛ እንጂ ሸክም የምትሆን ሚስት አላስፈለገችውም።

የፍቺውን ጽሕፈት ከማቅረቡ በፊት ግን መጽናናትና ንጹሕ ኅሊና ለመያዝ ስለ ወደደ ከአንድ ካህን ምክር ለመቀበል ይሻ ጀመር። ካህኑ የሰውየውን ችግር በርጋታ ሲያደምጠው ከቆየ በኋላ እርምጃውን ከመውሰዱ በፊት ለሦስት ቀናት ያህል የድንግል ማርያምን አማላጅነት በጸሎት በመጠየቅ እንዲቆይ መከረው። ካህኑም የሰውየውን ስም በቁራጭ ወረቀት ላይ ከጻፈ በኋላ በመሠዊያው ላይ አኖረው።

ሦስቱ ቀናት ከመጠናቀቃቸው በፊት ሰውየው ከሚሠራበት ያልተጠናቀቀ ረዥም ፎቅ አጠገብ ከቆመ መወጣጫ ላይ ወድቆ ከወገቡ በታች ሽባ መሆኑን በሕልሙ ይመለከታል። ባለቤቱ ታላቅ የልቅሶ ሰቀቀን ውስጥ ገብታ ስትንሰቀሰቅ በዚያ የተሰበሰቡት ሰዎች ዕድሜ ልኩን ሽባ ሆኖ ለሚኖር ሰው ይህን ያህል ልቅሶ አያስፈልግም። ይልቁንም የፍቺ ወረቀትሽን አቅርበሽ ከእርሱ ብትለዩ ይሻልሻል እያሉ ሲያጽናኗት ይመለከታል። እርሷ ግን እርሱን እጅግ በሚያስደንቅ ሁኔታ ለሰዎቹ እንዲህ ብላ ስትመልስላቸው ያያል፡- «ባለቤቴን በሚገባ መንከባከብና መርዳት ስለምፈልግ በቤቴ ውስጥ እርሱን እንደ ባሪያ ጠዋትና ማታ አገለግለዋለሁ። ምንም ዓይነት ነገር ቢፈጠር ትቼው አልሄድም።»

ሰውየው ከእንቅልፉ ሲነቃ ሕልሙ ለትዕግሥትና ለጽናት ከእግዚአብሔር የተላከ መልእክት መሆኑን ይገነዘባል። እርሱ በሚስቱ ቦታ ላይ ቢሆን እርሷ ጥላው እንድትሄድ አይፈቅድላትም ነበር። እርሱም ቢሆን ለእርሷ በትክክል ማድረግ የሚገባው ይህንኑ ነው።

ከዚህ በኋላ በቀጥታ ወደ ካህኑ በመሄድ ራሱን ሙሉ ለሙሉ እንደሚሰጥ በይፋ ይገልጽለታል። በበሽታዋ ሁሉ እንደሚንከባከባትና በፍጹም ፍቅርና ደስታ እንደሚያገለግላት ቃል ይገባል። ገቢው የሚያረካ ባይሆንም በቃሉ ለመኖር በድጋሚ ያረጋግጣል።

ይህ ሰው ነሐሴ 21 በሚከበረው በእመቤታችን በዓል ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳል። በዕለቱ የሚሰጠው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዳበቃ ሕፃናት ተሰብስበው ሲጫወቱ ተመለከተና ሽባ ከሆነች ሚስቱ



www.ethiopianorthodox.org

እስከ መጨረሻው ድረስ ልጅ እንደማያገኝ አሰላስሎ ለጊዜው አዘነ:: ይሁን እንጂ አሁን ስላለው ነገር እግዚአብሔርን አመስግኖ ሲያበቃ ሚስቱ ያለችበትን ሁኔታ ተቋቁሞ ያሳልፍ ዘንድ መለኮታዊ እርዳታው እንዳይለየው የድንግል ማርያምን አማላጅነት ተመርኩዞ ጠየቀ::

የዚያን ዕለት ወደ ቤቱ ሲደርስ አንድ ነገር የተፈጠረ ስለ መሰለው ጥንካሬ ተሰማው:: ወዲያው የቤቱን መዝጊያ ከፍቶ ሲገባ ድንቅ የሚያንጸባርቅ ብርሃን ቤቱን ሞልቶት ተመለከተ:: ከዚያም ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመሄዱ በፊት ሚስቱ ተቀምጣ ወደነበረችበት ስፍራ ሄደ:: እርሷ ግን በቦታዋ ላይ አልነበረችም:: ይልቁንም ሙሉ ለሙሉ ድና ልትቀበለው ወደ እርሱ ስትቀርብ ተመለከታት::

የሚመለከተውን ነገር ማመን አልቻለም:: «ይህ ሊሆን አይችልም! ሽባ የነበረችው ሚስቱ ቆማ እየተራመደች ነው! ይህ ተአምር መሆን አለበት!» እያለ በተደጋጋሚ ይጮህ ጀመር::

ጥቂት ከተረጋጋ በኋላ ሚስቱን ምን እንደ ተፈጠረ ይጠይቃት ጀመር:: እርሷም ረጋ ብላ የተፈጠረውን ነገር ተረከችለት:- «አንተ ወደ ቤተ ክርስቲያን ከሄድህ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ድንግልን:- 'ድንግል ሆይ፤አንቺ የወደድሽው ይህንን ነው? ሁሉም ሰው በዓልሽን እያከበረ፣ ቅዳሴሽን እያስቀደሰ፣ ቅዱስ ቁርባንም እየተቀበለ ነው:: እኔ ግን በአራት ግድግዳዎች መካከል ሽባ ሆኜ ተዘርግቼያለሁ!' እያልሁ እለምናት ጀመር::» ወዲያውኑ የሚያንጸባርቅ ገጽታ ያላት አንዲት የምታምር እመቤት ተመለከትሁ:: ከዚያም እመቤቲቱ በርኅራኄ ቃል «ተነሽና ተራመጂ!» አለችኝ:: እኔም «እመቤቴ ሆይ፤ይህንን እኮ ማድረግ አልችልም:: ሌላው ቢቀር እግሮቼን ለእርምጃ ማንቀሳቀስ ተረስቶኛል::» አልኋት:: ከዚህ በኋላ ሙከራ ሳደርግ በሚያስደንቅ ሁኔታ ቆምሁ መራመድም ቻልሁ:: እርሷም እንዲህ አለችኝ:- 'ባልሽን ስለ ፍቅሩ፣ ስለ እምነቱና ስለ ትዕግሥቱ አመስግኚው:: እግዚአብሔር በልጆች በረከት ይጎበኛችዋል፤በሰማይም ሆነ በምድር ዋጋውን እጥፍ ድርብ ያደርግለታል::'»

ሁለቱ ጥንድ ሰዎች ለረዥም ደቂቃዎች በመቆም ይህን ያደረገላቸውን እግዚአብሔርና ያማለደቻቸውን ድንግል ማርያም በጸሎት አመሰገኑ:: መሐሪ እግዚአብሔር ለእርሷ ሙሉ ጤንነት ለታማኝ ባሏ ደግሞ ዋጋ እንደሚሰጠው ቃል ገባለት::

«ከዳዊት ወገን ለተመረጥሽ፤በመዝሙራትና በዜማዎች ክብር ለተሰጠሽ ለአንቺ ምስጋና ይገባሻል፤ጻድቁ ዳዊት ይህን አስመልክቶ ምስጋና አቅርቦልሻልና::»







ድንግል ማርያም በግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ ስትገለጥ የታዩ ልዩ ልዩ ምልክቶች ከ8/92000ዓ.ም. እስከ 15/10/2000 ዓ.ም.

## ሸ. ድንግል ማርያም አባ ገብርኤልን እንደረዳችው::

> «በመልካም የሚያስተዳድሩ ቀሳውስት ይልቁኑም በመስበክና በማስተማር የሚደክሙት እጥፍ ክብር ይገባቸዋል::» 1ኛ ጢሞ 5:17::

አባ ገብርኤል በታላቁ ጳጳስ የተገለጸው «ለሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን የቅብጥ ቤተ ክርስቲያን የቆመ የማማ መብራት!» ተብሎ ነው::

አባ ገብርኤል ክህነትን የተቀበለው እ.አ.አ. በ1955 ዓ.ም. ሲሆን ምንኩስናን የተቀበለው ደግሞ እ.አ.አ. በ1969 ዓ.ም. ነበር:: የሚታወቀው በትሕትናው ሲሆን ልቡም በእምነት የተሞላ ነበር:: ራሱን በመካድ ውስጥ



www.ethiopianorthodox.org

ለክርስቶስ ምስክር ሲሆን ድሆችንና የተቸገሩትን ለመርዳትም ከፍተኛ ፍቅር ነበረው።

የሚሠራው ሥራ ሁሉ የክህነትን መንፈስ ከመግለጡም በላይ ለቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ፍቅር ነበረው። ክህነትን ከመቀበሉ አስቀድሞ ሞህሞዲ (Mouhmoudy) ሾብራ (Shoubra) እና ቤኒ ማዛር (Beni Mazar) በተባሉት ሥፍራዎች ላይ በሚገኙ የድንግል ማርያም አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በስሟ ወላጅ አልባ የሆኑ ልጆችን ማሳደጊያ አቋቁሞ ነበር።

አባ ገብርኤል የጸሎትን ኃይል ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ስለ ነበርና ጸሎትን በሕይወቱ ውስጥ ከማንኛውም ነገር ጋር አቀናጅቶ የሚኀዝ ሰው ስለሆነ እግዚአብሔር አምላክ ከክፉ ነገሮች ሁሉ ይጠብቀው ነበር። አንድ ማስታወሻ ወይም ዶሴ ማንበብ ካለበት ከማንበቡ አስቀድሞ በላዩ ላይ በመስቀልያ ቅርጽ ያማትባል።

ለአንድ ሰው ምክር ወይም አስተያየት ከመስጠቱም በፊት ይጸልያል። እርሱ ጸሎት በጥራት እንጂ በብዛት መመዘን እንደሌለበት ያምናል። ከዚህ በተጨማሪ በጸሎት ወቅት በጥልቀት፣ በመረዳትና በእያንዳንዱ ቃል ላይ በተመስጦ መቆየት እንደሚገባም ያምናል። ጸሎት መልካም ይሆን ዘንድ ሰዎች ዐይኖቻቸውን መጨፈንና ስሜቶቻቸውን ጸጥ ማድረግ አለባቸው። አንድ ሰው ሲጸልይ በትሕትና፣ እጆቹን በመዘርጋት፣ ልቡን ወደ ላይ በማንሣትና ምንም ዓይነት ነገር ሳያውከው መሆን አለበት። በጸሎት ወቅት የእርሱ ጉዳይ እግዚአብሔር ብቻ ሊሆን ይገባዋል።

አባ ገብርኤል ለጸሎት ሲቆም የሚለብሰው ቀሚስ በጣም ምርጥ የሆነውን ነው። ስለዚህ ጉዳይ ሲናገርም፦ «ለጸሎት ስቆም በጣም ንፁሑንና ምርጡን ቀሚስ የምለብሰው የዓለሙ ሁሉ ጌታና የነገሥታት ሁሉ ንጉሥ የሆነው አምላክ ፊት ስለሆነ ነው።» ይል ነበር።

ወዳጅነቱ ብዛት ካላቸው ቅዱሳን ጋር በመሆኑ ደስተኛ ነው። ከእግዚአብሔር እናት ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር ያለው ወዳጅነት ደግሞ ከሁሉ ይልቃል። ገና ከሕፃንነቱ አንስቶ ነው በፍጹም ልቡ ይወዳት የነበረው። በጸሎቶቹ ውስጥ ዘወትር አማላጅነቷን እንደ እናትነቷ ይማጸን ስለ ነበር እርሷም በአማላጅነቷ ፈጥና ትደርስለት ነበር። አንድም ጊዜ ቢሆን ትታው አታውቅም።

አባ ገብርኤል በርኩሳን መናፍስት የተያዙትን ሰዎች የማስለቀቅ ኃይል ነበረው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፦ «ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤በስሜ አጋንንት ያወጣሉ፤. . .» ማር 16:17። በምዋርተኝነት ለጌቶቿ ብዙ ትርፍ ታስገኝ የነበረችውን ሴት ርኩስ መንፈስ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ያስወጣው





እንዲህ ብሎ ነበር፦ «ጳውሎስ ግን ተቸገረና ዘወር ብሎ መንፈሱን፦ ከእርሷ እንድትወጣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝሃለሁ አለው፤በዚያም ሰዓት ወጣ።» ሐዋ 16:18።



ድንግል ማርያም በግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ ስትገለጥ የታዩ ልዩ ልዩ ምልክቶች ከ8/9/2000ዓ.ም. እስከ 15/10/2000 ዓ.ም.

አባ ገብርኤል ርኩሳን መናፍስትን በተሰጠው ሥልጣን ያስወጣቸዋል እነርሱም ይታዘዙለት ነበር። ይህን ከማድረጉ አስቀድሞ የሚያደርገው ጥቂት የዳዊት መዝሙራትንና ጥቂት የክህነት ጸሎቶችን ነበር። እርሱ ርኩሳን መናፍስትን ያስወጣቸው የነበረው በእግዚአብሔር ኃይል፣ የብርሃን እናት በሆነችው በድንግል ማርያም አማላጅነትና በቅዱሳን



www.ethiopianorthodox.org

ሰዎች ሁሉ እርዳታ ነው። ይህ ዝናው በሰዎች ሁሉ ዘንድ የታወቀ ስለ ነበር ከግብጽና ከውጪ ሀገራት ወደ እርሱ ይጎርፉ ነበር።

ለአንዲት ወጣት ሴት በመጸለይ ላይ ሳለ በእርሷ ላይ የሰፈረው ርኩስ መንፈስ እርሱን ካልነካው ከእርሱ ጋር በወዳጅነት ሊቆይ እንደሚችል ለአባ ገብርኤል ቃል ይገባለታል። አባ ገብርኤልም ከት ብሎ ከሳቀበት በኋላ፡- «እኔና አንተ ወዳጆች ልንሆን የምንችለው እንዴት ነው? ይህ የሚሆን ነገር አይደለም። ድንግሊቱ ገርፋ ታስወጣሃለች!» አለው። ይህን ካለው በኋላም ድንግል ማርያምን እንዲህ ብሎ ጠየቃት፡- «ድንግል ሆይ፤ይህ ትክክል ነው? እንዴት ልጅሽን ከርኩስ መንፈስ ሠንሠለት በታች ትተያታለሽ? አቤቱ ጌታ ሆይ፤የአንተ ፈቃድ እንጂ የእኔ ፈቃድ አይሁን።» አለ።

በዚህ ጊዜ ርኩሱ መንፈስ ወዲያውኑ ጮኸና፡- «አንተ እንደ ጠየቅሃት ድንግሊቱ የቅዱሳን ሰዎችንና የመላእክትን ሠራዊት እየመራች በመምጣት ላይ ናት!» አለ። ከዚያም አባ ገብርኤል ዳግመኛ ልጅቱ ዘንድ እንዳይደርስ ቃል አስገብቶት ሲያበቃ ልጅቱን ትቶ ወጣ።

አባ ገብርኤልም በክፍሉ ውስጥ ተሰብስበው ለነበሩት ሰዎች እንዲህ አላቸው፡- «ርኩሱን መንፈስ ከልጅቱ ውስጥ ያስወጡት ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም ናቸው።»

### ቀ. ድንግል ማርያም፤ትቀበያታለሽ?

ካይሮ ውስጥ በሚገኝ በአንድ የደናግል ገዳም ውስጥ የምትኖር አንዲት እማሆይ ነበረች። ይህች እማሆይ እግዚአብሔርን በፍጹም ልቧ፣ በፍጹም አሳቧና በፍጹም ነፍሷ ትወደው ስለ ነበር ኑሮዋ ሁሉ ለእርሱ ነበር። እርሷ ከጠቢቡ ሰሎሞን ጋር እንዲህ እያች ትዘምር ነበር፡- «እኔ የውዴ ነኝ፤የእርሱም ምኞት ወደ እኔ ነው።» *መኃ 7:11*።

በላዕላይ ግብጽ ውስጥ ከነበሯት ቤተሰቦቿ፣ ጓደኞቿና ዘመዶቿ በመለየት ራሷን ከአንዱ ጌታ ጋር ብቻ አንድ አደረገች። ድንግላዊነትን በመምረጥም ለክርስቶስ በንጽሕና ለመኖር ወሰነች። ድንግል ማርያምንም እናቷና ዐቢይ ምሳሌዋ አደረገች።

የመልካም ነገር ሁሉ ጠላት የሆነው ዲያብሎስ ግን አልተዋትም። እፉኝቱ ዲያብሎስ መከላከያዋን ለማዳከም በእርሷ ላይ ይፋ ጦርነት አወጀ። ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር እርዳታ ስለ ተቋቋመችው ከእርሷ ሸሽቶ እስኪሄድ ድረስ አዋረደችው። የእማሆይዋ የኃይል ምንጭ እግዚአብሔር ሲሆን የተገኘውም በጸሎት ኃይል ነበር። ይህን ማድረግ





እንደምንችልም ይህ ቃል ኪዳን ከጌታችን ተሰጥቶናል፡- «እነሆ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፤ የሚጎዳችሁም ምንም የለም።» *ሉቃ 10:19*።

ዲያብሎስ ለሁለተኛ ጊዜ ወደዚህች እማሆይ ሲመጣ በሕክምና ጠበብቶች ዘንድ ሊታወቅ ባልቻለ ከባድ በሽታ ክፉኛ መታት። በመጨረሻም የቀዶ ጥገና ሕክምና ቢደረግላት አስፈላጊ መሆኑ ተወሰነ።

በዚህ ሕክምና የሚሻል እውቀትና ልምድ ያላቸው የሕክምና ጠበብቶች ወደሚገኙበት ወደ ካይሮ የቅብጥ ማዕከላዊ ሆስፒታል ተወሰደች። እንደ አጋጣሚ ሆኖ አንድ በጣም የታወቀ ነገር ግን በእግዚአብሔር የማያምን ዋና የቀዶ ጥገና ሕክምና ባለሙያ ናይሮ ውስጥ መሆኑ ታወቀ።

ቀዶ ጥገናው ነገ ሊከናወን እንደ ዛሬ ሌሊት እማሆይዋ የማያቋርጥ ዕንባዋን ታፈስ ጀመር። በልቅሶዋም መካከል በሰቆቃ ድምፅ እንዲህ ስትል ነበር፡- «ሕይወቴን፣ ሥጋዬንና ነፍሴን ለእግዚአብሔር ከሰጠሁ በኋላ እንዴት እንዲህ ዓይነት ነገር ሊገጥመኝ ቻለ? ገላዬ በእግዚአብሔር በማያምን በአንድ ሐኪም እጅ እንዴት ይገለጣል? ቅድስት እናቴ ሆይ፤ እንዴት ይህ እንዲሆን ትፈቅጂያቀሽ?»

እማሆይዋ ይህን ተናግራ ከትራስዋ ሥር ያለውን መሀረብ ለማውጣት ዘወር ስትል ከአልጋዋ አጠገብ ካለው የድንግል ማርያም ሥዕል ውስጥ ድንቅ ብርሃን ሲፈነጥቅ ተመለከተች። ብርሃኑ የሙሉ ሰውነት መጠን እስኪይዝ ድረስ እየሰፋ መጣ። አሁን ድንግል ማርያም ከእማሆይዋ አጠገብ ቆማ፡- «የተከበርሽው እናት ሆይ፤ለምንድር ነው የምታዝኚብኝ? የቀዶ ጥገናውን ሕክምና የማከናውነው እኮ እኔ ነኝ። አሁን አጠገባችን ምንም ሰው ስለሌለ ቀዶ ጥገናውን ማካሄድ እንችላለን።» አለቻት። ከዚያም ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ «ቀዶ ጥገናው ተከናውኗል። በየሁለቱ ቀን እየመጣሁ ፋሻዎቹን እቀይርሻለሁ።» ብላ አሳሰበቻት።



www.ethiopianorthodox.org



ድንግል ማርያም በግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ ስትገለጥ የታዩ ልዩ ልዩ ምልክቶች ከ8/92000ዓ.ም. ኘ 15/10/2000 ዓ.ም.

በሚቀጥለው ቀን ጠዋት መነኩሲቷ ከእንቅልፏ ስትነቃ በእውነትም ቀዶ ጥገና እንደ ተደረገላት ትመለከታለች:: ነርሷ ወደ ቀዶ ሕክምና ክፍል ልትወስዳት ስትመጣ እማይሆዋ «እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁንና ቀዶ ጥገናው ተከናውኗል::» አለቻት::

የሕክምና ባለሙያዎቹ ቀዶ ጥገናው በትክክል መከናወኑን ሲመለከቱ እጅግ ተደነቁ:: በዚህ ሆስፒታል ውስጥ ሌሎች ሐኪሞች አሉ እንዴ? እዚህ ክፍል ውስጥ ቀዶ ጥገና እንዲያደርጉ የፈቀደላቸውስ ማነው? ብለው ጠየቁ:: ቀዶ ጥገናውን ያካሄደችው ቅድስት ድንግል ማርያም መሆኗን ሲሰሙ ጉዳዩን ተረዱ::





ቀዶ ጥገናውን ሊያካሂድ የታጨው ሐኪም የተከሰተውን ጉዳይ ሲሰማ አንዲት ቃል እንኳ አልተነፈሰም:: ይልቁንም ይህን ጉዳይ ከሥራ ባልደረቦቹ ሊያደምጥ ኢ-አማኒነቱ ተናወጠ፤የተከሰተው ተአምር የፈጣሪያችንን ኃይል ገልጦ አሳይቶአልና:: የሰው ልጆች ሁሉ አማላጅ የሆነችው የእግዚአብሔር እናት ጸሎት ዋጋ እንዳለውም ተገልጦአል::



ድንግል ማርያም በግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ ስትገለጥ የታዩ ልዩ ልዩ ምልክቶች ከ8/92000ዓ.ም. እስከ 15/10/2000 ዓ.ም.



www.ethiopianorthodox.org

**በ. የገዳሙ እድገት::**

> «እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ ሠራተኞች በከንቱ ይደክማሉ፤እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ ጠባቂ በከንቱ ይተጋል::» መዝ 126:1::

ራምሴ (Ramsey) ከሃይማኖተኛ ክርስቲያኖች የተገኘ ስለሆነ በድቁና ያገለግል ነበር:: እ.አ.አ. በ1936 ዓ.ም. ከፍተኛ ትምህቱን ሲያጠናቅቅ ወደ ጊዛ (Giza) ሄዶ ሥራ ተቀጠረ:: እርሱ እዚህ ቦታ ላይ ከአባ ሚና ኤል ባራሞሲ (Father Mina El Baramosi) ወይም ከአቡነ ቄርሎስ 6ኛ (Pope Kyrollos The Sixth) ጋር አገልግሏል::

እ.አ.አ. በ1939 ዓ.ም. አባ ሚና ተብሎ ምንኩስናን ተቀበለ:: ይኼኛውን አባ ሚና ከሌላኛው አባ ሚና ኤል ባራሞሲ (Father Mina El Baramosi) ጋር ለመለየት እንችል ዘንድ «ታናሹ አባ ሚና» ብለን ነው የምንጠራው:: ታናሹ አባ ሚና በ1945 ዓ.ም. በአባ ሳሙኤል ገዳም ውስጥ አገልግሏል:: ገዳሙ ከምንም ጥሬ ሀብትና ከጥቂት ያረጁና ለመሥራት አቅም ከሌላቸው መነኮሳት በስተቀር አንዳችም ነገር የሌለው በጣም ድሀ ገዳም ነበር::

ታናሹ አባ ሚና የተሰጠውን ኃላፊነት የተቀበለው በፍቅር፣ በትዕግሥትና በእምነት ነበር:: እርሱ በአቅራቢያው ወደሚገኙ መንደሮች በትጋት እየሄደ የሚሰጡትን ማንኛውንም ዓይነት እርዳታ በመሰብሰብ ለራሱና ለመነኮሳቱ ያከፋፍል ነበር:: ነፍሳቸውን ያቆየው ይህን በመሰለ መንገድ ነው::

እርሱ ይህን ያድርግ እንጂ በየዕለቱ ገዳሙ የሚበለጽግበትን መንገድ ያገኝ ዘንድ ድንግል ማርያምን አጥብቆ ይለምናት ነበር:: ከዕለታት አንድ ቀን በበረሀው ውስጥ ሲጓዝ ሦስት መስቀሎችን በሰማይ ላይ ተመለከተ:- አንዱ ወርቅማ፤አንዱ ቀይ፤አንዱ ደግሞ ነጭ:: ወርቅማውን መስቀል በገዳሙ ውስጥ ያለፋትን ወርቃማ ዘመናት የሚወክል አድርጎ ወሰደው፤ቀዩ ገዳሙ አሁን ያለበትን የውድቀት ዘመናት አድርጎ መሰደው፤ነጩ በድንግል ማርያም አማላጅነት በገዳሙ ውስጥ የሚመጣውን የሰላምና የብልጽግና ዘመን አድርጎ ወሰደው::

ታናሹ አባ ሚና በዚህ ገዳም ውስጥ የበላይ ኃላፊ ሆኖ የቆየው ለአርባ ዓመታት ነበር:: ብዙ ፈተናዎች ቢገጥሙትም እንኳ ታላቅ ትዕግሥትና ጽናት በእርሱ ዘንድ ነበሩ:: አዘውትሮም «ማድረግ ያለብኝ ነገር ቢኖር መጸለይ ብቻ ነው፤መልካም የሆነውን መመልከት





የእግዚአብሔር ፈንታ ነው::» ይል ነበር:: በእርግጥም ገዳሙ ከውስጥም ሆነ ከውጭ ይበለጽግ ጀመር:: የፈራረሱት ሕንጻዎች በድጋሚ ተገነቡ፤የአትክልቱና የእህሉ ስፍራዎችም ተመልሰው ያብቡ ጀመር:: ሌሎች ተጨማሪ ሕንጻዎች ተገነቡ አዳዲስ የሥራ መሣሪያዎችም ተገዙ::

ብዛት ያላቸው መነኮሳት በገዳሙ ውስጥ ክህነት ተቀበሉ:: ፈገግታ በማይለየው በታናሹ አባ ሚና ገጽታ ውስጥ የአባትነት ስሜትና የብሕትውና ጥቅም ታላቅ መሆኑ ዘወትር ይነበብ ነበር::

«እሹቱን ለሚያጠጣ ለይስሐቅ የምንጭ መገኛ ምስጋና ይገባል:: በብትሕውና ዓለም ላይ ከፍ ብላ ለምትወጣው ድንቅ ፀሐይም ምስጋና ይገባል::»

**ተ. ድንግል ማርያም በስጦታ ከተማ::**

እ.አ.አ. ከ1900-1961 ዓ.ም. ድረስ የኖረው ዲያቆን ራጌብ እስክንድር (Deacon Ragheb Iskander) አል አጎዛ (Al Agouza)፤አል ዶኪ (Al Doky)፤አል ጋማ (Al Gamaa) የተባሉትንና ሌሎች የአካባቢውን መንደሮች የሚያገለግል የእግዚአብሔር ሰው ነበር:: ይህ ሰው ግሩም ጠባይ ያለው ከመሆኑም በላይ የውስጥ ሰላም፣ የተግባራዊ ፍቅር፣ የታላቅ እምነትና አገልግሎት ምሳሌ ነበር::

ለዚህ ሰው እግዚአብሔር ዘር አልሰጠውም ነበር:: ይሁን እንጂ በእርሱና በሚስቱ ላይ ምንም ዓይነት ኀዘን አልነበረም:: እንዲያውም በተቃራኒው ይህ በመሆኑ እግዚአብሔርን በስፋት ለማገልገል ዕድሉን ከፍቶላቸዋልና ደስተኞች ነበሩ::

ራጌብ እስክንድር በጸሎት ኃይል አጥብቆ ያምን ነበር:: ማንኛውም ስብሰባ ከመካሄዱ በፊት እግዚአብሔር እርዳታውንና ጥበቡን እንዲያድለው በድንግል ማርያም አማላጅነት ይጠይቀው ነበር:: በሌሎች ሰዎች አማካይነት የሚሰነዘሩ ችግሮች አያስጨንቁትም፤በጸሎት ኃይል ለሁሉም መፍትሔ እንደሚገኝላቸው ዘወትር ያምናልና::

እርሱ በኖረባቸው ዘመናት ውስጥ ዛሬ ከምንመለከታቸው አብያተ ክርስቲያናት መንከል ብዙዎቹ አልተገነቡም ነበር:: ዶኪ መንደር ውስጥ አል አውቃፍ (Al Awkaf) ተብላ በምትጠራ ቦታ ላይ 665 ካሬ ሜትር የሚደርስ ባዶ ስፍራ እንዳለ ተመለከተ:: ዐይኑ እንዳመለከተው በዚህ ቦታ ላይ የእግዚአብሔርን ቤት ለመገንባት አለመ:: አንዳንድ ጊዜ ወጣቶችን ወደዚህ ቦታ በቡድን በመውሰድ በቦታው ላይ እንዲጸልዩ ያደርጋቸው ነበር::



www.ethiopianorthodox.org

በዙሪያው ያሉ ሰዎች ሕልሙ ከከንቱ ቅዠት የማያልፍ አድርገው ቢያስቡም በቦታው ላይ ተአምር ተፈጠረ። በትንሽ ጉባኤ መልክ የተሰባሰቡት ሰዎች ገንዘባቸው ወደ 800 ብር ሲጠጋ መሬቱ በሌሎች ሰዎች ተገዛ።

መሬቱን የገዛው ሃይማኖት የሌለው የሕክምና ባለሙያ ነበር። ከዚህ በኋላ መሬቱን ለጉባኤው አባላት ለመሸጥ ስምምነት ገባ። በተመሳሳይ ሰዓት የጉባኤው አባላት መሬቱን ሊገዙበት ያሰባሰቡትን ገንዘብ ሦስት እጥፍ የሚያህል ገንዘብ ከሌሎች ሰዎች ቀረበለት። ሐኪሙ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ጥቂት ቀናት እንደሚያስፈልገው ተናግሮ ወደ ቤቱ ተመለሰ።

የዚያን ዕለት ሌሊት ሐኪሙ የድንግል ማርያምን ሁለት መገለጦች ይመለከታል። ከዚህ በኋላ እርሱና ሚስቱ በጉዳዩ ላይ ተወያይተው ሲያበቁ መሬቱን ለጉባኤው አባላት በየወሩ በካሬ ሜትር 30 ብር ወለድ በማስከፈል ለመሸጥ ይስማማሉ።

በብርሃን እናት ምልጃ አማካይነት እግዚአብሔር ቅድሚያ ክፍያውን በሌላ ጉባኤ እንዲሸፈን ያደርጋል። ከዚህ በተጨማሪ ራጌብ የጡረታ ገንዘቡን፤ቆጥቦ ያስቀመጠውን ገንዘብና ኢምባባ (Imbaba) ውስጥ ያለ ቤቱን የሸጠበትን ገንዘብ ሰብስቦ አመጣ። ከዚህ በኋላ ወለዱ ለአንድ ዓመት ያህል በየወሩ ተከፍሎ ተጠናቀቀ። ባለ መሬቱ የመጨረሻውን ወር የወለድ ክፍያ ስለ ድንግል ማርያም ስል አልወስድም ይላል።

ራጌብና አንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የአዲሱን ቤተ ክርስቲያን ፕላን ከሚነድፈው ባለሙያ (architect) ጋር በቤቱ ሊገናኙ ቀጠሮ ይይዛሉ። ባለሙያው ቤት ሲደርሱ ግን በቤቱ ውስጥ የለም። ይሁን እንጂ በአቅራቢያው በሚገኝ በአንድ የክርስቲያን ሸቀጣ ሸቀጥ መጋዘን ውስጥ ስለ ነበር እዚያው ድረስ ሄደው አገኙት። ክርስቲያኑ ነጋዴ ሲሠራ ስለታቀደው ፕሮጀክት ሲሰማ ክርስቲያኖች ወደ ሆኑ ጎረቤቶቹ በመሄድ አራት ሺህ ብር ሰብስቦ ይመለሳል። በዚያን ዘመን ይህ በጣም ብዙ ገንዘብ ነበር። በዚህ ጊዜ ራጌብ ወደ አገልጋይ ባልንጀራው ዞሮ ብሎ «ለእግዚአብሔር ሥራና ለድንግል ማርያም አማላጅነት ምስክሮች ሆነናል።» አለው።

«ወይንና የወይን አትክልት እርሻ የሆንሽው ድንግል ማርያም ሆይ፤ምስጋና ይገባሻል። ቅርንጫፎቿ አብበው የወይን ፍሬ ያፈራሉ። እርሷ የጥበብ፣ የጥልቅ መረዳትና የክብር መገኛ ናት።»

ቸ. ድንግል ማርያምና አባ ስምዖን።

«እነሆም በኢየሩሳሌም ስምዖን የሚባል ሰው ነበረ፤ይህም ሰው የኢየሩሳሌምን መጽናናት ይጠባበቅ ነበር፤ጻድቅና



www.ethiopianorthodox.org



ትጉህም ነበረ፤መንፈስ ቅዱስም በእርሱ ላይ ነበረ።» ሉቃ 2:25።

እ.አ.አ. ከ1920-2000 ዓ.ም. ድረስ የኖረው አባ ስምዖን አርማኔዎስ (Fr. Simeon Armanious) የተወለደው ሉቅሶር (Luxor) በምትባል መንደር ሲሆን የመጀመሪያ ስሙም ናሲፍ (Nasif) ይባል ነበር። ከታላቅ እኅቱ ሞት በኋላ እጅግ ስላዘነ እርሷ የትም ትሁን የት በሞት ተከትሏት ቢሄድ እንደሚመርጥ ያሰላስል ነበር። ይህን እንጂ ታላቅ እኅቱ ከድንግል ማርያም ጋር ተገልጣ ናሲፍ ልቅሶውን እንዲያቆም ትጠይቀዋለች። ይህችው እኅቱ ከማልቀስ ይልቅ እርሷን ወደፊት ለጻድቃንና ለቅዱሳን ሰዎች በተዘጋጀው በመንግሥተ ሰማያት ያገኛት ዘንድ በዚህ ምድር ላይ መከራ መቀበል እንደሚገባው ትነግረዋለች።

ከዚህ በኋላ ናሲፍ ዓላማውና ግቡ እግዚአብሔር ከቅዱሳኑ ጋር የሚኖርባትን ሰማያዊ መንግሥት መውረስ መሆኑን ገና ከልጅነቱ አንስቶ አወቀ። በመሆኑም በሕይወት ዘመኑ ሙሉ ሥራው ነፍሱ ከሥጋው የምትላቀቅበትን አርነት መናፈቅና እዚህ ስፍራ ለመግባት የሚያስችለውን ዝግጅት ማከናወን ሆነ።

ወጣት እንደ መሆኑ ሾብራ-ካይሮ (Shoubra-Cairo) ውስጥ ከመጀመሪያዎቹ የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪዎች ጋር አገልግሏል። ከእነዚህም መካከል ናዚር ጋይድ (Nazir Gayed) የአሁኑ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ፤መሐንዲስ አሚን ናስር (Engineer Amin Nasr) የአሁኑ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አርሳኔዎስ (His Grace Bishop Arsanious) እና ራምሴ አዙዝ (Ramsey Azouz) የአሁኑ ጳጳስ አቡነ ዮሐንስ ይገኙበታል።

ይህ ሰው ታንታ (Tanta) ላይ የሚገኝ ሕክምና አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ውስጥ ይሠራ የነበረና በዚያው አካባቢ በሚገኝ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያገለግል የነበረ ሰው ነው። ናሲፍ በዚያ ሳለ የአገልግሎት ትኩረቱን ያነጣጠረው በወጣቶችና በመንደሩ ላይ ነበር። የወጣቶቹን ቤቶች በየጊዜው ይጎበኝ ስለ ነበር በማኅበረሰቡ ላይ ድንቅ ተጽዕኖ አሳድሮ ነበር።

ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ተቃውሞዎች ይገጥሙት ነበር። በአንድ ወቅት አንድ ወጣት ድምፁን ከፍ አድርጎ በመጮኸ «ሥራ የለህም እንዴ? በየጊዜው እየመጣህ የወጣቶች ቡድን-የወጣቶች ቡድን እያልህ ግራ የምታጋባን ለምንድር ነው?» ብሎት ነበር።

ናሲፍ ለዚህ ወጣት የመለሰለት የትሕትና መልስ እንዲህ የሚል ነበር:- «ወደዚህ የመጣነው አንተን ወደ ክርስቶስ ለመምራት ነው::» ይህን ቢለውም ወጣቱ አሁንም ድምፁን ከፍ አድርጎ መጮኹን አላቋረጠም:: በዚህ ጊዜ ናሲፍ በቅብጥ ቋንቋ «ኬይን ኢቭራን» (Khein Evran) አለው፤ትርጓሜውም «እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሁን::» ማለት ነው:: ይህን ተናግሮ በፍቅር ወደሚቀበሉት ወጣቶች ከመሄዱ በፊት ግን ወጣቱ ወዳቀበት አቅጣጫ በመስቀልያ ቅርጽ አማተበ::

የሚቀጥለው ቀን ጠዋት ላይ ወጣቱ ናሲፍን እየፈለገ ቤተ ክርስቲያን ድረስ መጣ:: እንዳገኘውም:- «ትናንትና ማታ እንቅልፍ ሊወስደኝ አልቻለም:: ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እኔ መጥቶ 'ለምንድር ነው አገልጋዮቼን የምትቃወመው?' ብሎ ጠየቀኝ:: እባክህ አቶ ናሲፍ፤ይቅር በለኝ::» አለው::

ናሲፍ ጡረታ ከወጣ በኋላ የቅስና ክህነት ተቀብሎ እግዚአብሔርን ያገለግል ጀመር:: ታንታ ውስጥ ለሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ኃላፊ በመሆን ለሃያ ዓመታት አገለገለ:: በአንድ ወቅት «ጌታ ሆይ፤አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ፤ዐይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና፤. . .» (ሉቃ 2:29-30) ብሎ የተናገረው የአረጋዊው ስምዖን ስም ተሰጠው::

ከዚህ በኋላ ትኩረቱን ያዞረው አስታዋሽ ወዳጡት፣ ወደ ድሆች፣ ወደ እስረኞችና ወደ ተራቆቱት ሰዎች ነበር:: በእስር ቤቶች ውስጥ ማብቂያ ስለሌለው ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ቸርነት ይሰብክል:: እጅግ መልካም ልብ ስለ ነበረው ሰዎች ሁሉ ይወዱት ነበር:: ብዙ እስረኞችን ከጨለማ ክፍላቸው ውስጥ ነጻ አውጥቷል:: በድንግል ማርያም አማላጅነትና በእግዚአብሔር ሥራ ሦስት እስረኞች ወደ ክርስትና እምነት ገብተዋል::

ከዕለታት አንድ ቀን ከመንፈስ ቅዱስ ልጆቹ አንዱን ለመጠየቅ ወደ ቤቱ ሲሄድ ከደረጃዎች ላይ ስለ ወደቀ ጭንቅላቱና ጀርባው ክፉኛ ተመታ:: በዙሪያው የነበሩ ሰዎች ዕድሜው የገፋና አወዳደቁ ከባድ መሆኑን ስለ ተመለከቱ በጣም አዘኑለት፤ከባድ ጉዳት ይደርስበታል ብለውም አሰቡ::

ሰዎቹ «ተርፏል?» ብለው ሲጠይቁት እንዲህ እያለ ይመልስላቸው ነበር:- «አትጨነቁ! ልክ እንዳደናቀፈኝ ድንግል ማርያም እጆቿን ዘርግታ ስለ ተቀበለችኝ ደረጃዎቹ አልመቱኝም::» ምንም ዓይነት ጉዳት እንዳልደረሰበት ሊያረጋግጥላቸው ስለፈለገም እያዩት ተነሥቶ በመራመድ ወደ ጉዳዩ ሄደ::





«ከአደጋ ልትታደገው የመጣችው ድንግል ማርያም የተመሰገነች ትሁን:: የተከበርኸው ቄስ ስምዖን ሆይ፤በደስታ መንፈስ መጥተህ ሕፃኑን አማኑኤል ታቀፈው:: ድንግል ሆይ፤ለአንቺም ምስጋና ይገባሻል::»

**ጎ. የጠፋችውን ልጃገረድ ድንግል እንደመለሰቻት::**

> **«በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ:: አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል::» ፊልጵ 4:6-7::**

እ.አ.አ. ከ1937-1987 ዓ.ም. ድረስ የኖረውና ፋዮም (Fayoum) በሚገኘው በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያገለግል የነበረው አባ ሳሊብ ሪስጋላ (Fr. Salib Risgalla) ሌሎች ሰዎችን በፍቅር በማገልገሉ ለሰዎች ሁሉ ምሳሌ ሲሆን የበቃ ሰው ነበር::

«ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን፤እንደሚታረዱ በጎች ተቆጠርን፤ . . .» ሮሜ 8:36::

አባ ሳሊብ ካህን እንደ መሆኑ ማናቸውንም መመሪያዎች ጠብቆ ይኖር ነበር እንጂ ከአንዳቸውም አላፈነገጠም::

ለምሳሌ:-

❖ መከራዎች ሁሉ ከእግዚአብሔር ወደ እርሱ የሚላኩት ለድኅነት ስለሆነ በአርምሞ ይቀበላቸዋል:: ይህን ተግባራዊ የሚያደርገውም የቅዱስ ጴጥሮስን ቃል በመከተል ነው:- «ኃጢአት አድርጋችሁ ስትጎሰሙ ብትታገሡ ምን ክብር አለበት? ነገር ግን መካንም አድርጋችሁ መከራን ስትቀበሉ ብትታገሡ ይህ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋና ይገባዋል:: የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራ ተቀብሎአልና::» 1ኛ ጴጥ 2:20-21::

❖ ምንም ዓይነት ነገር ሲያስፈልገው ሰዎችን በጭራሽ አይጠይቅም፤እግዚአብሔርን ብቻ እንጂ:: «ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ::» ዮሐ 14:14::

❖ ጸሎትን የሚጠቀመው ችግሮችን ለማቃለል ብቻ ነው፤ይህን የሚያደርገውም በጌታ ቅዳሴ ጊዜ ነው:: እርሱ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ



www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ማንኛውንም ዓይነት ችግር እንደሚያቃልል ያውቃል::

አባ ሳሊብ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በመከታተል ላይ ሳለ ነው በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ ማገልገል የጀመረው:: ከዕለታት አንድ ቀን አንዲት ልጃገረድ ከሰንበት ትምህርት ቤት ወደ ቤቷ ስትመለስ መንገድ ትስትና ትጠፋለች:: የልጅቷ አባት ሰንበት ትምህርት ቤት ትሆናለች ብለው እዚያው ድረስ ሄዱ:: በአገልጋዮቹ ስለ ተበሳጩም በቁጣ ቃል አስፈራሯቸው ዛቱባቸውም:: በዚህ ጊዜም አባ ሳሊብ ለችግሩ ሁነኛ መፍትሔ ሊሆን የሚችለው ጸሎት ብቻ መሆኑን አረጋገጠ:: ከዚህ በኋላም ልጅቱ ወደ ቤቷ በሰላም ትመለስ ዘንድ በድንግል ማርያም አማላጅነት እግዚአብሔርን ተማጸነ::

ጸሎታቸውን እንደ ጨረሱ ልጅቱን ለመፈለግ ከነበሩበት ክፍል ሲወጡ ፊት ለፊታቸው ቆማ ተመለከቷት:: የት ገብታ እንደ ነበር ሲጠይቋትም መንገዱ ስለ ጠፋባት ቆማ ስታለቅስ የዕጣን መዓዛ ያላት አንዲት ውብ ሴት ሙሉ ነጭ ቀሚስ ለብሳ እንደተገለጠችላትና እጇን ይዛ ወደዚህ ስፍራ እንደ መለሰቻት ተናገረች::

በዚህ ጊዜ የሰንበት ትምህርት ቤቱ አገልጋዮች እግዚአብሔርን አከበሩ፤ድንግል ማርያምንም አመሰገኗት:: ልጅቱን ወደ ወላጆቿ ወስደው ሲያስረክቡ አባቷ ቀደም ሲል ስለ ገለጡት ቁጣ ይቅርታ ጠየቋቸው:: ሁሉም አንድ ላይ ተሰብስበው ከቆሙ በኋላ ይህን የምስጋና ቃል አቀረቡ:- «የእውነተኛው ብርሃን እናት የሆንሽው ድንግል ማርያም ሆይ፤የዓለሙን ሁሉ ጌታ ወደኛ ስላመጣሽልን እናመሰግንሻለን::»

## ነ. የአባ ሚካኤል ሕይወት::

እ.አ.አ. ከ1899-1975 ዓ.ም. ድረስ የኖረው አባ ሚካኤል ኢብራሂም (Fr. Michael Ibrahim) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን የተከታተለው ቁስና (Quesna) ውስጥ በሚገኘው የቅብጥ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን የተከታተለው ደግሞ ካይሮ ውስጥ በሚገኘው የቅብጥ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ነው:: ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ አገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ በሚገኝ የአስተዳደር ክፍል ውስጥ ተቀጥሮ ይሠራ ጀመር::

ሥራው ባደረሰው ስፍራ ሁሉ የክርስቲያኖችን ኅብረት በማቋቋም አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን እንዲቋቋሙ ይረዳ ነበር:: ታማኝ ሠራተኛ በመሆኑም ብዙዎች ከእርሱ ምክርና መመሪያ ለመቀበል ወደ እርሱ ይሄዱ ነበር:: ሥነ ሥርዓቱ፣ ርኅራኄውና ንጽሕናው ለሰው ሁሉ የሚነበቡ መጻሕፍቱ ነበሩ::





አባ ሚካኤል ክህነት ከመቀበሉ በፊትም ሆነ በኋላ በመስቀለ ምልክት አጥብቆ የሚያምን ሰው ነበር:: እርሱ በመስቀልያ የሚያማትበው በሁሉም ነገር ላይ ነው፤በምግቡ፣ በመጠጡ፣ በወንበሩና በፋይሎቹ ሁሉ ላይ:: ስልክ ሊያነሣ ሲል እንኳ «በመስቀሉ ኃይል ይሁን!» ብሎ ነው የሚያነሣው::

በሥራ ላይ ቢሆንም ወደ መንደሯ ፖሊስ አዛዥ ቢሮ ሲገባ በትዕምርተ መስቀል አማትቦ ነው:: በእግዚአብሔር ላይ ያለውን ብርቱ እምነት አጠናክሮ እንዲቀጥልም ልዩ ልዩ ማበረታቻዎች ይደርሱት ነበር:: ይሁን እንጂ የቀድሞው ፖሊስ አዛዥ ወደ ሌላ መንደር ተዘዋውሮ በምትኩ አዲስ አዛዥ ሲመጣ ችግር ፈጠረበት:: አባ ሚካኤል ወደ ፖሊስ አዛዡ ቢሮ ሲገባ በመስቀል ቅርጽ አማትቦ እንዳይገባ ተከለከለ:: ታላቅ ስሕተት እንዲፈጽምም ታላላቅ ኃላፊነቶችን ደራርቦ አሸከመው:: ይህን በማድረጉም ከዕለታት በአንዱ ቀን ስሕተት ሲፈጽም እርሱ ራሱ መርምሮ ከቢሮው ሊያባርረው ተስፋ በማድረግ ይጠባበቀው ጀመር::

በዚህ መካከል ግን የፖሊስ አዛዡ ብቸኛ ልጅ ክፉኛ ታመመ:: ሚስቱም በሕልሟ አንዲት የሚያብረቀርቅ ቀሚስ የለበሰች ሴት «ሚካኤልን በመቃወም የተነሣሽው ለምንድር ነው?» ብላ ስትጠይቃት ተመለከተች:: ወዲያውኑ ከእንቅልፏ በድንጋጤ በመነሣት ባሏን ቀሰቀሰችውና ሚካኤል ማን እንደ ሆነና ለምን መከራው እንደበዛበት ትጠይቀዋለች:: ፖሊስ አዛዡ በውድቅት ሌሊት ይህን ከሚስቱ ሲሰማ ሚካኤልን ጠርቶ ይቅርታ ከጠየቀው በኋላ ለታመመ ልጁ ይጸልይለት ዘንድ ተማጸነው:: ወዲያውም ሚካኤል በልጁ ራስጌ ቆሞ ሲጸልይ ፖሊሱ ተመለከተው:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ልጁ ከተኛበት አልጋ ላይ በእግዚአብሔር ኃይልና በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ተነሥቶ በመቆም እግዚአብሔርንና ቅዱሳኑን አመሰገነ::

አባ ሚካኤል ምንኩስናን የተቀበለው እ.አ.አ. በ1951 ዓ.ም. ነው:: አባ ሚንኤል ምንኩስናን ከተቀበለ በኋላ የመጀመሪያዎቹን አርባ ቀናት ያሳለፈው በፍጹም ጸሎትና ተመስጦ ነበር:: በእነዚህ ቀናት ውስጥ ድንግሊቱ በርግብ ተመስላ ወደ ክፍሉ ስትገባና ከክፍሉ ስትወጣ ትታይ ነበር::

ለመጀመሪያ ጊዜ በምንኩስና ያገለገለው በተወለደባት መንደር በቃፍር አብዱ (Kafr Abdou) በምትገኘው የእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው:: እርሱ የየዕለቱን ጸሎት ስለሚያደርስ፣ መንፈሳዊ ጉባኤ ስለሚያዘጋጅ፣ ለወጣቶች መመሪያ ስለሚሰጥና ስለሚከታተል፣ ቤተሰቦችንም በየጊዜው ስለሚጠይቅ የክህነት ሹመቱ ለቤተ ክርስቲያኗ ታላቅ በረከት ነበር:: በአካባቢው የሚገኙ መንደሮችንም በአገልግሎቱ



www.ethiopianorthodox.org

ውስጥ ይኅበኛቸው ነበር:: እ.አ.አ. ከ1956 ዓ.ም. በኋላ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ያገለገለው ሾብራ (Shoubra) ውስጥ በምትገኘው በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነበር::

**ኘ. ድንግል ማርያም በአቡ ዛቢ (Abou Zaby)::**

> **«አቤቱ:- ረድኤቴ መድኃኒቴም፤የአፌ ቃልና የልቤ አሳብ በፊትህ ያማረ ይሁን::» መዝ 18:14::**

በአረብ ሰላጤ ውስጥ ከሚገኙት አገሮች መካከል አቡ ዛቢ (Abou Zaby) በሀብቷ የምትታወቅ ሀገር ስለ ሆነች የውጪ አገር ሠራተኞችን ወደ እርሷ ትስብ ነበር:: የቅብጥ ማኅበረሰብና ቤተ ክርስቲያን በታማኝነታቸው የታወቁ ስለሆኑ በሀገሪቱ መስፍንና በመላው ሕዝብ ዘንድ የተከበሩ ናቸው::

በዚሁ አገር የሚኖር አንድ ቅብጣዊ መሐንዲስ ሚስቱና የአንድ ዓመት ልጁ ከእርሱ ጋር ይቀመጡ ዘንድ ይጠራቸዋል:: ሚስቱና ልጁ ወደ እርሱ ከመጡ ከጥቂት ቀናት በኋላ ግን የሚስቱ የሰውነቷ የቀኝ ጎን የማይታዘዝ ይሆናል:: ባሏን ልትጠራው ብትሞክርም አንዲት ቃል እንኳ ማውጣት ይሳናታል::

ብዙ ሳይቆይ እጅግ ዘመናዊ የሆኑ የሕክምና መሣሪያዎች ወደ ተገጠመለትና ከዓለም ዙሪያ የተሰባሰቡ የታወቁ የሕክምና ባለሙያዎች ወደሚገኙበት ወደ አቡ ዛቢ ማዕከላዊ ሆስፒታል (Abou Zaby Central Hospital) ለሕክምና ተወሰደች:: ሐኪሞቹም በአንጎሏ ላይ ደም መርጋቱን አረጋገጡ::

የመሐንዲሱ ሚስት በቀን ውስጥ ረዥም ሰዓቷን የምታሳልፈው የሰዓታቱን የጸሎት መጽሐፍ በመድገምና ድንግል ማርያም ለባሏና ለልጇ ስትል ከልጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እንድታማልዳት በመማጸን ነበር::

በታወቁት የሕክምና ባለሙያዎች ዘንድ ከቀረቡት የምርመራ ውጤቶች መካከል አንዱ አቅላሚ ራጂ (Dye X-ray) እንድትነሳ የሚጠይቅ ነበር:: ይህ ሊከናወን የሚችለው ደግሞ በስተግራ በኩል አንገቷ ላይ በሚሰጥ የውስጠ አከርካሬ (Inter-vertebral) መርፌ ነው:: ሴቲቱ እዚህ አደገኛ ሕክምና ውስጥ እንዳትገባ ድንግል ማርያም በመካከል ትገኝ ዘንድ አጥብቃ ጠየቀቻት:: ይህችው ሴት የጸለየቻው ጸሎት ሳይታወቅ ሕክምናው በተራው ራጂ እንዲከናወን ይወሰናል:: ከአንድ ወር የሕክምና ክትትል በኋላ በሰውነቷ ላይ ጥቂት ለውጥ ታየ:: ጥቂት ቆይቶም ከባድ ሕመም





ስለ ተሰማት የመዳን ጉጉቷ ጨመረ:: ስለሆነም ድንግሊቷና ርኅርኂቷ እናት በተባረኩ እጆቿ ትዳስሳት ዘንድ ትለምናት ጀመር:: ይህንኑ ጸሎት ደግማ በመጸለይ ፊቷንና መላ ሰውነቷን በትዕምርተ መስቀል አማተበች:: ከዚህ በኋላ ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወሰዳት:: ከጥቂት ቆይታ በኋላ አንድ ነገር ቀኝ ክንዷን በስሱ ሲዳስሳት ተሰማት:: ዘወር ብላ ስትመለከትም የድንግል ማርያምን አንጸባራቂ ገጽታ ትመለከታለች:: ከመቅጽበት ከተኛችበት መኝታ ላይ ተነሥታ የቀረበላትን በረከት ከሙሉ ጤና ጋር ተቀበለች::

ሴቲቱ የተመለከተችውን ተአምር ትመሰክርለት ዘንድ ባሏን ጠራችው:: እንደ ደረሰም የሕክምና ባለሙያዎቹ ቡድን ዙሪያዋን ከብቦ ድንገት ስላመጣችው ሙሉ የጤና ለውጥ በመደነቅ ሲወያይ ተመለከተ:: «አልትራ ሳውንድ» እንድትነሣ ቢያዝዙም የተነሳው ምስል ምንም ዓይነት የደም መርጋት ሲያመለክት አልቻለም:: ከዚህ በኋላ ሐኪሞቹ የሰጡት አስተያየት እንዲህ የሚል ነበር:- «የተከናወነው መለኮታዊ ፈውስ ነው:: እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን:: እዚህ ላይ ፍርድ መስጠት ባይቻልም እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ማድረግ ይችላል::»

ሴቲቱ የሕክምና ክትትሏን አጠናቃ ከሆስፒታሉ ስትወጣ የተሰጣት ማስረጃ እንዲህ የሚነበብ ነበር:- «ታማሚዋ በመልካም የጤና ሁኔታ ላይ የምትገኝ ከመሆኗም በላይ ምንም ዓይነት የበሽታ ፍንጭ አይታይባትም:: በመሆኑም ያለ ምንም ክልከላ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዋን ማከናወን ትችላለች::»

**ኡ. የድንግል ማርያም ሥዕል::**

> **«በጽድቅህም ነፍሴን ከመከራዋ አውጣት::» መዝ 142:11::**

እ.አ.አ. ከ1829-1908 ዓ.ም. ድረስ የኖረው አባ ዮሐና ክሮንስታድ (Fr. Youhanna Kronstadt) ስለ ጽድቅ ሥራው በሩሲያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚታወቅ ሰው ነበር:: ከጥልቅ ፍቅር ጋር ባሕታዊ ሆኖ ቢኖርም እንደ ካህንም አገልግሏል:: በቅዱስ ወንጌል ጸጋ የተቃኘ አባት ስለሆነም ሕልምና ራእይ የመመልከት፣ ተአምራት የመፈጸምና በሽተኞችን የመፈወስ ስጦታ የታደለ ሰው ነበር::

ሲያስተምር ትምህርቱ ጥልቅ ነገር ግን ቀላል ነበር:: በቃላቱ ውስጥ ከዚህ ቀደም ተደምጠው የማይታወቁ አዲስና ቅዱስ ምሥጢራት ይገለጡ ስለ ነበር እንዲህ እያለ ያስተምር ነበር:- «የተስፋ ቅድስናን በምታድለን በእግዚአብሔር እናት በድንግል ማርያም ላይ እምነት ይኑራችሁ:: አማላጅነቷ በራሷ ቅድስና የተጠናከረ ስለሆነ ወደ ለእርሷ



www.ethiopianorthodox.org

የምናቀርበው ጸሎት ፈጽሞ ያለ ዋጋ አይቀርም:: በጸሎቷ አማካይነት ለኃጢአቶቻችን ምሕረትና ይቅርታ እናገኛለን፤ድኅነታችንንም እናረጋግጣለን:: የምንባረከውም በጤና፣ በሀብት፣ በጥበቃና በክፉ ቀን ከጥፋት በመጋረድ ነው::

ቅዱሳት ሥዕላት ቅዱሳኑን የሚወክሉ ገጽታዎች ናቸው:: ቅዱሳት ሥዕላት የሚረዱን በፍቅራችንና በጸሎታችን መንፈሳዊነታችን ይዘን ወደ ቅዱሳኑ ለመጠጋት ነው::

የድንግል ማርያምን ምልጃ ከልባችሁ ሆናችሁ ስትጠይቁ ከእግዚአብሔር ልብ ጋር የምትነጋገሩ ነው የሚመስላችሁ::

## ከ. ታማኙ ተጠርጣሪ::

እሁድ ታኅሣሥ 22 ቀን 1996 ዓ.ም. (እ.አ.አ.) አንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ በብዙ ሺህ የሚቆጠር የፓውንድ ምንዛሪ ምስር ባንክ አሲዮት ቅርንጫፍ (Misr Bank, Assiuot branch) ለማስቀመጥ ይሄዳል:: ገንዘቡን በመቁጠር ላይ ያለው ገንዘብ ሰብሳቢ ጥቂት የተጭበረበሩ የሃያ ፓውንድ ምንዛሪዎች ስላገኘ ለደኅንነት ሠራተኞቹ ምልክት ይሰጣል:: የባንኩ ሥራ አስኪያጅና የየክፍሎቹ ኃላፊዎች አገልጋዩ መልካም የታማኝነት ዝና ስላለው ምንዛሪውን ከሌሎች ሰዎች እንደ ተቀበለው አድርገው አሰቡ:: ቀደም ሲል ያካሄዳቸው የገንዘብ ልውውጦች ሙሉ ለሙሉ ሕጋዊ ቢሆኑም መርማሪዎቹም አገልጋዩን እንደ ባንኩ ሠራተኞች እስኪያውቁት ድረስ ምርመራውን ማንሄድ እንዳለባቸው ገለጡ::

ይህ ሁሉ ሲሆን ገንዘብ ሰብሳቢው ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድበት ይወተውት ነበር:: በላቦራቶሪ ምርመራ ብቃት ያላቸው ባለሙያዎች፣ ብዛት ያላቸው ከፍተኛ የፖሊስ መኮንኖችና ሌሎች ወንጀል መርማሪዎች ቀረቡ:: ከቅርንጫፉ ባንክ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ከዚያም ወደ አቃቤ ሕጉ ከዚያም ወደ ሌላ ፖሊስ መምሪያ እጅግ ረዥምና በጣም አድካሚ ጉዞ ተደረገ:: በአጠቃላይ ውጣ ውረዱና ምልልሱ ብዙ ቀናትን አስቆጠረ::

በእነዚህ ቦታዎች ላይ ያለው ምርመራ ሲጠናቀቅ አገልጋዩ ካይሮ ውስጥ ወደሚገኘው ወደ ዋናው ቢሮ ተወሰደ:: ወደዚህ ቢሮ የመጣው «ፐብሊክ ፈንድስ ዲነክቲቭ ፎርስ» ከተባለው ድርጅት ማረጋገጫ ለማግኘት ነው:: ከአሲዩት ወደ ካይሮ የተደረገው ጉዞ 24 ሰዓታት የፈጀና እጅግ አድካሚ ከመሆኑም በላይ ካይሮ ደርሶ ሌሊቱን ያሳለፈበትን ኤል ከሊፋ የተባለ ዘግናኝ ፖሊስ ጣቢያ መግለጽ እጅግ አዳጋች ነበር:: በዚያ ሌሊት በአንዲት እጅግ ጠባብ ክፍል ውስጥ በጣም ብዙ እስረኞች





ታጭቀው ስላደሩ ሁለት እስረኞች በአየር እጦት ሕይወታቸውን አጥተዋል::

ኋላ ላይ ግን ከሌላ ስፍራ የመጣ እስረኛ መሆኑ ሲረጋገጥ ለእነዚህ እስረኞች ወደተዘጋጀው የተሻለ ክፍል አዘዋወሩት:: እዚህ ክፍል ሲገባ የተገረመው የድንግል ማርያም ስዕል በክፍሉ መካከል ተሰቅሎ በመመልከቱ ነበር:: እነዚህን ሁሉ መከራዎች ከተቀበለ በኋላ የድንግሊቱን ስዕል ሲመለከት ለሕሊናው ሰላምና ፀጥታ ወረዱለት:: ከዚህ ሁሉ መከራ በሰላም ወጥቶ ወደ ትውልድ መንደሩና ወደ ቤተሰቦቹ በመሄድ ይኖር ዘንድ ድንግል ማርያም በአማላጅነቷ እንድትረዳው ተማጸናት:: ይህን ሲናገር እርሷ ጥልቅ ጸሎቱን እንደምትሰማው እርግጠኛ ስለሆነ እንዲሁ እንደማትተወው ተማመነ::

በሚቀጥለው ቀን በ«ፐብሊክ ፈንድስ ዲነክቲቭ ፎርስ» ከፍተኛ መኮንኖች አማካይነት ጉዳዩ በድጋሚ ይጠና ጀመር:: ይህ ጥናት ረዥም ጊዜ ስለ ወሰደ በሳምንት አንድ ቀን እስረኞችን ወደመጡበት ቀዬ የሚያጓጉዘው ባቡር አመለጠው:: በመሆኑም በአል ከሊፋ እስር ቤት ውስጥ ለተጨማሪ አንድ ሳምንት መቆየት ግድ ሆነበት::

ይህ አገልጋይ በሁኔታው እጅግ ስላዘነ ድንግል ማርያምን እንዲህ እያለ ይማልዳት ጀመር:- «ይህ እንዲሆን ለምን ፈቀድሽ? አሁን እኮ የልደት በዓልንና የአዲስ ዓመት በዓልን ዋዜማ ከቤተሰቦቼ ጋር ማሳለፍ አልችልም::» በዚህ ጊዜ ድንግል በጉዳዩ ጣልቃ ገባች:: ወዲያውኑ አንድ ፖሊስ እርሱ ወደታሰረበት ክፍል እየሮጠ ሲመጣ ተመለከተ:: ፖሊሱም ለአገልጋዩ ካይሮ የሚገኘው ዋና ጣቢያ አገልጋዩን በነጻ ፈትታችሁ ልቀቁት የሚል ውሳኔ አስተላልፏል አለው::

ወዲያውኑ ሁሉም ሰነድ ተፈራርሞ ስለ ተጠናቀቀ ታኅሣሥ 31 ቀን 1996 ዓ.ም. ወደ ትውልድ ከተማው ወደ አሲዩት ተወሰደ:: የአዲስ ዓመት ዋዜማንና ቅዳሴም ከቤተሰቦቹ ጋር አከበረ:: ድንግል ማርያም በከንቱ የጎደፈ ስሙን ለማደስ በመከራ ጊዜዎቹ ሁሉ በአማላጅነቷ አብራው ስለ ቆየች አመሰገናት::

«የኖኅ መርከብ ለሆነች ለእርሷ ምስጋና ይገባታል:: የንጋት ኮከብ ለሆነች ለእርሷም ምስጋና ይገባታል:: የአንቺ በመካከላችን መገኘት እንደ ፀሐይ ያበራልናል፤ለእኛ ለሰው ልጆችም ሁሉ ብርሃንን ይፈነጥቅልናል::»

## ኸ. ድንግል ሆይ ይቅር በዪኝ::

ባኒ ስዌፍ (Bani Swaef) ውስጥ በምትገኘው የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካገለገሉ በኋላ በሞት የተለዩን አባታችን ዲሚትሪ ጊዮርጊስ ስድስት ወንዶች ልጆች ነበሯቸው:: እነዚህ ልጆቻቸው



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር በሚመለክበት ቤተሰብ ውስጥ ስላደጉ አንዱ የምንኩስናን ማዕረግ ሲቀበል ሁለቱ ደግሞ የቅስናን ማዕረግ ተቀበሉ። ሌሎቹ ሁለቱ በመኪና አደጋ ሕይወታቸውን ሲያጡ የቀረው አንዱ ወይም አይሊያ (Ilia) ተብሎ የሚጠራው ውትድርና ለመቀጠር ተመዘገበ።

የጤንነት ምርመራ እንዲያደርግም ወደ ካይሮ ተወሰደ። በዚያ ለረዥም ቀናት ወደ ቤቱ ሳይመለስ ስለ ቆየ አባቱ ይጨነቁ ጀመር። አንድ እሁድ ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደው በመሠዊያው ፊት ለፊት ያለው ደረጃ ላይ ከተቀመጡ በኋላ ዓይኖቻቸውን የድንግል ማርያም ሥዕል ላይ ተክለው ይማጸኗት ጀመር፡- «ድንግሊቱና እውነተኛዋ ንግሥት ሆይ፤ ሰላምታ ይገባሻል። በእኔ ዘንድ የቀረው አንድ ልጄ ውትድርና ተቀጥሮ ሊለየኝ ስለሆነ በጣም አዝኜያለሁና ከጌታዬ ጋር አማልጂኝ።»

አባት ዲሚትሪ ሰኞ ዕለት ወደ ካይሮ የሚወስደው ባቡር ላይ ተሳፍረው እንደ ደረሱ በቀጥታ የሄዱት ወደ መቀጠሪያው ሰፍራ ነበር። ይህ ስፍራ አንድ ከተማ ያህላል። ከዚህ ቦታ ውስጥ ልጁን ፈልጎ ማግኘት በጭድ ክምር ውስጥ የወደቀች መርፌን ፈልጎ እንደ ማግኘት ይቆጠራል። በመጨረሻ በድካም እጅግ ስለ ዛሉ የመንገዱ ጠርዝ ላይ ራሳቸውን አስደግፈው ተቀመጡ። በዚያ እንዳሉም አንዲት ሴት ከአጠገባቸው ተቀመጠችና፡- «አባት ዲሚትሪ ሆይ፤ለምንድር ነው ያዘንኸው?» ብላ ጠየቀቻቸው። እርሳቸውም «ልጄን ለማግኘት ሞክሬ ስላልቻልሁ ነው።» አሏት። ሴቲቱም፡- «ልጅህ እዚህ የለም። እርሱ ያለው አሲዩት (Assiuot) ግዛት ውስጥ ነው። ልጅህ በዚያ ስለሚጠብቅህ ወደ ትውልድ ከተማህ ሂድ። ዳግመኛም በእኔ ላይ እንዳታዝን ይሁን።» አለቻቸው። ሴቲቱ ማን እንደ ሆነች ተገንዝበው ወደ እርስዋ ዘወር ሲሉ ከአጠገባቸው ያጧታል። በዚህ ጊዜ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው፡- «ይህ አይሆንም! ይህ ሊሆን አይችልም! ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? የት ነው ያለሁት? ድንግል ሆይ፤ ይቅር በዩኝ! ንግሥት ሆይ፤ በድዬሻለሁና በደሌን ይቅር በዩኝ! ድንግል ሆይ፤ይቅር በዩኝ . . .» አሉ።

በመጨረሻ አባት ዲሚትሪ ወደ ትውልድ ከተማቸው የሚያደርሳቸው ባቡር ላይ ተሳፍረው እንደ ደረሱ ልጃቸው ኢሊያን ባቡር ጣቢያው ውስጥ ያገኙታል። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔርን ስለ ቸርነቱ ድንግል ማርያምንም ስለ ርኅራኄዋ እያመሰገኑ ወደ ቤታቸው ሄዱ።

### ወ. ውቢቷ ርግብ ድንግል ማርያም።

«እኅቴ፤ወዳጄ፤ርግቤ፤መደምደሚያዬ ሆይ፤. . .» መኃ 5:2።

ድንግል ማርያም ብዙ ጊዜ ለሰዎች ልትገለጥ ስትል የአንድ ትልቅ አንጸባራቂ ርግብ ምስል ይታያል። አሲዩት (Assiuot) የሚገኘው የቅዱስ





ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ላይ ስትገለጥ እነዚህ ርግቦች ከየት እንደ መጡ ሳይታወቅ ይገለጡና በቤተ ክርስቲያኑ ጉልላት ላይ ጥቂት እየበረሩ ከዞሩ በኋላ የሚገቡበት ቦታ ሳይታወቅ ድንገት ይሰወራሉ። ምንም እንኳ ትክክለኛዎቹ ርግቦች በጨለማ እንደማይበሩ ብናውቅም እነዚህ የገነት ፍጥረቶች ግን ድንግል ማርያም ስትገለጥ እነርሱም ይገለጣሉ። እርሷ ከእነዚህ ንፁሕና ነጫጭ ርግቦች ጋር አብራ የምትገለጠው ጉዳት ስለማያደርሱና የሰላም ምሳሌዎች ስለሆኑ ነው። «. . . እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ።» ማነ 10:16።

### ዐ. ድንግል ማርያም በአስዩት (Assiuot)።

እ.አ.አ. ጥር 18 ቀን 2000 ዓ.ም. አንድ የኤሊክትሪክ ሠራተኛ ወደ አስዩት ሆስፒታል ይላካል። በፊቱ ላይ ያሉት ነርቮች አልታዘዝ ስላሉት ከፍተኛ ምርመራ ይደረግለት ጀመር። በመጨረሻም ፊቱ እብጠት ማሳየት ስለ ጀመረ ለተጨማሪ ሕክምና ወደ ካይሮ እንዲላክ ይወሰናል። መስከረም 12 ቀን ሙሉ ምርመራ እንዲደረግለት ቀጠሮ ይያዝለታል።

መስከረም 11 ቀን በሽተኛው ድንግል ማርያም የተገለጠችበትን የቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ለመሳለም ወደዚያው ይሄዳል። በዚያ ሳለም ቤተ ክርስቲያኑን የከበቡትን ሰማያዊ ብርሃናትና አንጸባራቂዎቹን ርግቦች ይመለከታል። እርሷ ስትገለጥ አንባቢውን የሚያውደውንም ሽቱ ያሸታል። በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ ለጥቂት ሰዓታት ከቆየ በኋላ የፊቱ እብጠት ሙሉ ለሙሉ ይጠፋለታል። ከዚያም ወደ ሚስቱ ስልክ ደውሎ «ይህ የቅድስት ድንግል ማርያም ተአምር ነው! አሁን በፊቴ ላይ ምንም እብጠት የለም! እብጠቱ ጠፍቷል!» አላት።

በሚቀጥለው ቀን ለሕክምና ሲቀርብ ሐኪሙ የተመለከተው የእብጠቱን መጥፋት ብቻ ሳይሆን ፊቱ ላይ ያሉት ነርቮችም እንደ ቀድሞው መታዘዝ መጀመራቸውን ነው። እብጠቱና በሽተኛው የነበረበት ሁኔታ እንዴት እንደዚህ ሙሉ ለሙሉ ሊጠፋ እንደ ቻለ ባለማወቃቸው ሐኪሞቹ መደነቃቸው አልቀረም።

በመጨረሻም በሽተኛው ሰው የድንግሊቱን አስደናቂ ተአምር እያደነቀ ወደ መንደሩ ወደ አስዩት ተመለሰ።

### ዘ. ቅድስት ማርያምና አባ አባኑብ (St. Abanoub)

አንድ ቀን አንዲት የ60 ዓመት መበለት ታክሲ ስትሳፈር ወደቀች። ወዲያውኑ በአቅራቢያው ወደሚገኘው ሆስፒታል ወስደው ራጂ ሲያስነሷት በወገቧና በአኒሳዋ ላይ ብዛት ያላቸው የአጥንት ስብራቶች እንዳሉ ተረጋገጠ። ሐኪሞቹ ያለችበት ሁኔታ ተስፋ አስቆራጭ ስለሆነ ዝም ብላ እንድታርፍ ይነግሯታል።



www.ethiopianorthodox.org

የመበለቷ ልጆች ድንግል ማርያም አስዩት ውስጥ በሚገኘው በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ላይ መገለጧን ስለሰሙ እናታቸውን ወደዚያው ይዘዋት ይሄዳሉ። ይሁን እንጂ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ እንዳይገቡ የሕዝቡ ብዛት ከለከላቸው። በዚህ ጊዜ ምንም ሳይታሰብ አንድ የ12 ዓመት ልጅ በቤተ ክርስቲያኑ የጓሮ በር በኩል መጥቶ «ከተቀመጥሽበት ተነስተሽ 'የያዕቆብ ልጅ ሆይ፤ምሕረት አድርጊልኝ፤አድኚኝም።' በዪ አላት።» መበለቲቱም ብላቴናው እንደነገራት አደረገች፤ወዲያውኑም ከስብራቷ ሁሉ ተፈወሰች፤በሚቀጥለውም ቀን ወደ ሥራዋ ተሰማራች።

ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ መበለቲቱ የብላቴናው የፊት ገጽታ ከቅዱስ አባኑብ ሥዕል ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ተናገረች።

**ዧ. ከድንግል ማርያም የተላከ መልዕክት።**

እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ብዙ ጊዜ ተገልጣ ግብጽን ባርካታለች። እርሷ ዜይቶን (Zeitoun) ውስጥ በሚገኘው ቤተ ክርስቲያን ጉልላት ላይ እ.አ.አ. በ1968 ዓ.ም. ተገልጣ ለሦስት ዓመት ያህል ቆይታለች፤በቅድስት ዴሚና (St. Demiana) ቤተ ክርስቲያን ጉልላት ላይ ለወራት ተገልጣለች፤አስዩት ውስጥ በሚገኘው በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ጉልላት ላይም በ2000 ዓ.ም፣ ተገልጣ ለብዙ ወራት ቆይታለች።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ ስለ ድንግል ማርያም መገለጥ እ.አ.አ. በ1968 ዓ.ም. ሲናገሩ «እነዚህ ተአምራት እምነታችንን ያጠናክሩልናል፤ያላመኑትንም ወደ እውነተኛው እምነት ያመጡልናል።» ብለው ነበር።

***5/ ይህ ሁሉ ምን ማለት ነው?***

ይህን በማስመልከት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ የተናገሩት ሮዜልዩሴፍ (Roselyoussef) በተባለ የፖለቲካ መጽሔት ላይ ታትሞ ስለ ወጣ እንደሚከተለው ይነበባል፦

«የእነዚህ መገለጦችና ተአምራት ዓላማ የሰውን ብርታትና በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት ማጠናከር ነው። ሰዎች ከሞት በኋላ ሕይወት መቀጠሉን ማመን አለባቸው። ከሞት በኋላ ሕይወት በመኖሩም ሰው ወደዚህ ሕይወት ለመድረስ ታላቅ ጥረት ማድረግ አለበት። እነዚህ ሁሉ መገለጦች በቤተ ክርስቲያን በኩል ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡ ናቸው። በአጠቃላይ ግን እነዚህ መገለጦች ለምን እንደ ተከሰቱ አናውቅም። ይሁን እንጂ ይህ መገለጥ ከጌታችንና ከመድኃኒታችን





ከኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ የተሰጠ ማበረታቻ፣ ተስፋና የገቡ አቅጣጫ ነው ብለን መደምደም እንችላለን።»

ከዚህ በተጨማሪ ቅዱስነታቸው አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ የተቀደሰው ቤተሰብ ማለትም ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ድንግል ማርያምና አረጋዊው ዮሴፍ ግብጽን መጎብኘታቸውንና እነርሱ ግብጽ ውስጥ ሲቆዩ በተቀመጡበት ቦታ (ዜይቶን/Zeitoun) ላይ የቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን መገንባቱን ሳያስታውሱ አላለፉም።

**በኀውን ሁሉ ለእኛ ያደረገና የሚያደርግ እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን!**



www.ethiopianorthodox.org

## መጽሐፍ ሦስት

# ድንግል ማርያም በዜይቱን ቤተ ክርስቲያን እንደ ተገለጠች

(መገለጧ)

(አዘጋጅ፡- የዜይቱን ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ አለቃ ቡትሮስ ጋይድ)

መግቢያ፡፡
- ❖ በፓትርያርኩ የተመራ የልዑካን ቡድን፡፡
- ❖ በዜይቱን የተገለጡ ተአምራታዊ ድንቅቶች፡፡
- ❖ በዜይቱን የምትገኘው የድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን፡፡

የድንግል ማርያም መገለጥ፡፡
- ❖ በተለይ በዜይቱን ልትገለጥ የቻለችው ለምንድር ነው?
- ❖ ድንግሊቱ መገለጧን የገለጠችው ለምንድር ነው?
- ❖ ቤተ ክርስቲያንና ድንግል ማርያምን ቅድስት የምንልበት ግንዛቤ፡፡
- ❖ ሙስሊሞችና ቅድስት ድንግል ማርያም፡፡
- ❖ የድንግሊቱ ሥዕል፡፡
- ❖ ድንግል ማርያም በዜይቱን ላይ የተገለጠቸው እንዴት ነው?
- ❖ ድንግሊቱ በተገለጠች ጊዜ የታዩ ያልተለመዱ ሁኔታዎች፡፡

በድንግል ማርያም የተፈጸሙ ተአምራት፡፡
- ❖ ድንግል ማርያም ብረት እንዳሟሟች፡፡
- ❖ ኢጥሪብ (Itreeb) ውስጥ የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ተአምራት፡፡
- ❖ ሦስተኛው ተአምር፡፡

ድንግል ማርያም ስትገለጥ የተፈጸሙ ተአምራት፡፡
- ❖ ድንግል ማርያምና የቤተ ክርስቲያኗ ካህን፡፡
- ❖ ሙሽራሽ ይህ ነው፡፡
- ❖ ድንግል ማርያምና የዘይቱ ብልቃጥ፡፡
- ❖ ድንግል ማርያምና በካንሰር በሽታ የተጠቃችው ሴት፡፡
- ❖ ሰባቱ መስቀሎችና በቅብጥ ቋንቋ «አብኖቲ» (Avnoti) ወይም ደብዳቤዎች የሚለው ቃል፡፡
- ❖ ድንግል ማርያም የዐይኗን ብርሃን እንደመለሰችላት፡፡
- ❖ ድንግል ማርያምና የድሆች ፍቅር፡፡
- ❖ ብርቱ የጆሮ ውስጥ ህመም፡፡
- ❖ ከችግሮቼ እንድወጣ እርዳኝ፡፡



ቅድስት ድንግል ማርያም



ወንጌላዊው ቅዱስ ማርቆስ



www.ethiopianorthodox.org



መገለጡ የታየበት ዜይቱን ውስጥ የሚገኘው የድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን
የምሥራቅ በር የፊት ለፊት ገጽታ







መገለጡ የታየበት ቤተ ክርስቲያን መጋረጃ



www.ethiopianorthodox.org



መገለጡ የታየበት ቤተ ክርስቲያን መካከለኛ ጉልላት የውስጥ ስዕል







ወደ ግብጽ የተደረገ ስደት
«. . . ልጄንም ከግብጽ ጠራሁት።» ሆሴ 11:2።
(ጥንታዊቷ ካይሮ ውስጥ የሚገኝ የአል ሙዓላኪህ ቤተ ክርስቲያን።)



www.ethiopianorthodox.org



. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ፤
በቅዱስ ማርቆስ መንበር 117ኛው የእስክንድርያ ኦርቶዶክስ
ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ
እና
አለቃ ቡትሮስ ጋይድ፤
ዜይቶን የሚገኘው የድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ።



ቅድስት ድንግል ማርያም




ዜይቶን ውስጥ የሚገኘው አዲሱ የድንግል ማርያም ካቴድራል



www.ethiopianorthodox.org

ሰውነት የተገለጠችው ቅድስት ድንግል ማርያም በጉልላቱ ላይ እየተንቀሳቀሰች በመስቀሉ ፊት ስትሰግድ ታየች!

እኔ ዜይቱን ውስጥ በሚገኘው የማርያም ቤተ ክርስቲያን ላይ የድንግሊቱን መገለጥ በደስታ ለመመስከር ታድያለሁ::

በቱማንቤይ ጎዳና ላይ የድንግል ማርያምን መገለጥ ለመመልከት በጣም ብዙ ሰው ስለ ተሰበሰበ የትራፊክ እንቅስቃሴው ሙሉ ለሙሉ ተዘግቶ ነበር:: በወቅቱ በጋራዡ ውስጥ በፈረቃቸው ይሠሩ የነበሩት ሠራተኞች በሙሉ ተመሳሳይ የምስክርነት ቃላቸውን ስለ ሰጡ ይህን ክስተት አረጋግጠዋል አጽንተውማል::

የቤተ ክርስቲያኗ አገልጋይ የሆኑት ቄስ ቆስጠንጢኖስ (Rev. Costantin) ይህንኑ መገለጥ ተመልክተዋል::

ድንግሊቱ አንዳንድ ጊዜ ከወገቧ በላይ ስትገለጥ በሌላ ጊዜ ደግሞ በሙሉ ቁመናዋ ተገልጣ በጉልላቱ ላይ ወዲያና ወዲህ ትንቀሳቀስ ነበር:: ቤተ ክርስቲያኗንና በፊት ለፊቷ የተሰበሰበውን ታዳሚ ሕዝብ እጅ በመንሣት ባርካለች:: በአንዳንዶቹ ምሽቶች ውስጥ ጸሎት በሚጸልይ ሰው ቅርጽ ተገልጣ ታይታለች:: በቤተ ክርስቲያኗ ጉልላትና መስቀል ፊት ስትሰግድም ታይታለች:: አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አንጸባራቂና ብሩኅ በሆኑ ርግቦች በተመሰሉ ሰማያዊ የሰዎች አካላት ታጅባ ትገለጣለች ወይም ርግቦቹ ቀድመዋት ይገለጡ ነበር:: እንዲሁ አንዳንድ ጊዜ የወይራ ዝንጣፊ በእጇ ይዛ ተገልጣለች::

እነዚህ መገለጦች ዓመቱን ሙሉ ቢከሰቱም የድንግሊቱ ተአምራት እስከ ዛሬ ድረስ እየተፈጸሙ ነው::

በዚህች አነስተኛ መጽሐፍ ውስጥ እኔ ራሴ የተመለከትኳቸውን ተአምራት መዝግቤ ይገኛያለሁ ትክክለኝነታቸውንም አረጋግጬያለሁ::

ይህን መጽሐፍ አሁን በያዘው ቅርጽ አወጣው ዘንድ የረዳኝን አቶ ሳፍዋት ፋሒምን አመሰግናለሁ::

አሌቃ ቡትሮስ ጋይድ
የዜይቱን ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ::

በፓትርያርኩ የተመራ የልዑካን ቡድን::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ 6ኛ፤በቅዱስ ማርቆስ መንበረ የእስክንድርያ ጳጳስ፤በአፍሪቃና በመካከለኛው ምሥራቅ የቅዱስ ሲኖዶስ





ፓትርያርክ፤አንዳንድ ከፍተኛ ማዕረግ ያላቸው አባቶችን እየመሩ ቦታው ድረስ በመሄድ ምርመራና ማረጋገጫ እንዲካሄድ አድርገዋል:: ቅድስት ድንግል ማርያም በጉልላቱ ላይ ወዲያና ወዲህ እያለች በቤተ ክርስቲያኗ ፊት ለፊት የተሰበሰበውን ሕዝብ ስትባርክ እነርሱም በገዛ ዐይኖቻቸው እስኪመለከቱ ድረስ ለብዙ ቀናት በስፍራው ላይ ቆይተዋል:: በዚህ ወቅት በሌሎች ቅርጾችም ተገልጣለች:: በመሆኑም አንዳንድ ጊዜ በሚያንጸባርቅ ብሩኅ አካል ስትገለጥ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከወገቧ በላይ ተገልጣለች:: በእነዚህ ጊዜያት ሁሉ በራሷ ላይ የሚያበራ ነጭ የብርሃን ክበብ (ሀሎ) የነበረ ሲሆን ይህ ብርሃንም ከጉልላቱ ከፍተት ወይም ከጉልላቱ በታች በነበረውና እርሷ እየተረማመደች በመስቀሉ ፊት ስትሰግድበት ከነበረው ከቤተ ክርስቲያኗ ጣሪያ መካከል ነበር:: ይህ ብርሃን የመፈንጠቅ ኃይል ያለው ነበር:: ከቤተ ክርስቲያኗ ፊት ለፊት ባለው ሕዝብ አንጻር ቆማም ሰዉን ሁሉ በእጆችዋና በተቀደሰ ጭንቅላትዋ ንቅናቄ ስትባርክ ታይታለች::

አንዳንድ ጊዜ የምትገለጠው በሚያንጸባርቅ ብሩኅ ደመና ላይ በሚንሳፈፍ ሰማያዊ የብርሃን አካል ሲሆን ይህ ከመታየቱ ቀደም ብሎ በከፍተኛ ፍጥነት የሚበሩ መንፈሳዊ ርግቦች ተገልጠው ይታያሉ::

መገለጦቹ በጣም ለረዥም ጊዜ ቆይተዋል:: ለምሳሌ:- እ.አ.አ. ኤፕሪል 30 ቀን 1968 ዓ.ም. የታዩት መገለጦች ለሁለት ሰዓታት ያህል ቆይተዋል::

በተለያዩ የሃይማኖት ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የሀገርና የውጪ ሀገር ዜጎች ለእነዚህ መገለጦች ምስክር ሆነዋል:: የሃይማኖት ድርጅቶች፣ የሳይንስ ሰዎች፣ የተለያዩ ባለሙያዎችና ሌሎችም የተለያዩ ሰዎች ይህን ጉዳይ በመግለጥ ምስክርነታቸውን በገሃድ ሰጥተዋል:: ሁሉም ሰዎች መገለጫዋን፣ ቅርፅዋን፣ የተገለጠችበትን ጊዜና ቦታ ተመሳሳይ በሆነ ቃል ተናግረዋል:: ይህ ሙሉ መስማማት የድንግል መገለጥ ከጥርጥር ውጪ መሆኑን አረጋግጧል::

ይህ መገለጥ በሁለት ጠቃሚ ጉዳዮች የታጀበ ነበር:-

1/ የመጀመሪያው ጉዳይ:- በእግዚአብሔር፣ በሚመጣው መንግሥትና በቅዱሳን ማመንን ያረጋግጣል:: ይህን የተመለከቱ ኢ-አማንያንና ደካማ እምነት ያላቸው ሰዎች በአዲሱና በእውነተኛው እምነታቸው አማካይነት ይለመልማሉ::

2/ ሁለተኛው ጉዳይ:- የሚመለከታቸው የጤናና የሳይንስ ሰዎች መርምረዋቸው ሊድኑ ያልቻሉ ብዛት ያላቸው በሽተኞች በዚህ መገለጥ ወቅት በአስደናቂ ተአምር መዳናቸው ነው::



www.ethiopianorthodox.org

ይህ በረከት ለዓለማችን የሚመጣውን ሰላም ጠቋሚ ምልክት ከመሆኑም ሌላ ለተባረከችው አገራችንና ለምንወደው ሕዝባችን የብልጽግና ገድ ነው::



መገለጡ ሊታይ እንደ ጀመረ

**በዜይቱን የተገለጡ ተአምራታዊ ድኅነቶች::**

በዜይቱን ያለውን የቅብጥ ቤተ ክርስቲያን ከጎበኙ በኋላ በማይድን በሽታ የተያዙ ብዙ በሽተኞች በአስደናቂ ተአምር ተፈውሰዋል:: በፓትርያርኩ የተመራው የልዑካን ኮሚቴ የተገለጡትን ድኅነቶች ከሕክምናና ከሳይንስ አንጻር መርምሯል:: ዐይነ ሥውርነት፣ ሽባ የሆኑ የሰውነት ብልቶች፣ ካንሰርና ዲዳነት ዜይቱን ውስጥ በስሟ በተገነባው ቤተ ክርስቲያን አማካይነት የቅድስት ድንግል ማርያምን አማላጅነት በመማጸን ፈውስ ተገኝቶላቸዋል:: የሕክምና ባለሙያዎች (Doctors) ከመደነቃቸው በላይ እነዚህን ለመሰሉ ፈውሶች ምንም ዓይነት የሕክምና መግለጫ መስጠት እንደማይቻል በይፋ አረጋግጠዋል::

**በዜይቱን የምትገኘው የድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን::**

ይህች ቤተ ክርስቲያን እ.አ.አ. በ1924 ዓ.ም. የታነጸችው በጣሊያናዊው የሕንጻ ፕላን አዘጋጅ በሊዮሚንጌሊ (Leomingelli) የበላይ ተቆጣጣሪነት ሥር ይገኝ በነበረውና ዛሬ በሕይወት በሌለው በቶፊቅ ካሊል





(Tawfeek Khalil) አማካይነት ነው:: ቤተ ክርስቲያኗ እ.አ.አ. በ1925 ዓ.ም. የተባረከችው የቤኒ ስዌፍ ጳጳስ (Bishop of Beni Sweif) በነበሩት በአባ አትናትዮስ አማካይነት ነው::

በትውፊት እንደሚነገረው ድንግል ማርያም ዛሬ በሕይወት ለሌለው ለካሊል ፓሻ ኢብራሂም ተገልጣ (Khalil Pasha Ibrahim) በዚህ ቦታ ላይ በስሟ አንድ ቤተ ክርስቲያን እንዲያንጽ ነግራው ነበር፤በዚህ ጊዜም ከአምሳ ዓመታት በኋላ በዚህች ቤተ ክርስቲያን ላይ እንደምትገለጥ ቃሏን ሰጥታው ነበር:: እነሆ እንደተናገረችውም ይህ ቃል ኪዳኗ ከአምሳ ዓመታት በኋላ ኤፕሪል 2 ቀን 1968 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ ተግባራዊ ሆነ::

አንዲት የኖርዌይ ሴት የድንግል ማርያምን የመገለጥ ዜና ይፋ እንደ ሆነ አስሎ በሚገኘው መኝታ ቤቷ ውስጥ ተገልጣ ከልጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በስደት ሳሉ ዜይቱን ውስጥ ያርፉበት በነበረው ቦታ ላይ በታነጸችው ቤተ ክርስቲያን ላይ እንደምትገለጥ ነግራት እንደ ነበር በደብዳቤ ገልጻ ልካለች::

**የድንግል ማርያም መገለጥ::**
**በተለይ በዜይቱን ልትገለጥ የቻለችው ለምንድር ነው?**

እንደ እኔ እምነት ከሆነ መገለጧ ሁለት ተልዕኮዎች አሉት:: የመጀመሪያው አሁን የተፈጸመው ተልዕኮዋ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በሂደት የሚፈጸመው ተልዕኮዋ ነው::

የመጀመሪያውና የተፈጸመው ተልዕኮ ጥርጥር በተስፋፋበትና ቁሳዊ እምነት በተንሰራፋበት ዘመን እምነትን ለማጠናከር የተገለጠ ነው:: ስለ እነዚህ የእምነት ተቃዋሚ ምክንያቶች ስንናገር የምንናገረው ስለ ኮሚዩኒዝም፣ በትንሣኤ ሙታን ስላለማመን፣ ስለ ሥነ ምግባር ጉድለት፣ የነፍስንና የእግዚአብሔርን መኖር ስለ መካድና በእውቀት ስለ መመራት ነው::

በዚህ ወቅት ድንግል ማርያም ተገለጠች ማለት የአማኞችን እምነት ይጠናከር ዘንድ አነሣሣች የተጠራጣሪዎችንም ከንቱ ጥያቄ ዋጋ አሳጣች ማለት ነው::

የድንግል ማርያም መገለጥ የኦርቶዶክስን የእምነት መሠረት አጠናክሯል:: እኛ የተሳሳተ መንገድ ውስጥ ገብተን ቢሆን ኖሮ መገለጦቿ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጉልላቶች ላይ ለአንድ ዓመት ያህል አይቆዩም ነበር::



www.ethiopianorthodox.org

የወይራ ዛፍ ምንጊዜም ለምለም ነው:: ይህም የዕድገት፣ የልምላሜና መቼም ቢሆን የማይጠወልግ የፍሬያማ ክርስቲያን ምሳሌ ነው::

በወይራ ዛፍ ተራራ ላይ (ጌቴሴማኒ) ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲጸልይ ያድር ነበር:: መከራውን እንደ ነገ መቀበል ሊጀምር እንደ ዛሬ ይህችን ምድር ከሰውነቱ በሚወጣውና እንደ ደም ነጠብጣብ በተንጠባጠበው ወዙ አርሷት ነበር:: ይህ በመሆኑም ይህች ምድር እስከ መጨረሻው ድረስ የተቀደሰች ሆናለች::

ከዚህ በተጨማሪ እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በተለይ ሁኔታ በዜይቱን የተገለጠችው እርሷና ተወዳጁ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ግብጽ ባደረጉት እጅግ አድካሚ የስደት ጉዞ ላይ በዚህ ቦታ ላይ ዕረፍት ስላደረጉ ነው::

**ቤተ ክርስቲያንና ድንግል ማርያምን ቅድስት የምንልበት ግንዛቤ::**

«እነሆም ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤. . .» ሉቃ 1:48::

ቤተ ክርስቲያን ድንግል ማርያምን የምትቀበላት በቅድስትነቷ ነው:: በመሠረተ ሃይማኖት ድንጋጌ መቅድም ውስጥ እንዲህ እንላለን:- «እነሆ የእውነተኛው ብርሃን እናት ለሆንሽው ክብርና ምስጋና ይገባሻል፤ለቅድስት ድንግል ማርያም ምስጋና ይገባታል::»

በጸሎቶቻችን ውስጥ ልመናዎቻችን ተቀባይነት ያገኙ ዘንድ የእርሷን አማላጅነት እንደምንሻ በጸሎት መጽሐፋችን ውስጥ ተገልጦአል::

ዕጣን ስናሳርግም ካህኑ ፊቱን ወደ ሰሜን መልሶ:- «እኛም እንደ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል 'ጸጋን ለተመላሽ ለአንቺ ሰላም ይሁን!' » እንላለን::

ካህኑ ሲባርክም እንዲህ ይላል:- «አቤቱ ጌታ ሆይ፤እኛ ዘወትር ጸሎት ስናቀርብ የእግዚአብሔር እናት በሆነችው በንግሥቲቱ በቅድስት ድንግል ማርያም ስም ስለምናቀርብ ይህን ልመናችንን ተቀብለህ ክርስቲያኖች በሚሻሉ ነገሮች እንዲደሰቱ አድርግ::»

ልክ እንደዚሁ ቅዳሴ ሊጠናቀቅ ሲል «ቅድስተ ቅዱሳን የሆነችው የእግዚአብሔር እናት ፍጹም ንጹሕ ናት::» በማለት እናወድሳታለን::





ከዚህ በተጨማሪ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ እያለች ታዜማለች:- «አንቺ የወርቅ ጥና ነሽ፤አዳኙ መድኃኒት ደግሞ የጥናው መልካም መዓዛ ነው::»

«በዕርቅ ጸሎት» ውስጥ ካህኑ የጥናውን መያዣ በማስቀመጥ «ሥጋ የለበሰው ክርስቶስ የሰውን መልክ ያዘ» ይላል:: የዕርቁ ጸሎት እንዳበቃም ቤተ ክርስቲያን እንዲህ እያለች ታዜማለች:- «አቤቱ ጌታ ሆይ፤ የእግዚአብሔር እናት በሆነችው በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ኃጢአታችንን ይቅር በለን::» በመጨረሻም «ድንግል ሆይ፤ልብሽ በሐሴት ይሙላ . . .» እንላለን::

በቅዳሴያችንም ይህን እንላለን:- «አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፤ መንገዶችህን ገና ከጅምሩ የተከተሉትን ሰዎች አስባቸው፤በተለይም ደግሞ በጸጋህ የተሞላችውን፤ዘላለማዊ ድንግል የሆነችውንና የእግዚአብሔር እናት የሆነችውን ቅድስት አስባት::»

በንስሓ ወቅትም ይህን እንናገራለን:- «ሕይወት የሚሰጠው ሥጋ ይህ ነው፤የተገኘውም የእግዚአብሔር እናት ከሆነችው ከንግሥቲቱ እመቤት ከቅድስት ድንግል ነው::»

በእርግጥም የተባረከው የቅድስት ማርያም ኅሊና በየእንዳንዱ ሰው ዘንድ የተከበረ ነው:: እውነቱን ለመናገርም ይህ ኅሊና በማንም ዘንድ አይገኝም፤እርሷ የእግዚአብሔር እናት አይደለችምን?!

***ሙስሊሞችና ቅድስት ድንግል ማርያም::***

ቁራን ውስጥ ስለ ድንግል ማርያም ከፍተኛ ዋጋና ታላቅ ክብር ብዛት ያላቸው ማስረጃዎች አሉ:: ብዙ ሴቶች ለዚህ ክብር ሳይታደሉ እርሷ ግን በእግዚአብሔር ተመርጣለች:: እርሷ በሰው እጅ ያልተነካች ስለ ሆነች እግዚአብሔር እርሷንና ልጇን የዓለም መደነቂያ አድርጓቸዋል::

**የድንግሊቱ ሥዕል::**

የእናታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ሥዕል ለመጀመሪያ ጊዜ የሣለው ቅዱስ ሉቃስ ወንጌላዊ ነው:: ቅዱስ ሉቃስ ወንጌልንና የሐዋርያት ሥራን የጻፈ ታላቅ ሐዋርያ ነው:: እርሱ ሐኪምና ሠዓሊም ነበር::

ቀደም ሲል ቅዱስ ሉቃስ የድንግሊቱን ምስል የቀረጸው በእንጨት ላይ ሲሆን ኋላ ላይ ግን ከዚህ ቅጽል ብዛት ያላቸው ሥዕሎች ተሥለው ታትመዋል:: አብዛኛዎቹ እነዚህ ሥዕሎች በሮማ ነገሥታትና በንግሥት ቦልጋሪያ (Empress Bolgaria) የተወረሱ ናቸው::

በጣም ጥንታዊ የሆኑ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሥዕሎች የሚገኙት ካይሮ በሚገኘው በኤል ኤዝባዌያ (El-Ezbawweya)



www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ክርስቲያንና ኤል ናትሩን ሸለቆ (El-Natroun Valley) ውስጥ የሚገኘው ኤል ሴሬያን (El-Seryan) ገዳም ውስጥ ነው።

ምንጊዜም ቢሆን የድንግል ማርያም ሥዕል የሚቀመጠው ከመሠዊያውና ከኢየሱስ ክርስቶስ በስተቀኝ ነው። «በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች።» መዝ 44:9።

**ድንግል ማርያም በዜይቱን ላይ የተገለጠቸው እንዴት ነው?**

ድንግል ማርያም ራሷን ዜይቱን በሚገኘው በቅድስት ድንግል ማርያም ላይ የገለጠችው እ.ኤ.አ. በኤፕሪል 2 ቀን 1968 ዓ.ም. ዋዜማ ላይ ነው። መገለጦቿ የታዩት ሙሉና ጉልህ ሆነው ነበር። ከዚህ በተጨማሪ ብዛት ያላቸው ሌሎች ቅርጾችም ታይተዋል። ለምሳሌ:-

1/ የመጀመሪያው ሙሉና አንጸባራቂ ቁመና ነበር። በዚህ ጊዜ ከእግሮቿ የሚረዝም ቀሚስ ለብሳ ነበር። አንዳንድ ጊዜ በጣም ደማቅ በሆኑ ከዋክብት ትታጀብ ነበር። በሌላ ጊዜ ደግሞ በራሷ ላይ የአንገት ልብስ ጣል አድርጋ ሁለት እጆቿ ወደፊት ይዘረጉ ነበር።

2/ ድንግሊቱ በተለይም በቤተ ክርስቲያኑ መካከለኛ ጉልላት ላይ ወዲያና ወዲህ እያለች ትራመድ ነበር። በመካከልም በደማቅ ብርሃን በተሞላው መስቀል ፊት ለፊት ትሰግድ ነበር።

3/ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሕፃን ልጅ እንደ ታቀፈች ትገለጥ ነበር።

4/ በቤተ ክርስቲያኑ ምሥራቃዊ ጉልላት ላይ በአንጸባራቂ ቅርጽ ትገለጥ ነበር። መላ ቁመናዋ ግልጽ ነበር።

5/ የድንግሊቱ መገለጥ ቀደም ብለው በሚታዩና ቤተ ክርስቲያኑን በሚዞሩ ነጫጭ ርግቦች ይታጀብ ነበር።

6/ አንዳንድ ጊዜ መብረቅ የሚመስል ብርሃን ይከሰት ነበር። ይህ ብርሃን ለጥቂጥ ጊዜ ይቆይና ይጠፋል። አንዳንዴ ደግሞ ጭጋግ የሚመስለው አንጸባራቂ ብርሃን ዙሪያውን ይበተንና አካባቢውን በመልካም መዓዛው በሚያውድ ዕጣን ያሻትተዋል።

7/ እኔ ራሴ ጨረቃይቱ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ በቀረበች ቁጥር በክብ ሰሌዳዋ ላይ ድንግል ማርያም ሕፃን ልጅ በክንዶቿ ላይ እንደ ታቀፈች መገለጧን በገዛ ዓይኖቼ ተመልክቼያለሁ።

ድንግሊቱ ዓመቱን ሙሉ በሺዎች በሚቆጠሩ ሰዎች ፊት እየተገለጠች ቆይታለች። ድንግል ማርያም ሲመጡ ባላቸው ከባድ





ክስተቶች ላይ የምሥጢር ተልዕኮ አላት ብዬ አምናለሁ። ስለ አገራችንም ብዛት ያላቸው ቃል ኪዳኖች አሏት ብዬ አስባለሁ።

**ድንግሊቱ በተገለጠች ጊዜ የታዩ ያልተለመዱ ሁኔታዎች።**

1/ **ርግቦች።** በሌሊት ይበሩ ስለ ነበር ከሚታወቁት ርግቦች ይለያሉ። በመጠናቸው ትላልቅ ሲሆኑ በቅርጽም ይለያያሉ።

2/ **ከዋክብት።** ከሚታወቁት ከዋክብት በመጠን ይተልቃሉ። በቤተ ክርስቲያኑ ላይ በፍጥነት ይወርዱ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ክብ ቅርጽ ሲኖራቸው በሌላ ጊዜ ደግሞ የፋኖስ ቅርጽ ይይዙ ነበር።

3/ **ብርሃን።** በተደጋጋሚ ይወጣ የነበረው በጉልላቱ ላይ ነበር። የብርሃኑ ቀለም ብርቱካናማና ፈካ ያለ ሰማያዊ ነበር። ይህ ብርሃን ቤተ ክርስቲያኗን እንደ ተቀደሰ ክበብ ይከብባት ነበር።

5/ **መስቀል።** መስቀሉ ብርሃን የማያስተላልፍ ቢሆንም በትልቁ ጉልላት ላይ እንደ «ፍሎረሰንት» መብራት ያበራ ነበር። አንዳንድ ጊዜ በጉልላቶቹ ላይ ወይም ድንግል ማርያም በተገለጠች ጊዜ በላይዋ ላይ በጣም ደማቅ መስቀል ይወጣ ነበር።

6/ **ዕጣን።** አካባቢውን ብርቱ የሚያስደስት ሽታና ነጭ ጭስ ያውደው ነበር።

7/ **ደመናዎች።** ይከሰቱ የነበረው በጉልላቱ ላይ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ የሚከሰቱት የድንግሊቱን ቅርጽ እንደ ያዙ ነበር።



www.ethiopianorthodox.org











ከዚህ በላይ የሚታዩት ሦስት ፎቶግራፎች የሚያሳዩት የርግብ ቅርጽ ያላቸው ፍጥረታትን ነው:: ከየት እንደሚመጡ አይታወቅም፤ሲበሩም ክንፎቻቸውን አያራግቡም፤በመጨረሻም እንደ አመጣጣቸው ይሰወራሉ:: የመጀመሪያው ፎቶግራፍ የመስቀል ቅርጽ እንደ ያዙ ያሳያል::

**በድንግል ማርያም የተፈጸሙ ተአምራት:: (በዚህ ርዕስ ሥር የተካተቱት 3 ተአምራት ብቻ ናቸው::)**

**1/ ድንግል ማርያም ብረት እንዳሟሟች::**

ሐዋርያው ቅዱስ ማትያስ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰብክ ዘንድ ገላትያ አጠገብ ወደምትገኘውና ቦንጦስ (Bounts) ተብላ ወደምትጠራው ከተማ ሄዶ ነበር::

በዚያ ሳለ የከተማዋ ሰዎች ለጣዖታት ይጸልዩ ነበር:: ማትያስ የእግዚአብሔርን ቃል ከሰበከላቸው በኋላ ግን ጣዖታቱን ሰባብረው በታተኗቸው:: አገረ ገዥው ይህን ባወቀ ጊዜ እጅግ ስለ ተቆጣ ማትያስን አስሮ በወኅኒ ቤት ጣለው:: በኢየሩሳሌም ከተማ ያለችው ድንግል ማርያም ስለ ችግሩ ሰማች:: ከዚያም አለበት ቦታ ድረስ በመሄድ ወኅኒው ደጃፍ ላይ ከቆመች በኋላ ተወዳጁ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያው የቅዱስ ማትያስን



www.ethiopianorthodox.org

ከመከራዎቹ ያድነው ዘንድ ተማጸነችው:: በዚህ ጊዜ በእስር ቤቱ ውስጥ ያሉት ብረቶች ብቻ ሳይሆኑ በከተማው ውስጥ ያሉት ብረቶች ሁሉ ሙሉ ለሙሉ በመቅለጥ ልክ እንደ ውኃ ፈሰሱ:: እስረኞቹ ሁሉ ከእስር ቤቱ ውስጥ በደስታ ወጥተው ሄዱ:: አገረ ገዥው አንድ አእምሮው የተቃወሰ ልጅ የነበረው ቢኖረውም በድንግል ማርያም አማላጅነት ሊፈወስ በቃ::



የድንግል ማርያምና የሐዋርያው ማትያስ ሥዕል

አገረ ገዥው የደረሰውን አደጋ አስመልክቶ ድንግልን ስለ ተማጸናት ብረቶቹ ወደ ቀደመ ይዘታቸው ተመለሱ:: በመጨረሻም አገረ ገዥው የተቀሩትን ጣዖታት ሙሉ ለሙሉ ሰባብሮ ካጠፋ በኋላ የከተማዋ ነዋሪዎች ሁሉ በቅዱስ ማትያስ እጅ እንዲጠመቁ አደረገ:: አገረ ገዥው ይህን ሁሉ ካደረገ በኋላ አንዲት ድንቅ ቤተ ክርስቲያን በከተማው ውስጥ አስገነባና በእግዚአብሔር እናት በቅድስት ድንግል ማርያም ስም እንድትጠራ አደረገ::

## 2/ ኢጥሪብ (Itreeb) ውስጥ የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ተአምራት::

በሐሩን ኤል ረሺድ (Harun El-Rasheed) ዘመነ መንግሥት ግብጽን ይመራ የነበረ አንድ ጨቋኝ አገረ ገዢ ነበር:: ይህ አገረ ገዢ አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ እንዲጠፉ ትእዛዝ አወጣ:: የአገረ ገዢውን ትእዛዝ የተቀበሉ ወታደሮችም ወደ ኢጥሪብ ገሥግሠው ደረሱ:: በከተማዋ ውስጥ





በድንግል ማርያም ስም የምትጠራ አንድ ብዙ ወርቅና ጠቃሚ ንብረቶች ያሉባት ቤተ ክርስቲያን ነበረች::

የወታደሮቹ አዛዥ ወደ ከተማዋ ሲደርስ አንድ ካህን ወደ እርሱ በመቅረብ ወደ ድንግል ማርያም ሥዕል ይዞት ከመጣ በኋላ የአረብ ሙስሊሞች ግዛት የበላይ ኃላፊ ከሆነው ከሊፋ ቤተ ክርስቲያኗ ከጥፋት የምትድንበትን ትእዛዝ እስኪያመጣ ድረስ የሦስት ቀናት ጊዜ እንዲሰጠው ጠየቀው:: አዛገዡ ከዚህ ተነሥቶ ከሊፋው ወደሚቀመጥባት ወደ ባግዳድ (Baghdad) ከተማ ለመድረስ ወራት እንደሚፈጅ ከገለጠለት በኋላ በካህኑ ላይ በጣም ከት ብሎ ሳቀበት:: ካህኑ አጥብቆ ስለ ለመነው ብቻ ያለ ውዴታው የሦስቱን ቀናት ፈቃድ ሰጠው::

ይህ ካህን የአዛገዡንና የወታደሮቹን የሦስት ቀናት ወጪ ካሰላ በኋላ 300 ፓውንድ በእጁ ሰጠው:: ከዚህ በኋላ ካህኑ በፍጥነት ወደ ድንግል ማርያም ሥዕል ከሄደ በኋላ አጥብቆ በመጸለይ እንድትረዳው ጠየቃት:: ካህኑ በመጸለይ ላይ ሳለ ባግዳድ ውስጥ በሚገኘው በከሊፋው ዙፋን ላይ ደማቅ ብርሃን ከበራ በኋላ ቤተ ክርስቲያኗ ከጥፋት የምትታደግበትን አዋጅ ማወጁን የሚገልጥ ጦማር ጽፎ እንዲልክ ትእዛዝ ይሰጠዋል::

አዋጁ ከተጻፈ በኋላ አንዲት ወፍ በአፏ ነጥቃ በመውሰድ ወደ ስፍራው እየከነፈች ሄደች:: ከጥቂት ሰከንዶች በኋላ ወፊቱ ኢጥሪብ ደርሳ ጦማሩን በአዛገዡ ፊት ለፊት ከጣለች በኋላ በመጣችበት ሁኔታ ተመልሳ ሄደች:: ከጥቂት ቀናት በኋላ ከሊፋው ከሚፈታተነው ክፋትና በእርሱ ላይ ከሚጠነሰሱ ሴራዎች ታድነው ዘንድ በስሟ አንድ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ለመገንባት ያለውን ዕቅድ በይፋ ገለጠ:: ይህ በመሆኑም በክርስቲያኖች ላይ የሚደርሰው ጭቆና እጅጉን ስለ ቀነሰ በሰላም ይኖሩ ጀመር:: ስለ ልመናዋ ድንግል ማርያም የተመሰገነች ትሁን::

## 3/ ሦስተኛው ተአምር::

ይህ ተአምር የተገለጠው ድንግል ማርያም ያረፈች ጊዜ ነው:: ድንግል ማርያም ከዚህኛው ዓለም ተለይታ የምትሄድበት ጊዜ ሲደርስ ሐዋርያት በዓለም ዙሪያ ተበትነው ነበር:: የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነም ሁሉም ከነበሩበት ሀገረ ስብከት በደመና ተጭነው ወደ ጌቴሴማኒ ከተሰባሰቡ በኋላ ድንግል ማርያምን ሲያዩያት ስለ ቻሉ ተደሰቱ:: እርሷም እነርሱን ለማየት ስለቻለች ሐሴት አደረገች:: ከዚያም በኋላ አጽናናቻቸው ተሰናበተቻቸውም:: በዚህ ጊዜ ሐዋርያት ጸሎትና ዝማሬ ማቅረብ ስለ ጀመሩ የማይታዩ መላእክት አብረዋቸው ያዜሙ ጀመር::

አይሁድ በቀብሩ ሥነ ሥርዓት ላይ የተገኙ ለመምሰል ተሰባሰቡ:: ከመካከላቸውም አንዱ እጁን ዘርግቶ ሥጋዋ ያረፈበትን ሳጥን ገፍቶ መሬት ላይ ጣለው:: በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር ቁጣ በእነርሱ ላይ ነደደ::



www.ethiopianorthodox.org

ሁሉም ዐይኖቻቸው ታወሩ:: ሳጥኑን ገፍቶ የጣለው ዓመፀኛ ይሁዲ ግን ሁለት እጆቹ ከሰውነቱ ተለይተው በአየር ላይ ተንጠለጠሉ::

በዚህ ጊዜ ዓመፀኛው ይሁዲ እየጮኸ ያለቅስ ጀመር:: ይህን የተመለከተው ቅዱስ ጴጥሮስ ወደ ሰውየው ተጠግቶ ይህች እናት ዘላለማዊ ድንግልና የእግዚአብሔር እናት መሆኗን በፍጹም ልቡ እንዲያምን ጠየቀው:: ሰውየው ጥፋተኛነቱን በማመን ለታላቅ ንስሓ ድምፁን ከፍ አድርጎ መጮኹን ቀጠለ:: በዚህ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ ሰውየውን ወደ አጎበሩ ሲያስጠጋው እጆቹ ወደ ቦታቸው በመመለስ ከሰውነቱ ጋር ተጣበቁ:: በዚያ የነበሩ ሁሉ ሁኔታውን ተመልክተው ወደ እምነት ተመለሱ:: ቅዱስ ጴጥሮስም ምሕረት ታደርግላቸው ዘንድ ሰዎቹ ሁሉ ወደዚህች ንጽሕት ድንግል ልብስ እንዲጠጉ ጠየቃቸው::

ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ ከወንጌል አገልግሎት ከህንድ በደመና ተጭኖ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለስ መላእክት የድንግል ማርያምን ሥጋ በህባቤና በታላቅ ክብር ሲያሳርጉ ይመለከታል::

ከዚህ በኋላ ሐዋርያት ድንግል ማርያም ስታርግ ለመመልከት ለ15 ቀናት ሱባኤ ስለ ያዙ እግዚአብሔር ይህን ምሥጢር ገለጠላቸው::

እኛም የእመቤታችን ድንግል ማርያምን ጾም በየዓመቱ (ከነሐሴ 1 እስከ ነሐሴ 16 ቀን ድረስ) ከጾምን በኋላ ቅዱስ ሥጋዋ ወደ ገነት ከፍ ከፍ ያለበትን የዕርገቷን በዓል ነሐሴ 16 ቀን አያይዘን የምናከብረው ይህንኑ ለማሰብ ነው::



የድንግል ማርያምን እረፍት የሚያሳይ ሥዕል







የድንግል ማርያም ዕርገት የሚያሳይ ሥዕል

**ድንግል ማርያም ስትገለጥ የተፈጸሙ ተአምራት::**

የድንግል ማርያም መገለጥ ታዋቂ የሕክምና ባለሙያዎች (Doctors) ባረጋገጧቸው ብዛት ባላቸው ተአምራት የታጀበ ነበር:: እነዚህ ተአምራት እስከ ዛሬ ድረስ እየተከሰቱ ነው::

ድንግል ማርያም ስትገለጥ የተፈጸሙት እነዚህ ተአምራት በመጽሔቶችና በመጻሕፍት ላይ ወጥተዋል::

ይህ ይሁን እንጂ እኔ እ.አ.አ. ጁላይ 1962 ዓ.ም. በዋለው የሐዋርያት ጾም ውስጥ ክህነት ተቀብዬ በማገልገል ላይ ባለሁበት በዚህ ዘመን ውስጥ የተመለከትኋቸውን አንዳንድ ተአምራት መዝግቤ ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ ስለ ታየኝ ይህን አድርጌያለሁ:: እነዚህ ተአምራት ከዚያን ጊዜ አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ እየተፈጸሙ ናቸው::

**1/ ድንግል ማርያምና የቤተ ክርስቲያኗ ካህን::**

ኤፕሪል 2 ቀን 1968 ዓ.ም. ዜይቱን ውስጥ በምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ጉልላት ላይ ስትገለጥ ቀድመው የተመለከቷት ከቤተ ክርስቲያኗ ፊት ለፊት ባለው ጋራዥ ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች ነበሩ::



www.ethiopianorthodox.org

ኤፕሪል 10 ቀን 1968 ዓ.ም. ድንግል ማርያምን በስተ ምሥራቅ አቅጣጫ በሚገኘው ጉልላት ላይ የተመለከቷት ደግሞ ራሳቸውን ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አሳልፈው የሰጡት አባ ቆስጠንጢኖስ (Fr. Costantine) ናቸው::
))(

እኒህ አባት ካሰርየት ኤል ሪሐን (Kasryet El-Rihan) ውስጥ በምትገኘው በድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በምሽት ማኅሌት ላይ ዕጣን እያሳረጉ ሲጸልዩ ድንገት ቤተ ክርስቲያኗን ብርሃን ሞላት:: ይህ የሆነው ኦገስት 21 ቀን 1969 ዓ.ም. ነበር::

እኔ ክህነት እንድቀበል በመጀመሪያ አሳብ የቀረበልኝ እ.አ.አ. በ1942 ዓ.ም. ሲሆን የተቀበልሁት ግን ከሠላሳ ዓመት በኋላ እ.አ.አ. በ1969 ዓ.ም. ነው:: ይህ የሆነውም በድንግሊቱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነበር:: በመጨረሻ ድንግል ማርያም ራሷ ወደዚህ ማዕረግ እስክትስበኝ ድረስ ለዚህ ክብር የምበቃ ሰው አይደለሁም በማለት ከክህነት ስሸሽ ኖሬያለሁ::

ኤል ናትሩን ሸለቆ (El-Natroun Valley) ውስጥ ከሚገኘው ከድንግል ማርያም ገዳም በወጣሁ በመጀመሪያው ሳምንት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስብከት ስሰብክ በጉባኤው ላይ የተገኙት ምዕመናን ድንግል ማርያም በመሠዊያው ፊት ለፊት በሙሉ ክብር ቆማ እንደ ነበር ገለጹልኝ:: ድንግል ማርያምን ሙሉ ለሙሉ የተመለከቷት ሰዎች እጅግ በጣም ተደንቀው ስለ ነበር አንዲት ቃል እንኳ ከአንደበታቸው ሊያጡ አልቻሉም ነበር::

## 2/ ሙሽራሽ ይህ ነው::

በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ላይ ተገኝታ የማታውቅ አንዲት ባለጸጋ እመቤት እኔን ለማግኘት ወደ ቤተ ክርስቲያን መጣች:: ኤል ዶኪ (El-Dokki) ከሚባለው የከተማ ዳርቻ የመጣች አንዲት ወጣት እመቤትም ከሴትዮዋ ጋር ነበረች:: ወጣቷ እመቤት ለሦስት ተከታታይ ቀናት በሕልሟ ድንግል ማርያም ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እየጠቆመች «ሙሽራሽ ይህ ነው!» ስትላት ተመለከተች:: ወጣቷ የተመለከተችውን ሕልም ለቤተሰቦቿ ተናግራለች:: ወደ እኔ መጥታም ዕንባዎቿ በጉንጮቿ ላይ እየወረዱ ምን ማድረግ እንዳለባት ጠይቃኛለች::

በጣም የተደነቅሁት ደግሞ በሚቀጥለው ሳምንት አንዲት ሌላ ልጃገረድ ወደ እኔ መጥታ ተመሳሳይ ሕልም ማየቷን ስትነግረኝ ነበር:: ድንግል ማርያም ለእርሷም ክርስቶስን እያመለከተቻት «ሙሽራሽ ይህ ነው!» ብላ እንደነገረቻት ነው የገለጸችልኝ:: እርሷም እንደ ቀድሞዋ





እመቤት ልቧ ተነክቶ ስለ ነበር «ማድረግ ያለብኝ ነገር ምንድር ነው?» ብላ ነው የጠየቀችኝ::

## 3/ ድንግል ማርያምና የዘይቱ ብልቃጥ::

አንድ ረቡዕ ቀን ከቅዳሴ በኋላ ከጥቂት ሴቶች ጋር በመነጋገር ላይ ሳለሁ ድንቅ ገጽታ፣ ክብ የመልክ ቅርጽና መካከለኛ ቁመት ያላት አንዲት ሙሉ ነጭ ቀሚስ የለበሰች እመቤት ብልቃጡን ከፍቼ እንድመለከተው ግድ እያሳሰበችን አንድ የዘይት ብልቃጥ ሰጠችኝ:: በጣም በሚገርም ሁኔታ የእመቤቲቱን መልክ በብልቃጡ ዘይት ውስጥ ተመለከትሁት::

ከዚህ በኋላ እመቤቲቱ ተጨማሪ ብልቃጦችን ሰጠችኝና ጥቂት ፈገግ ብላ ከአጠገቤ ተሰወረች::

ዓመቱን ሙሉ ይህችን እመቤት በድጋሚ ለመመልከት ብሞክርም አልቻልሁም:: ከየዕለቱ ቅዳሴ በኋላ ስለ እርሷ መረጃ ለማግኘት ብጠይቅም ፈጽሞ ላገኛት አልቻልሁም::

እግዚአብሔር ይጠብቃቸውና ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊን ገዳም ውስጥ በሚገኝ ባእታቸው ውስጥ ሳገኛቸው ከፊሎቹን በዘይት የተሞሉ ብልቃጦች ለእርሳቸው ሰጠሁና ከፊሎቹን ደግሞ ለራሴ አስቀረሁ:: ይህች እመቤት ድንግል ማርያም ትሆን? እያልሁ እደነቃለሁ::

## 4/ ድንግል ማርያምና በካንሰር በሽታ የተጠቃችው ሴት::

አቤቱ ጌታ ሆይ! ይህች ሴት እንዲህ የምታነባው ለምንድር ነው? ዕንባዎቿ እኮ እንደ ጎርፍ ውኃ እየወረዱ ነው! ሴቲቱ ሰው ሁሉ ቅዳሴውን አስቀድሶ ወደየቤቱ ከሄደ በኋላ በመሠዊያው ፊት ወድቃ በምሬት ከልቧ እያለቀሰች ነበር:: ስለሆነም ወደ እርሷ ጠጋ ብዬ ምን እንደሚያስለቅሳት ጠየቅኋት::

በልቧ ውስጥ ድንግል ማርያም አልረዳችኝም የሚለው አሳብ ስላለ የምታለቅስ መሆኗን ገጸለችልኝ:: ይህን አስመልክታ ስትነግረኝ እንዲህ ትለኝ ነበር:- «ድንግል ማርያም ለብዙ ሰዎች በመጸለይ ከበሽታዎቻቸው አድናቸዋለች . . . ይሁን እንጂ እኔ አንገት ላይ የወጣውን አደገኛ ዕጢ ግን እንዲሁ ትታዋለች . . . ትናንሾቹ ልጆቼ በጣም ቢፈልጉኝም ሐኪሞቹ ከአሁን በኋላ ለ40 ቀናት ብቻ እንደምኖር እየነገሩኝ ነው::»



www.ethiopianorthodox.org

እንዲህ ዓይነቱን ጥጥ ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ነበር:: ይህ በመሆኑም አንድ ባለጸጋ ሰው ወደዚህች ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ከፊሉን ጥጥ ለራሱ በመግዛት ገንዘቡን ከፍሎ ይሄዳል::

ሙሉ አንድ ቀን ሳይውል ድንግል ማርያም በራእይ ተገልጣ በትሕትና በመገሰጽ ጥጡን ወዳመጣበት ቦታ እንዲመልስ ጠየቀችው::

ለድሆች ለጋስ የሆንሽው የአዳኛችን የመድኃኒዓለም እናት ሆይ፤አንቺ የተባረክሽ ነሽ!

**8/ ብርቱ የጆሮ ውስጥ ህመም::**

ወ/ሮ ኤ.ኤፍ. (Mrs. A.F.) ሐኪሞች ሊያድኑ ያልቻሉት ሕመም በጆሮዋ ውስጥ ይቀሰቀሳል:: ሕክምናው ወይም መድኃኒቱ ሊጠቅማት ካልቻለ ከጥፋት በስተቀር ምን ሊበጃት ነው!? በቤቷ ውስጥ ያለው የድንግል ማርያም ስዕል ላይ ጆሮዋን አስጠግታና በታላቅ እምነት ውስጥ ሆና ድንግል እንዲህ ባለው ጊዜ እንድትረዳት እንጂ እንዳትተዋት አጥብቃ ጸለየች::

እምነትና ተስፋ በውስጧ ሲሰፍኑባት ታወቃት:: እንቅልፏን ካንቀላፋች በኋላ ድንግል ማርያም ተገልጣ «ስትጠሪኝ ስለ ሰማሁሽ እነሆ መጥቼያለሁ . . . የመጣሁት ልፈውስሽ ነው::» አለቻት:: ሴቲቱ ከእንቅልፏ ስትነቃ ሙሉ ጤናማ ሆና ነቃች::

**9/ ከችግሮቼ እንድወጣ እርዳኝ::**

የሚሠራው በትምህርት መስክ ውስጥ ቢሆንም ሁለት ልጃገረድ ልጆቹን ለመዳር ብዙ ወጪ ስላወጣ ብዙ ከስሯል:: ኪሳራው ብዙ ስለነበርም የቤት ዕቃዎቹን፣ የሚስቱን የወርቅ አምባሮች ለመሸጥ ተገዷል::

ብዙ ሳይቆይ በትምህርት ቤቱ ውስጥ በአደራ መልክ በእርሱ ዘንድ ተቀምጦ የነበረ 500 ብር መሰረቁን ሲሰማ በንዴት ራሱን ሊስት ደረሰ:: በማግስቱ ሒሳብ ተቆጣጣሪው (ኦዲተሩ) መጥቶ ገንዘቡ መጥፋቱን ማረጋገጡ ስለማይቀር ወደ ወኅኒ መውረዱ አይቀርም:: አሉባልታና ውርደት ፊት ለፊት ተጋፈጡት::

በመጀመሪያ ራሱን ሊያጠፋ ወሰነ:: ከዚህ በፊት ግን የመጨረሻ አድርጎ የወሰደው አማራጭ የቤተ ክርስቲያንን እርዳታ መሻት ስለሆነ በቀጥታ ወደ እኔ መጥቶ ተስፋ በቆረጠ ልሳን «ከችግሮቼ እንድወጣ እርዳኝ!» አለኝ::



www.ethiopianorthodox.org



እኔም ስብከቴን እስከጨርስ ድረስ እንዲጠብቀኝ ነገርሁት:: ጊዜው እሁድ ምሽት ስለ ነበር በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በጉባኤው ላይ ታድመው ነበር:: ያ ጎስቋላ ሰው በአስተዳዳሩ ጽሕፈት ቤት ውስጥ እየጠበቀኝ መሆኑን እንዳልዘነጋ ስለ ጉዳዩ ቁራጭ ወረቀት ላይ ጽፌ ከፊት ለፊቴ አስቀመጥሁ:: ይሁን እንጂ የጉባኤው አባላት ሰውየውን እንዲረዱት ሳልናገር ስብከቴን አጠቃለልሁ:: ሰዉ ሁሉ ከቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ወጥቶ ከሄደ በኋላ ግን ሰውየው ትዝ ስላለኝ ጉዳዩ ራሴን መታኝና፡- አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፤እንዴት ልዘነጋው ቻልሁ?! ይህ የሆነው ለምንድር ነው?! አልሁ::

በዚህ ቅጽበት በመሠዊያው አጠገብ የቆመች አንዲት ሴት እንደምትፈልገኝ ስለ ተነገረኝ ወደ ቤተ መቅደሱ ገባሁ:: ሙሉ ለሙሉ የለበሰችው ነጭ ቀሚስ ሲሆን ውበቷ እጅግ ድንቅ ነው:: ፈገግ ብላ እጇን በመዘርጋት ገንዘብ ሰጠችኝና «አንድን ሰው ከችግሩ እንዲወጣ እርዳው!» አለችኝ:: የተናገረችኝ ይህ ቃል እስከ ዛሬ ድረስ በጆሮዎቼ ውስጥ ያስተጋባል::

አቤቱ ጌታዬ ሆይ! ቃሏ በአስተዳደሩ ጽሕፈት ቤት ውስጥ ያለው ሰው ከተናገረኝ ቃላት ጋር ተመሳሳይ ናቸው! ያቺ ውብ ሴት የሰጠችኝ ገንዘብ ምስኪኑ ሰው ከጠፋበት ገንዘብ ጋር እኩል 500 ብር ነበር::

ያቺ እመቤት ማን ነበረች?! ይህን የረሳሁበት ምክንያትስ ምንድር ነው? ምናልባት ይህ የሆነው እግዚአብሔር ራሱ መፍትሔውን ስለ ሰጠ ይሆናል::

**በጎውን ሁሉ ለእኛ ያደረገና የሚያደርግ እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን::**



የሕክምና ባለሙያዎች (Doctors) በአንድ ድምፅ የማይድን በሽታ ነው በማለት አረጋግጠዋል። ይሁን እንጂ ድንነቱ በድንግል ማርያም አማላጅነት ውጤታማ ሆኗል። በውስጥ ልብሶቹ ላይ ጥቂት መስቀሎች ታይተዋል።



«ዐይነ ሥውር ነበርሁ፤አሁን ግን አያለሁ።» የማየት አቅሙን ቢያጣም በድንግል ማርያም አማላጅነት እንደ ቀድሞው ተመልሶለታል።








ብዛት ያለው ሕዝብ የቅድስት ድንግል ማርያምን መገለጥ ሲመለከት።
(ኤል አንዋር መጽሔት፤ቤይሩት)



www.ethiopianorthodox.org

**የግብጽ ጋዜጣ፤ዓርብ ኤፕሪል 11 ቀን 1969 ዓ.ም.**
**«የድንግል መገለጥ እስከ ዛሬ ድረስ እየታየ ነው»**

ከሩብ ሚሊዮን የሚበልጡ ግብጻውያንና የውጪ ጎብኚዎች ካይሮ አጠገብ በሚገኘው በዜይቶን የድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየተካሄደ ያለውን የድንግል ማርያም ዓመታዊ የመገለጥ በዓል በማክበር ላይ ናቸው።

ምንም እንኳ ይህ መገለጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ታየ ተብሎ ሪፖርት ከተደረገ አንድ ዓመት ያለፈ ቢሆንም አሁን ድረስ እየተገለጠ ነው። የዚህ መገለጥ የቅርብ ጊዜ ሪፖርት ኤፕሪል 4 ቀን ሲሆን በዚህ የ30 ደቂቃ የመገለጥ ጊዜ የታየው በቤተ ክርስቲያኑ መካከለኛ ጉልላትና በቤተ ክርስቲያኑ አጥር ላይ ከፍ ብሎ በተሰቀለው መስቀል መካከል ነው። መገለጡ ከቤተ ክርስቲያኑ አጥር ውጪ ቆመው ወደ ነበሩት ሰዎች ራሱን ይነቀንቅ ነበር።

በሌሎች ሦስት የቅርብ ጊዜ ክስተቶች መገለጡ የታየ ሲሆን በእያንዳንዱ ጊዜ ከመገለጡ ቀደም ብሎ የርግቦች ቅርጽ የሚመስል ነጭ የሚያንጸባርቅ ደመና ከመታየቱም በላይ ቤተ ክርስቲያኑን የሸፈነ ብርሃን ወርዶ ታይቷል። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ 4ኛ የእስክንድርያና የመላው አፍሪካ የቅብጥ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በዚህ የመገለጥ ዓመታዊ በዓል ላይ የሚነበብ የጽሑፍ መልዕክት ልከዋል። መልዕክቱም በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ በዓሉን በማክበር ላይ ላሉት ሰዎች ተነቧል።

**የማይድኑ በሽታዎች።**

አሥራ ሁለት ሰዓት የፈጀው የበዓል አከባበር ከሰርክ 11:00 ሰዓት ጀምሮ እስከሚነጋ ድረስ ቀጥሎ ነበር።

የፓትርያርኩ መልእክት፡- የድንግል ማርያም መገለጥ በስሟ በተሰየመውና ዜይቱን ውስጥ በሚገኘው ቤተ ክርስቲያኗ ውስጥና ውጪ ከኤፕሪል ወር 1968 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ከተባበረው የአረብ ኢምሬት (ዩ.ኤ.አር.) እና ከሌሎች የተለያዩ አገሮች በመጡ በሺዎች በሚቆጠሩ ሰዎች መታየቱን ገልጧል።

ፓትርያርኩ ከዚህ በተጨማሪ ሲናገሩ፡- በማይድኑ በሽታዎች ተይዘው በመሰቃየት ላይ የነበሩ ብዛት ያላቸው ሰዎች ይህን እይታ ከተመለከቱ በኋላ ከበሽታዎቻቸው ተፈውሰዋል።





ፓትርያርኩ፡- ቅዱሱ ቤተሰብ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት በስደት ወደ ግብጽ እንደመጣና ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ድንግል ማርያምና ዮሴፍ ኢን ሻምስ አጠገብ የሚገኘውን ዜይቶን መጎብኘታቸውን ሳይጠቅሱ አላለፉም . . .

ይህ መገለጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በኤፕሪል ወር 1968 ዓ.ም መታየቱ ሪፖርት ከተደረገ በኋላ የቅብጥ ፓትርያርክ ጉዳዩን ለማጣራት አንድ ልዩ ኮሚቴ እንዲቋቋም አድርገዋል።

**የፓትርያርኩ መግለጫ።**

ጉዳዩን ለማጣራት በተቋቋመው ልዩ ኮሚቴ ውስጥ ያሉት አባላት መገለጡን እንደ ተመለከቱ ሪፖርት አቅርበዋል። ከዚህ ሪፖርትና ከሌሎች መረጃዎች ላይ በመነሣት ፓትርያርኩ ድንግል ማርያም ዜይቶን ውስጥ በምትገኘው ቤተ ክርስቲያኗ ላይ እና ውስጥ መገለጧን በይፋ አረጋግጠዋል።

የቤኒ ሴይፍ ሀገረ ስብከት ጳጳስና የኮሚቴው ሊቀመንበር የሆኑት አቡነ አትናቴዎስ ስለ ተመለከቱት ሲናገሩ፡- «መገለጡ የሚያበራና የሚያንጸባርቅ ነጭ ደመና ሲሆን መጠኑም 100 ሴ.ሜ. በ60 ሴ.ሜ. ይሆናል . . . «ምስሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ከተሰቀለ በኋላ በድንግል ማርያም ገጽታ ላይ ይነበብ የነበረውን ሁኔታ (ኀዘነ ልቡና) ይገልጣል።» ብለዋል።

ጳጳሱ አቡነ አትናቴዎስ ከዚህ በመቀጠል ሲናገሩም፡- ምስሉ ከመገለጡ ቀደም ብሎ በከፍተኛ ፍጥነት የሚበሩና የርግብ ቅርጽ ያላቸው ነጫጭ ደመናዎች ይታያሉ። ጳጳሱ ከዚሁ ቀጥለው ሲናገሩም፡- በአንድ ወቅት በራሱ ዙሪያ የሚያስደንቅ ብርሃን በሚያወጣ የደመና ክበብ (ሀሎ) የተከበበና ሙሉ የሰው መጠን ያለው ምስል ተገልጦ ተመልክቼያለሁ ብለው ተናግረዋል።

እስከ ዛሬ ድረስ ብዛት ያላቸው የውጪ ዜጎች ወደ ካይሮ በመጉረፍ መገለጡን እየተመለከቱ ሲሆን በዚህም ቅዱሱ ቤተሰብ በአንድ ወቅት ሲና በረሀን አቋርጦ ግብጽ መግባቱን እያስታወሱ ነው . . .

**ጆርጅ ሻፊቅ**

---

**ዘ ኒውዮርክ ታይምስ፤እሁድ ሜይ 5 ቀን 1968 ዓ.ም.**
**«ካይሮ ውስጥ የድንግል መገለጦች ይፋ ሆኑ።»**

**ስለ መገለጡ ከሚናገሩት ሰዎች መካከል የቅብጥ ጳጳስ አንዱ ናቸው።**

ካይሮ፤ዛሬ ሜይ 4 ቀን ረዣዥም ጢም ያላቸውና ጥቋቁር ቀሚሶች የለበሱ አሥራ ሁለት የቅብጥ ቤተ ክርስቲያን አባቶች የፕሬዝዳንት ገማል አብደል ናስር ትልቅ ፎቶግራፍ በተሰቀለበት በፓትርያርኩ ልዩ ቤተ



www.ethiopianorthodox.org

መንግሥት ውስጥ ተቀምጠው ድንግል ማርያም በሚያስደንቅ ሁኔታ ካይሮ ውስጥ መገለጧን የሚበስረውን ሪፖርት አረጋግጠዋል::

ይሁን እንጂ የእስክንድርያ ፓትርያርክ የሆኑት አቡነ ቄርሎስ 4ኛ በጋዜጣዊ መግለጫው ላይ አልተገኙም ለጋዜጠኞች ተባዝቶ በታደለው ወረቀት ላይም ፊርማቸው አላረፈም::

ለጋዜጠኞቹ በታደለው ወረቀት ላይ የሰፈረው ሪፖርት:- ካይሮ አውራጃ ውስጥ በምትገኘው በዜይቶን ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ላይ ድንግሊቱ መገለጧን «በሺዎች የሚቆጠሩ ግብጻውያንና የውጪ ሀገር ዜጎች» መስክረዋል የሚል ነው::

በዚህ ዓረፍተ ነገር ግርጌ የተጻፈው «ከጳጳሱ መኖሪያ» የሚል ቃል ብቻ ነው:: አንድ ካህን ግን ፓትርያርኩ አቡነ ቄርሎስ የመጀመሪያው ዶኩመንት ላይ ፈርመዋል ሲል ሌላው ካህን ደግሞ አቡነ ቄርሎስ ጉዳዩ እስኪጣራ ድረስ ምንም ዓይነት መግለጫ ለመስጠት ፈቃዳቸው አይደለም በማለት ተናግሯል::

የቤኒ ሴይፍ ጳጳስ የሆኑት አቡነ አትናቴዎስ ያለፈው ማክሰኞ ከጠዋቱ 2:45 እስከ ጠዋቱ 5:00 ሰዓት ድረስ «በጠንካራ ጨረር» የታጀበውን መገለጥ መመልከታቸውን ይፋ አድርገዋል:: አቡነ አትናቴዎስ ይናገሩ የነበረው በአረብኛና በእንግሊዘኛ ቋንቋ ነበር::

ቅብጣውያን የግብጽ ጥንታውያን አገር በቀል ክርስቲያኖች ሲሆኑ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጋር በዶክትሪን (በነገረ ሃይማኖት) ኅብረት አላቸው::

«የቱሪዝምና የማስታወቂያ ሚኒስቴር ክፍል» በሚል የራስጌ ርዕስ ከተባዛ ሁለተኛ ጽሑፍ በታች በትልቁ የተጻፈው ርዕስ ደግሞ ሐተታውን የሚጀምረው «ድንግል ማርያም በየዕለቱ እየታየች ነው» በማለት ነው:: ይኼኛውም ጽሑፍ ጋዜጣዊ መግለጫው በተሰጠበት ወቅት ለጋዜጠኞቹ ታድሎ ነበር::

እንደ ጋዜጠኞቹ ሪፖርት ከሆነ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገለጠውን ምስል ኤፕሪል 2 ቀን የተመለከተው የጋራዥ ጠባቂ የሆነ አንድ ሙስሊም ሲሆን እርሱም የድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ካህን የሆነውን ሰው ከእንቅልፉ በመቀስቀስ ራሷን ወደ ታች በመወርወር ነፍሷን ለማጥፋት የቤተ ክርስቲያኑ ጣሪያ ላይ ወጥታ ያኀበሰች ሴት መኖሯን ነግሮታል::





ከዚያን ጊዜ በኋላ ቤተ ክርስቲያኒቱ እንደ ሐውልት ቆመው በንቃት በሚጠባበቁ በሺዎች በሚቆጠሩ የምሽት ሰዎች ትኩረት ስላገኘች አካባቢው በፈንዲሻና ሽንብራ ሻጮች አጀብ ተሞልቶ ነበር:: በወቅቱ ስለ መገለጡ በጣም ተደጋጋሚና ጥቂት የሚቃረኑ ሪፖርቶች ተሰጥተው ነበር::

እዚሁ አገር ታትሞ የወጣ አንድ ጋዜጣ ሁኔታውን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት:- «ሌላዋ ፍልስጤማዊ ስደተኛ! እስራኤል በተቆጣጠረችው በኢየሩሳሌም ግዛት ውስጥ ያለውን ሁኔታ ልትቋቋመው አልቻለችም::» ብሏል::

ቁርዓን የድንግልና ልደትንና ኢየሱስ ክርስቶስ መሐመድን ቀድሞ የተገለጠ ነቢይ መሆኑን ስለሚያረጋግጥ ክርስቲያኖችም ሆኑ እስላሞች ለድንግል ማርያም ክብር አላቸው::

አቡነ አትናቴዎስ ሪፖርት ስለተደረገባቸው መገለጦች ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል:- «መገለጦቹን መልካም ወይም ከእግዚአብሔር የሆኑ ምልክቶች ናቸው ብለን እናስባለን፤እርሱ በተቀደሱት የኢየሩሳሌም ቦታዎች ላይ አይሁድ ያደረጉትን ነገር ይመለከታልና:: እግዚአብሔር በዚህ ደስተኛ ስላልሆነ እኛን ይረዳናል:: የተከሰተው ነገር የሚያልፍ እንጂ ቋሚ ሆኖ የሚቀጥል አይደለም:: እግዚአብሔር ግብጽ ውስጥ ያሉትን ሰዎችና የአረቦቹን ነገሥታት መንፈስ እያጠናከረ ነው፤የሚመጣውንም ድል እየጠበቅን ነው::»

«ከጳጳሱ መኖሪያ» የሚል ጽሑፍ ያረፈበት የተባዛ ዶኩመንት ጽሑፉን የሚጠያቃለለው «. . .ልጄንም ከግብጽ ጠራሁት::» በሚለውና ለመንፈስ ቅዱስ በተጠቀሰው ጥቅስ ነው::

ቶማስ ኤፍ ብራዲ
የኒዮርክ ታይምስ ልዩ ጋዜጠኛ

በጎውን ሁሉ ለእኛ ያደረገና የሚያደርግ እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን!



www.ethiopianorthodox.org

## መጽሐፍ አሥራ ሦስት

የመጽሐፉ ርዕስ:- እግዚአብሔርና ሰው
አዘጋጅ:- ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ
ተርጓሚ:- አያሌው ዘኢየሱስ
የመጽሐፉ ይዘት:- «እግዚአብሔርና ሰው» የተባለው መጽሐፍ እስከ ዛሬ ድረስ ከተረጎምኋቸው የአቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ መንፈሳዊ መጻሕፍት መካከል በመጠን ትልቁ ነው:: በዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ክፍል ውስጥ የእግዚአብሔር ብቻ ስለሆኑ ባሕርያት ማለትም ስለ ፈጣሪው፣ ስለማይወሰነው፣ ስለ ቅዱሱ፣ ስለ ኃያሉና ስለ ትሑቱ እግዚአብሔር እናነባለን:: በሁለተኛውና «እግዚአብሔር ከሰው ጋር ያለው ዝምድና» በሚለው ርዕስ ሥር ደግሞ እግዚአብሔር ከሰው ጋር ዝምድናውን የጀመረው በፍቅርና በመስጠት ስለ መሆኑ፣ስለ እግዚአብሔር በረከት፣ ስለ ጥበቃው፣ ስለ መልካምነቱ፣ ስለ ማዳኑ፣ ስለ ጥበቡ . . . ወዘተ እንረዳለን:: በመጽሐፉ ሦስተኛ ክፍል እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ ስላለው ቦታ፣ ለእኛ ስለሚሆን ስለ እርሱ ቃል፣ ከእርሱ ጋር ስለሚኖረን ዝምድና፣ ከእርሱ ስለ መሸሸችን፣ ከእርሱ ጋር ኅብረት ስለ መፍጠር፣ እርሱን ስለ መጠበቅ . . . ወዘተ እናውቃለን:: ከዚህ የአቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ መንፈሳዊ መጽሐፍ የምንገበየው መንፈሳዊ ዕውቀትም ይህንኑ ነው::
የተተረጎመበት ቦታ:- አዲስ አበባ
የታተመበት ጊዜ:- መስከረም 2001 ዓ.ም.
የገጽ ብዛት:- 240
ዋጋው:- ብር 19.00

**«የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል::» 2ኛ ጢሞ 3:16-17::**

**ይቆየን!**



www.ethiopianorthodox.org